


6

ትምህርት

የተባበረ *መንግሥት*

ባለፈው ክፍለ ትምህርት የእግዚአብሔር ሕዝብ በኢያሱ መሪነት ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደገቡና በመሣፍንቱ ዘመን ያጋጠሟቸውን የተለያዩ ችግሮች ተመልክተናል። ጊዜው እስቸጋሪ የነበረ ቢሆንም እግዚአብሔር ከባዕዳን ገዢዎቻቸው ነጻ የሚያወጧቸውን መሪዎች ያስነሳላቸው ነበር። በዚህ ዘመን ነበር እግዚአብሔር የመጨረሻውን መስፍን ሳሙኤልን ያስነሳላቸውና ለእሥራኤን መሪ ያደረገው። በዚህ ክፍለ ትምህርት ይሣሙ ሳኦል የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ እንዴት እንደተመረጠና ከእርሱ ቀጥሎም ዳዊትና ሰሎሞን በተከታታይ በእስራኤል ላይ እንደነገሡ እንመለከታለን።

የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉሥ የሆነው ሳኦልን ቀብቶ ያነገሰው ሳሙኤል ነበር። በእስራኤል ታሪክ የነገሥታት ዘመን የተጀመረው በሳኦል ዘመነ መንግሥት ነው። ይህ የተባበረው መንግሥት የቀጠለው እስከ ሰሰሞን ዘመን ሲሆን፣ የሦስቱ የተባበረው መንግሥት ነገሥታት ስም ሳኦል፣ ዳዊትና ሰሎሞን ይባላል። እያንዳንዳቸውም 40 ዓመት ያህል ነግሰዋል።

የነገሥታት ዘመን በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ብሩህ ጊዜ ነበር። የጨለማው ዘመን በወርቃማ ዘመን ተተካ። የእግዚአብሔር ተስፋዎችም ተሟሉ። እስራኤል በዓለም ሕዝቦች መካከል ገናና ሆነች። ሕንፃዎቿ፣ ሥነ ሕፍቿና ብልጥግናዎቿ ሰዓሰም ሕዝብ በግልጽ የሚታዩ የእግዚአብሔር በረከቶች ነበሩ። በኅዚህ በሦስት ነገሥታት ዘመን እስራኤል ስለነበራት አስደናቂ የበረከትና የብልጽግና ጊዜ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

የክፍለ ትምህርቱ አስፈላጊ

- የንጉሥ ጥያቄ
- የሳኦል ዘመነ መንግሥት
- የዳዊት ዘመነ መንግሥት
- የሰለሞን ዘመነ መንግሥት

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- እስራኤላውያን ንጉሥ እንዲኖራቸው በመጠየቃቸው እግዚአብሔር ለምን እንዳልተደሰተ መግለጽ።
- የመጀመሪያዎቹ ሦስት ነገሥታት የንግሥት ዘመን ምን እንደሚመስል መግለጽና የእያንዳንዱን ጠንካራና ደካማ ጐን መግለጽ።
- ለእስራኤል ነገሥታት ጌታን በናዳም መታዘዝ እንዴት አስፈላጊ እንደነበረ መግንዘብ።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ከ 1ኛ ሳሙ 8 እስከ 1ኛ ነገ 11 ድረስ ያለውን በጥንቃቄ አንብብ።
2. ትምህርቱን ደረጃ በደረጃ እየተከታተልክ ለክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ የተሰጡትን ጥያቄዎች መልስ፤ ከዚያም የመከራ ፈተናውን በመውሰድ መልሶችህን በመጽሐፉ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት የተሳሳትከው ካለ አስተካክል።

የትምህርቱ ዝርዝር

ያግኙሙ ጥያቄ

ነሳሙ 8 አንብብ

ዓላማ 1 የእሥራኤልን ንጉሥ በተመለከተ እግዚአብሔር የሰጠውን መመሪያዎችና ማስጠንቀቂያዎች ለመግለጽ።

የእግዚአብሔር መመሪያ

እስራኤላውያን እስካሁን ድረስ ንጉሥ ተብሎ የሚጠራ መሪ አል ነበራቸውም። ንጉሣቸው እግዚአብሔር ነበር። "ቲዎክራሲ" ወይንም "መለኮታዊ አስተዳደር" ነበራቸው። እንዲህ ዓይነቱ አስተዳደር እግዚአብሔር በመረጣቸው መሪዎች አማካይነት የሚከሔድ አመራር ሲሆን ይህም ድክመት አልነበረውም። ሆኖም ሰዎቹ ከዚህ አደጉት አመራር የሚገኘውን ጥቅምና በረከት ሊረዱ አልቻሉም። ምንም እንኳን ፍጹም የሆነ ፈቃዱ ባይሆንም፣ የእስራኤል ሕዝብ ንጉሥ ይኖራቸው ዘንድ እግዚአብሔር ፈቀደላቸው። ንጉሥ እንዲኖራቸው የሚጠይቁበትን ወቅት እግዚአብሔር አስቀድሞ ያውቅ ስለነበር፣ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት ስለ ነገሥታት ወግና ሥርዓት መመሪያ ሰጣቸው (ዘዳ 17፡ 14-20)።

(1). በዘዳ 17:14-20 ላይ የተጻፈውን ካነበብክ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. ንጉሥ የሚሆነው ማን ነበር?
ለ. ንጉሥ የሚያደርገው ምን ነበር?
ሐ. ንጉሥ ማድረግ የማይገባው ምን ነበር?
ስለንጉሥ የተሰጡትን መመሪያዎች በአጭሩ እንዲህ ልናስቀምጣቸው እንችላለን።

1. የእስራኤል ነገሥታት በራሳቸው ፈቃድ ማስተዳደር የለባቸውም።
2. ለራሳቸው ብርና ክብር መቆም የለባቸውም።
3. ዓላማቸው ሊሆን የሚገባው ስሕዝቡ ጥቅም ሲሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ምሪት መፈለግና መከተል ነበር።
4. ንጉሥ እንደማንኛውም ተራ እስራኤላዊ ለእግዚአብሔር ተገዥ ሊሆን ይገባዋል።

እነዚህ አምላካዊ መመሪያዎች በእስራኤል ላይ በነገሡት ነገሥታት ሁሉ ተፈጻሚ ሆነዋል። ንጉሡ በእግዚአብሔር ፈቃድ እስከተመላለሰ ድረስ ይብለጽግ ነበር። ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛትን ሲተውና አለመታዘዝ ሲያምር ከሥልጣኑ ይወርድ ነበር።

የሕዝቡ ጥያቄ

እስራኤላዊያን ራሳቸውን ከጎረቤት አገሮች ጋር ሲያስተያዩ ሕብረት የነደላቸውና ይካሞች እድርገው ራሳቸውን ቆጠሩ። በዚህ ላይ ደግሞ የሳሙኤል ልጆች ክፋዎች ስለነበሩ የወደፊት መሪዎቻቸው እንዳይሆኑ ፈለጉ (1ኛ ሳሙ 8:1-5)። ስለዚህ በሳሙኤል አገር በራማ ተሰብስበው ንጉሥ እንዲሾምላቸው ጠየቁት። አለመታዛታቸውና አለመታዘዛቸው ከባድ ኃጢአት መሆኑን የተረዳው ሳሙኤል በጋዘን ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀረበ። እግዚአብሔር እስራኤል ለእርሱ የተለየ ሕዝብ እንዲሆኑ ሲፈልግ እነርሱ ግን የጎረቤት አገር ሕዝቦችን መምሰል ፈለጉ (1ኛ ሳሙ 8:5፣ 19-20)። ሳሙኤል በኋላ እንዳመለከተው፣ ንጉሥ መጠየቃቸው የእግዚአብ ሔርን ጥበቃ አለማመን መሆኑን ያሳያል (1ኛ ሳሙ 12: 6-12)። ለሳሙኤል "በእነርሱ ላይ እንዳልነግስ እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ" በማለት አሳሰበው (1ኛ ሳሙ 8:7)።

(2). እግዚአብሔር እኔን እንጂ አንተን አልናቁም በማለት ለሳሙኤል የተናገረው ለምን ነበር?

የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ

ንጉሥ እንዲኖራቸው መምረጣቸው ውጤቱ ምን እንደሚሆን ለሕዝቡ እንዲያስጠነቅቅ እግዚአብሔር ሳሙኤልን መራው።

(3). 1ሳሙ 8፡10-22 ላይ ያለውን ካነበብህ በኋላ ከዘዳ 17:14-20 ጋር በማነጻጸር የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ በአጭሩ መልስ።

ሀ. በዘዳ 17:14-20 እግዚአብሔር በሰጠው መመሪያ መሠረት የንጉሱ ዋና ግዴታ ምን ነበር? ንጉሡ ይህን ግዴታ ከፈጸመ የሚከተሉት ውጤቶች ምንድን ናቸው?

ለ. 1ሳሙ 8:10-22 ላይ እግዚአብሔር በሳሙኤል በኩል በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት የንጉሡ ዋና ተግባር ምን ነበር? የሚከተለውስ ምን ነበር?

ሕዝቡ ድርጊታቸው የሚያስከትለውን ውጤት ከነገሡ በኋላም ንጉሥ ያስፈልገናል የሚለው ጥያቄአቸው እየከረረ መጣ። ስለዚህም ንጉሥ እንዲሾምላቸው እግዚአብሔር ሳሙኤልን አዘዘው (1ሳሙ 8:19-22)። ሳኦል ንጉሥ እንዲሆን በተቀባበት ወቅት ሳሙኤል መሪያቸው እንደመሆኑ መጠን የመጨረሻ ንግግሩን አሰማ (1ሳሙ 12)። በንግግሩም በፊታቸው ያለንቀሩ እንደተመላለሰ አስገዘባቸው። እነርሱም ደኅንት (ቁ 3-5)። እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገላቸውን ሁሉ ጠቀሰላቸው (ቁ 6-11)። ንጉሥ

መጠየቃቸው በእግዚአብ ሔር አለመተማመንና በደል መሆኑንም አንድገና ነገራቸው (ቁ 12)።

ሕዝቡም የሳሙኤል ቃልና ቃሉን ለማጽናት እግዚአብሔር ያደረገው ተአምራት አስፈራቸው። "ንጉሥ በመለመናችን በኃጢአታችን ሁሉ ላይ ይህን ክፋት ጨምረናልና፣ እንዳንሞት ስለባሪያዎችህ ወደ እግዚአብሔር አልይ" ብለው ወደ ሳሙኤል ጮኹ (ቁ 19)። ሳሙኤልም ይህን እንደሚያደርግ ካረጋገጠላቸው በኋላ እግዚአብሔርን እንዳያሳስባ አሳሰባቸው። ሳሙኤል የተናገራቸው መመሪያዎች ሊጎሙ ላላቸው ነገሥታት ሁሉ ትንቢታዊ ቃሉች ነበሩ (ቁ 20-25)። "እግዚአብሔርን ፍሩ፣ ያደረገላችሁን ታላቅ ነገር አይታችኋልና በፍጹም ልባችሁ በእውነት አምልኩት። ነገር ግን ክፉ ብትሰሩ እናንተም ንጉሳችሁም ትጠፋላችሁ" (ቁ 24-25) አላቸው።

ሳሙኤል ምንም እንኳን የመሪነቱን ቦታ ቢለቅም በሕዝቡ ዘንድ ታላቅ ተደማጭነት ነበረው። ሕዝቡም የእርሱ ዕርዳታ እንዳይለያቸው ስለተማጠኑት ሳሙኤል ጥያቄአቸውን በደስታ ተቀበለ (1ሳሙ 12:19-23)።

(4). 1ሳሙ 12:23 ላይ በተጻፈው መሠረት ሳሙኤል ተስፋ የሰጠው ምን ለማድረግ ነበር?

(5). በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ልትጸልያላቸው የሚገባህን ሰዎች ስም አስፍር። ለእነርሱ መጸለይን እንዴትዘነጋ የስማቸውን ዝርዝር አልፎ አልፎ መመልከት መልካም ነው።

የሳኦል ዘመነ መንግሥት

1ሳሙ 9-15 አንብብ
ዓላማ 2 በሳኦል ሕይወት ውስጥ የተፈጸሙትን ዋና ዋና ድርጊቶች ለመግለጽ።

ለንጉሥነት መመረጥ

ምንም እንኳን ሕዝቡ በራሱ ድምፅ ባያመርጥም እግዚአብሔር እንደ ፍላጎታቸው የሆነ ንጉሥ ነበር ያስነገሳቸው። ስለሳኦልም የተነገረው አገላለጽ በ1ኛ ሳሙ 9:2 "ከእስራኤልም ልጆች ከእርሱ ያለቀ መልካም የሆነ ሰው አልነበረም"። ከሕዝቡም ሁሉ ያለቀ ከትከሻውና ከዚያም በላይ ቁመቱ ዘለግ ያሰ ነበር" የሚል ሲሆን ይህም ሕዝቡ ስለንጉሥ ያላቸውን ሥዕል የሚያሚያ ነበር።

ሳኦል ንጉሥ እንደሚሆን እግዚአብሔር ለሳሙኤል ከገለጠለት በኋላ ሳሙኤል በሚስጥር ቀባው (1ሳሙ 9:15-17፣ 9:27-10)። እግዚአብሔር ምርጫውን ለማረጋገጥ ስለሚሰጠው ምልክቶች ሳሙኤል ለሳኦል ከነገረው

በኋላ በጌልጌላ ለመሾናንት ተቀባጠሩ። ምልክቶቹም ሳሙኤል እንደተነበየው ተፈጸሙ። በመጨረሻም አስራኤላውያን በተሰበሰቡበት ንጉሥ በመሆየታቸው መበደላቸውን እንደገና ካሳሰባቸው በኋላ ሳሙኤል የሳኦልን ንጉሥነት በደሩ አወጀ (1ሳሙ 10:1-27)።

(6). 1ሳሙ 10:9 እንብብ። እግዚአብሔር ጸጋውንና አርዳታውን ለሳኦል ያሳየው እንዴት ነበር?

ድሎችና ውድቀቶች

ሳኦል ከወታደራዊ መሪነት አንጻር አስተዋይ ሰው ነበር። በተደጋጋሚም በድል ላይ ድል ተጎናጽፎአል። ራሱን በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ማምጣት ግን አልቻለም። ይህ ውድቀቱ በመጨረሻው እግዚአብሔር ከንጉሥነቱ እንዲሽረው አድርጎታል።

(7). ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ምንባቦች ካነበብህ በኋላ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ስለ ሳኦል ድሎች ወይም ውድቀቶች የሚሰጡትን መግለጫዎች ባጭሩ አስፍር። የመጀመርያው ምሳሌ እንዲሆንህ ተመርጧል።

ሀ. 1ሳሙ 11:1-15
ለ. 1ሳሙ 13:8-13
ሐ. 1ሳሙ 14:1-23
መ. 1ሳሙ 15:1-7 አሞሪውያንን በማሸነፍ ድል ተቀዳጀ
ሠ. 1ሳሙ 15:8-23

ከንጉሥነት መሻር

ሳኦል በጌልጌላ ጥፋትን ከፈጸመ በኋላ እርሱና ቤተሰቡ ለወደፊት አስራኤልን መምራት እንደማይችሉ ሳሙኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ለሳኦል አሳወቀው። "እግዚአብሔር እንደልቡ የሚሆንለትን ሰው አግኝቷል" በማለት ሳሙኤል አወጀለት (1ሳሙ 13:8 -12)።

"ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ደስ የሚለውን ያህል፣ እግዚአብሔር፣ በሚያጠፋ ቁርጣንና መስዋዕት ደስ ይሰዋልን? እነሆ፣ መታዘዝ ከመሥዋዕት፣ ማዳመጥም ከአውራ በግ ሥብ ይበልጣል። ዐመፅ እንደ ጥንቁላ ያለ ኃጢአት፣ እልከኝነትም እንደ ጣዖት አምልኮ ያለ ክፉ ነገር ነው፣ አንተ የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ናቅህ፣ እርሱም ንጉሥ አንዳትሆን ንቆሃል።" በማለት ቁርጠኑን ነገረው (1ሳሙ 15:22-23)።

(8). ሳኦል በንጉሥነት እንዳይቆይ የተደረገበት ዋነኛ ምክንያት
ሀ. እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ መታዘዝ አስፈላጊ አልመሰለውም።

ለ. የያዛትን የአንዲትን ከተማ ንጉሥ ባለመግደሉ።
ሐ. የሚታጠል መስዋዕት ለእግዚአብሔር በማቀረቡ።

ሳኦልም በቀረው ዘመኑ እግዚአብሔርን መፀየል አበሳ እንጂ ምንም መልካም ለውጥ አላሳየም። የሳኦል መናቅና መሻር ለሳሙኤል ከፍተኛ ሀዘን ሆነበት። ሆኖም ግን በእግዚአብሔር ፊት ሌላ የተዘጋጀ ሰው ነበር (1ሳሙ 15:35)።

የዳዊት ዝርዝር መግለጫ

ዓላማ 3 በዳዊት ሕይወት ስለተፈጸሙት ዋና ዋና ድርጊቶች ለመግለጽ

ለታላቁ የእስራኤል ንጉሥ ለዳዊት መንገድ የጠረገለት ነቢዩ ሳሙኤል ነበር። ዳዊት የወጣትነት ጊዜውን ያሳለፈው በእረኝነት ሲሆን በመዝሙር ውስጥ የተጻፉትን ብዙ መዝሙሮቹን ለማፍለቅ ምክንያት የሆነው ከእረኝነት ኑሮው ያገኘው ልምምድ ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለንጉሥነት ስለ መረጠው እረኛ ሆኖ አልቀረም።

ለንጉሥነት መቀባት
1ሳሙ. 16:1-13 አንብብ

እግዚአብሔር ሳሙኤልን ለሳኦል ከሚያለቅስበት ሥፍራ በመቀስቀስ ወደ ቤተልሔም ወደ እሴይ ቤተሰብ ዘንድ ላከው።

(9). 1ሳሙ 9:2፣10:23 እና 16:1-13 ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ መልስ።
ሀ. ሳኦልና ኤሊያብ የሚመሳሰሉበት ነገር ምን ነበር?
ለ. ኤሊያብን እግዚአብሔር ለምን ናቀው?
ሐ. የእግዚአብሔር ዳዊትን መምረጥ ስለ ዳዊት የሚያሳየው ነገር ምን ነበር?

ሳሙኤል ዳዊትን ቀባው። ከዚያን ቀን ጀምሮ የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ በኃይል መጣ (1ሳሙ 16:13)።

የእግዚአብሔርን ጊዜ መጠባበቅ
1ሳሙ 16:14-23፣ 17:1-31:13፣ 2ሳሙ 1 አንብብ

ዳዊት በእስራኤል ላይ ከመንገሡ በፊት ብዙ ዓመታት አለፉ። ዳዊት በመጀመሪያ ክፉ መንፈስ ያሰቃየው የነበረውን ሳኦልን በበገና ለማዝናናትና ለማሳረፍ ወደ ቤተ መንግሥት ተወሰደ (1ሳሙ 16:14-23)።

(10). 1ሳሙ 16:14-23 ካነበብህ በኋላ በዚህ ጊዜ ሳኦል የነበረበትን ሁኔታ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ዳዊት ፍልስጤማዊውን ንጉሥ ስመቋቋም ፈታዴኛ በመሆኑ በጌታ ላይ ያለውን እምነቱን አሳወቀ (1ሳሙ 17:20-58)። በንጉሥ ላይ የተቀዳጀውም - ድል በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ ታዋቂነትን እንዲያተርፍ አደረገው። ሆኖም ግን የዳዊት መታወቅ ሳኦልን አስቀናው (1ሳሙ 18:6-9)። ሳኦል ዳዊትን ሰግቶታል ያቀደው ወጥመድ ሁሉ ከሸፈ። ዳዊትም የሳኦልን ልጅ ሚልኮን አገባ፣ ከዚያም ከዮናታን ጋር ወዳጅች ሆኑ።

ዳዊት በውጊያዎቹ ሁሉ እየተሳካለት በሄደ ቁጥር የሳኦል ቅናት እየጨመረ ሄደ። ሳኦል እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር መሆኑን ያውቅ ነበር (1ሳሙ 18:12፣28)። በመጨረሻም የሳኦል የግድያ መከራ ስለበዛበት ዳዊት ሰመነብሰል ተገደደ (1ሳሙ 19:11-17)። ነቢዩ ጋድም በዚህ በችግር ጊዜና በኋላም ከዳዊት ጋር ይተባበር ነበር (1ሳሙ 22:5፣ 2ሳሙ 24:11-25)።

ዳዊት በመጀመሪያ መሸሸግ የሞከረው በእስራኤል ግዛት ውስጥ ነበር። በኋላ ግን ወደ ጌት ንጉሥ ወደ አንኮስ ሸሸ (1ሳሙ 21)። ወደ እስራኤል ግዛትም ሲመለስ በአዶላም ዋሻ መሸገ። በዚያም ብዙ ሴሎች ተከታዮች አገኘ (1ሳሙ 22)። ነቢዩ ሳሙኤል ከሞተና በአርማቴም ከተቀበረ በኋላ ዳዊት ወደ ፋራን ምድረበዳ ሄደ (1ሳሙ 25:1)። በመጨረሻም ከሳኦል የግድያ መከራ ብዙ ጊዜ ስጥቂት ካመለጠ በኋላ ጠቅላላ መኖሪያውን በጺቅላግ አድርጎ ሳኦል እስኪሞት በዚያ ተቀመጠ (1ሳሙ 27)። በእነዚህ የስደትና የመከራ ዓመታት ውስጥ ዳዊት ራሱን ስእግዚአብሔር ፈቃድ ማስገዛትን መረጠ።

(11). 1ሳሙ 24 እና 26 ካነበብክ በኋላ ዳዊት ሳኦልን ስመግደል አንድ እድል ባጋጠመው ጊዜ ስምን ላለመግደል ወሰነ?

ስእግዚአብሔር ባሳየው መታዘዝ ዳዊት ከአንድ ንጉሥ የሚጠበቀውን አርአያነት አሳየ። ሳኦል ግን የዚህ ተቃራኒ ነበር። ይከተሰው የነበረው የአመፅ መንፈስ እስከጥንቆላም አድርሶት ነበር (1ሳሙ 15:23፣ 28:3-25)። የሳኦል የመጨረሻዎቹ ዓመታት በኩባላዩ ንጉሥና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን መንፈሳዊ ውጊያ ያሳያሉ። በመጨረሻም ሙሉ ስሙሉ በተረታበት ሰዓት በጊልቦአ ተራራ ላይ የራሱን ሕይወት በሣ እጁ አጠፋ። ሦስቱ ወንዶች ልጆቹም፣ ዮናታንን ጨምሮ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ባደረጉት ጦርነት ተገደሱ። የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉሥ ታሪክ በዚህ ዓይነት አሳዛኝ ሁኔታ ተፈጸመ። ዳዊት ስሳኦልና ስወዳጁ ስዮናታን ያለቀሰው ልቅሶ በ2 ኛ ሳሙኤል 1 ላይ ተጽፎ እናገኛለን።

በይሁዳ ላይ መንገሥ
2ሳሙ 1-4 አንብብ

ከሳኦል ሞት በኋላ የዳዊትን ንጉሥነት የተቀበሉት የይሁዳ ነገድ ብቻ ነበሩ። እነርሱም በኬብሮን እንገሥና ሰባት ዓመት ያህል ቆዩ። "እሥራኤል" ተብሰው በአጠቃላይ በተጠሩት በቀሩት ነገዶች ላይ የሳኦል

ልጅ ኢያቡስቴ ነገሰ። ሆኖም ግን የዳዊት ቤት እየበረታ የሳኦል ቤት እየደከመ ሄደ (2ሳሙ 3:1)። በእነዚህ ሁሰት መንግሥታት የእርስ በእርስ መጋጨትና የመርዛት ሂደት ኢያቡስቴ በራሱ ሁለት ወታደሮች ተገደሰ፣ ዳዊትም በጠቅላላ እስራኤል ላይ ነገሠ።

በእሥራኤል ላይ መንገሥ
2ሳሙ 5-24፣ 1ነገ 1:1-2:12 አንብብ

ኢያቡስቴ ከሞተ በኋላ ነገዶች ሁሉ ተሰብስበው ዳዊትን በመላው እስራኤልና ይሁዳ ላይ በኬብሮን እንገሥት (2ሳሙ 5:1-5)። ዳዊትም ኢየሩሳሌምን ከኢያቡሳውያን ላይ በመውሰድ ስተባበረው መንግሥት መዲና አደረጋት (2ሳሙ 5)። በዚያም 33 ዓመት ነገሠ።

ዳዊትም ስእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛቱን ቀጠለ። በመጀመሪያ የመስደው የሥራ እርምጃ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ማምጣት ነበር (2ሳሙ 6)። ይህ ታቦት በኤሊ ዘመን በአፈቅ ወርነት በፍልስጥኤማውያን ተማርኮ ነበር። ከዚያም የእግዚአብሔር ፍርድ ስስበዛባቸው ፍልስጥኤማውያን ወደ እስራኤል መለሱት። እስራኤላውያንም ስስረፋ ታቦቱን በቂርያትይአሪም አስቀመጡት። ቂርያትይአሪም ከኢየሩሳሌም 13 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ቢሆንም ታቦቱ በዚያ ለ60 ዓመታት ያህል ቆይቶአል (1ሳሙ 5-7) ይህም በሳሙኤል፣ በሳኦልና በዳዊት ዘመን ነበር።

(12). 2ሳሙ 7:1-29 ካነበብክ በኋላ እውነተኛ የሆነውን መግለጫ ሬዶሱን በመነበብ አመልክት።

ሀ. ስቃል ኪዳኑ ታቦት ቤት እንዳሰራ እግዚአብሔር ዳዊትን ጠየቀው።
ለ. ስቃል ኪዳኑ ታቦት ቤት ስመሥራት ዳዊት ስእግዚአብሔር ቃል ገባ።
ሐ. ከልጆቹ አንዱ ስቃል ኪዳኑ ታቦት ቤት እንደሚሰራ እግዚአብሔር ስዳዊት ነገረው።

በዚህ ጊዜ ነበር እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን ያደረገው። ስዳዊትም የዘላለም መንግሥት ተሰፋ ሰጠው። ዳዊትም የአገሩን ደንበር እያሰፋ ሄደ። ፍልስጥኤማውያንን፣ ሞአባውያንንና አሞናውያንን አሸንፋቸው (2ሳሙ 8-10)።

ዝናው እጅግ በገነነበት ሰዓት ዳዊት ከባድ ኃጢአት ውስጥ ወደቀ። ቤርሳቤህ ከተባለች ሴት ጋር አመነዘረ፣ ባልዋን አርዮንንም በጦርነት ውስጥ እንዲገደል አደረገው (2ኛ ሳሙ 11)። አርዮን ስረጅም ጊዜ የዳዊት ረዳትና የጦር አበጋዝ ነበር። የዳዊትን ኃጢአት ነቢዩ ናታን ገለጠበት፣ የእግዚአብሔርንም ቅጣት አስታወቀው። ከቤርሳቤህ የተወለደው ልጅም ሞተ (2ኛ ሳሙ 12:15-23)። ዳዊት በተሰበረና በተሞረደ ልብ ንስሐ ገብቶ ነበርና እግዚአብሔር ይቅር አለው (መዝ 32ና 51)።

(13). መዝሙር 32 እና 51 ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. ስለ ኃጢአት እግዚአብሔር በመቀሰው ጊዜ ዳዊት የሰጠው ምላሽ እንዴት ነበር?
ለ. በኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር ወቅሶህ ያውቃል? የሰጠኸው መልስ እንዴት ነበር?

እግዚአብሔር ፍጹም የሆነ ይቅርታውን ለዳዊት ለማጸናት ከዘርሳቤህ ሊላ ልጅ ሰጠው፣ ይህም ልጅ ሰለሞን ነበር። ሰለሞን የሚቀጥለው የእስራኤል ንጉሥ ሆነ (2ሳሙ 12:24-25፣ 1ነገ 1:39-40)።

ዳዊት ንስሐ ቢገባም ቅሰ የኃጢአቱ ውጤት በቤተሰቡ ውስጥ መታየት ጀመረ። ከተለያዩ ሚስቶች በወለዳቸው ልጆቹ መካከል ጠብ ተፈጠረ (2ሳሙ 13-14)። ዳዊት ከዙፋኑ እስኪለቅ ድረስ የገዛ ልጁ አቤሴሎም አመጸበት (2ሳሙ 15-18)። በኋም ወደ ዙፋኑ ተመለሰ (2ሳሙ 19-20)። ለእግዚአብሔር ምስጋናና ክብር ሰጠ (2ሳሙ 22-23)።

ዳዊት የሕዝብ ቆጠራ በማድረግ ዳግመኛ ኃጢአት ሠራ። ይህም እምነቱን ከእግዚአብሔር ይልቅ በሰራዊቱ ላይ በማድረጉ ነበር። በዚህም መቅሰፍት በእስራኤል ላይ መጣ። ዳዊትም ንስሐ ገብቶ ወደ እግዚአብሔር ማለደ። በእርናም አውድማ መሰዊያ ሠርቶ ሰዋ። መቅሰፍቱም ተከለከለ (2ሳሙ 24:10-25)።

ዳዊት ወደ ሕይወቱ መጨረሻ ሲደርስ ከልጆቹ አንዱ አዶንያስ የተባለው ዙፋኑን ለመያዝ ሞከረ። ከመያዝ ተከልክሎ በእርሱ ፋንታ ለሰለሞን ተሰጠና ሰሎሞን ንጉሥ ሆነ። ዳዊት ሞተ፣ ተቀበረ (1ነገ 1:1-2:12)። የእስራኤል ታሪክ እንደሚያሳየው ሊሎቹ ነገሥታት የሚነጻጸሩት በዳዊት ለእግዚአብሔር ተገዢነት አንጻር እንደነበረ እንመለከታለን።

(14). ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በማስቀመጥ እብሮ የሚሄደውን አመልክት።
1. ለንጉሥነት ተቀባ
2. የእግዚአብሔርን ጊዜ መጠበቅ
3. የይሁዳ ንጉሥ ሆነ
4. የመላው እስራኤል ንጉሥ ሆነ

___ሀ. በኬብሮን አነገሡት።
___ለ. ሳኦልን ለመግደል እንቢ አለ።
___ሐ. የታቦት ኪዳኑን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም አመጣ።
___መ. ለሳኦል መዝሙር እንዲዘምር ወደ ቤተ መንግሥት መጣ።
___ሠ. እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ታል ኪዳኑን አደረገ።
___ረ. ንጉሥ እንዲሆን ሳሙኤል ቀባው።
___ሰ. በጎልያድ ላይ ድል ተቀዳጀ።
___ሸ. የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ ተገደለ።
___ቀ. ልጁ አቤሴሎም አመጸበት።

የሰለሞን ዘመነ መንግሥት

1ነገ 2:13-11:43 አንብብ

ዓላማ 4 ለሰሎሞን መንግሥት መሳካትና ውድቀት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ለይቶ ለማወቅ

መታዘዝና መሳካት

የሰለሞን ዘመን የእስራኤል መንግሥት ገናናነት በዓለም ሁሉ የተደነቀበት ጊዜ ነበር። ሰለሞን ከጅማሬውም ታላቅ ሆኖ ለ40 ዓመት ነገሠ (1ነገ 11:42)።

እግዚአብሔር በተገለጠለትና ምን እንደሚፈልግ በጠየቀው ጊዜ የሰለሞን ልመና የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያስተዳበት ጥበብ ማግኘት ነበር። ይህም ልመና እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው (1ነገ 11:42)። ሰለሞን በተበበኛነቱ የታወቀ ሆነ። በእግዚአብሔር ላይ እምነትና ፍቅር ነበረው (1ነገ 3:3፣ 28፣ 4:29-34)።

በሰለሞን ዘመን ብዙ መንፈሳዊ መዝሙራትና ጽሑፎች ተደርሰዋል። ሰለሞን ብቻውን 3000 ምሳሌዎችን የጻፈ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 375 ያህሉ በብሉይ ኪዳናችን ሰፍረዋል። ወደ 1005 የሚሆኑ መዝሙራትም ደርሰ ሦስቱ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ተጠቅሰዋል። እነዚህም መዝሙር 75፣ 117ና መኃልየ መኃልይ ናቸው።

ስለ ሰለሞን መንግሥት ከተጻፉት 11 ምዕራፎች ውስጥ አራቱ ያሚናገሩት ስለ መቅደሱ ሕንጻ አሠራር ነው (1ነገ 5-8)። ቤተ መቅደሱ ውብም፣ ውድም ነበር። በአሁኑ ዘመን ምንዛሪ ቢተመን ቤተ መቅደሱ የፈጀው 40 ቢሊዮን ብር እንደሚሆን ይገመታል። ለመቅደሱ ሥራ የዋለው የሰው ኃይል 30 ሺህ ያህል እይሁዶችና ከ153 ሺህ በላይ የሚሆኑ ከነዓናውያን ነበሩ።

(15). ስለ መቅደሱ የተሰጠውን መግለጫ ከ1ነገ 5-8 ላይ ካነበብህ በኋላ በአራተኛው ክፍለ ትምህርት ከተጠቀሰው ከማይሪያው ድንኳን ጋር የሚመሳሰለባትን ሦስት መንገዶች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፍ። ልዩ የሆኑበትንም አንድ ዋና መንገድ ግለጽ።

(16). ሰለሞን መቅደሱን ሰርቶ ካስመረቀ በኋላ እግዚአብሔር እንደገና ለእርሱ ተገለጠለት። 1ነገ 9:1-9 ካነበብህ በኋላ ሰለሞንና ዘሮቹ ማየት ይገመልኩ መቅደሱ ምን እንደሚሆን እግዚአብሔር የተናገረውን በማስታወሻ ደብተርህ ላይ በራስህ ቃላት ግለጽ።

ሰለሞን በነገሰባቸው ዓመታት በእስራኤል ላይ ይታይ የነበረው ክብር እግዚአብሔር የታል ኪዳን ሕዝቡን ለመባረክ ያለውን ዓላማ የሚገልጥ ነበር። በ1ነገ 10:14-29 ላይ የተሰጠው ገለጻ ግእስራኤልን መንግሥት ታላቅነት ያመለክታል። የእግዚአብሔር ክብር በእነርሱ ላይ የሚገለጥባቸው ሰለሆኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለዓለም አሰደናቂ ሕዝብ ነበሩ።

አለመታዘዝና ውድቀት

ሰለሞን ነገሮች በሚያሰደንቅ ሁኔታ እየተሳኩለት ቢሄዱም ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ከመሆን ተቆጠበ። መንግሥቱ በሃብትና በዝና ገነነ። ከውጭ መንግሥታት ጋር ግንኙነትን ፈጠረ። በእግዚአብሔር ቃል የተከለከለውን ነገር፣ ግሚስቶችን ከእሰራኤል ውጭ አገባ (ዘዳ 17:17)። የሰለሞን ሚሰቶችም ከአባቱ ከዳዊት እምላክ አራቁት (1ነገ 11:1-8)። ሰለሞን ሌሎች ባዕድ አማልክትን አመለከ፣ ባለመታዘዙ ምክንያት የእግዚአብሔር ፍርድ መጣበት።

(17). 1ነገ 11:9-11 ካነበብህ በኋላ ትክክለኛ የሆነውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. እግዚአብሔር ለዳዊትና ለኢየሩሳሌም ሲል ለሰሎሞን ልጅ ሁሰት ነገዶች እንደሚተው ተናገረ።
ለ. ልጁ በሚነግሥበት ጊዜ የሰሎሞን መንግሥት ከእርሱ ይወሰዳል።
ሐ. ሰሎሞን የተፈረደበት ብዙ ሃብት ሰለነበረው ነው።

(18). ስሰ ስለሞን መንገሥ የሚናገረውን ክፍል ደግመህ ከታኘህ በኋላ 1ነገ 3:3 እና 11:1-2 አንብብ። ከሚከተሉት መግለጫዎች ለስለሞን ነገሮች እንዲሳኩለትና ከዚያም እንዲነግሥ ምክንያት የሆኑትን በተሻለ መን ገድ የሚገልጸው የትኛው እንደሆነ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. ሰለሞን ብልጽግናና ሃብት እያተረፈ ሲሄድ ነገሮች የተሳኩለት ሰው ሆነ። በኋላ ግን ከጌታ እንዲርቅ ያደረጉት እነዚሁ በረከቶች ነበሩ።
ለ. የንጉሥ ዳዊት ልጅ እንደመሆኑ ሰሎሞን ታላቅና ዘለቂታ ላለው በረከት ተሰፋ ተሰጥቶት ነበር። ነገር ግን ለጥበብ የነበረው ፍላጎት በጣም ኃይለኛ ሰለነበር ሊወድቅ ቻለ።
ሐ. በንግስት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ሰሎሞን እግዚአብሔርን በመውደ ድ ለእርሱ ታዘዘ። በኋላ ግን ብዙ የውጪ ሚስቶችን በማግባት የእነርሱን አማልክት ማምለክ ጀመረ።

ሰለሞን እንደጎረቤት አገሮች መሪዎች አምባገነን መሆን ጀመረ። ከሞተ በኋላም ግናና መንግሥቱ እየደከመ መጣ። ክርሰቶስ ሲመጸ ሲዋረድ የመጣው ከዳዊት ልጅ ከናታን እንጂ ከሰለሞን አልነበረም (2ሳሙ 5:15፣ ሉቃ 3:3)። ይሁን እንጂ የመንግሥቱ ክብርና ብልጽግና እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊሰጥ የሚፈልገውን የተትረፈረፉ በረከቶች ምሳሌ ናቸው።

የመከራ ፈተና

ከሚከተሉት ውስጥ ንጉሥነትን በተመለከተ እግዚአብሔር የሰጠውን መመሪያዎችና ማስጠንቀቂያዎች በተሻለ መንገድ የሚያጠቃልለው የትኛው ነው?

1. ሀ. መመሪያዎቹ የንጉሱ ዋና ተግባር የሕዝቡ መንፈሳዊ መሪ እንዲሆን ነበር። ማስጠንቀቂያው በርከት ያሉ ካህናትን ወደ ቤተሰቡ ካላመጣ ሕዝቡን ሊያሰተዳር እንደማይችል ነበር።

   ለ. መመሪያዎቹ ንጉሡ ለእግዚአብሔር ሕግ በሩጹም መታዘዝ እንደነበረበትና ይህን ከማድረግ ምንም ነገር እንዲያግደው መፍቀድ የለበትም። ማስጠንቀቂያው ንጉሡ የራሱን ቤት ለመገንባት ከሕዝቡ እንደሚወስድና ሕዝቡም በመጣረር እንደሚያትረመርም ነበር።

   ሐ. መመሪያዎቹ ንጉሡ መቅደስ የመሥራቱን ኃላፊነት እንዲወሰድና ለእስራኤል ጥበቃ በዛ ያለ ሠራዊት እንዲሰበሰብ ሲሆን፣ ማስጠንቀ ቂያው ንጉሡ ኃይለኛ ሠራዊት ከሌለው መንግሥቱ እንደሚወሰድበት ነበር።

2. የሚከተሉትን ሰዎች ከሚመስላቸው ሥራዎቻቸው ጋር አገናዝብ።

   1) ሳኦል 2) ዳዊት 3) ሰለሞን

___ሀ. የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ያስመለሰ።
___ለ. ከእርሱ በኋላ ንጉሥ የሆነውን ሰው ለመግደል የሞከረ።
___ሐ. በጥበብ የታወቀ።
___መ. የእስራኤልን የመጀመሪያ ንጉሥ እንዳይሞት ያደረገ።
___ሠ. መቅደሱን የሠራ።
___ረ. ብዙ የውጭ ሚስቶች ያገባ።
___ሰ. እግዚአብሔር በኃጢአቱ በወሳሰው ጊዜ ምላሽ በመስጠቱ ሁለት መዝሙር የጻፈ።
___ሸ. ወደ ጥንቆላ የተመለሰ።

3. እግዚአብሔር ንስሐ የሚገባን ሰው ይቅር በማለት እንደገና እንደሚጠቀ ምበት ለሰዎች ለማሰተማር ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የየትኛው ንጉሥ ታሪክ ነው?
   ሀ) ሳኦል ለ) ዳዊት ሐ) ሰለሞን

4. ከዚህ በታች የቀረቡትን አሥር ድርጊቶች በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ቁጥር በመሰጠት በቅደም ተከተል አሰቀምጥ። መጀመሪያ ለተፈጸመው ድርጊት 1፣ ከዚያም 2፣ እያልክ እስከ 10 በመጻፍ አመልክት።

___ሀ. ሳኦል ለንጉሥነት ተቀባ።
___ለ. በቤተልሔም ዳዊት ተቀባ።
___ሐ. ሰለሞን ተወለደ።
___መ. ሕዝቡ ንጉሥ እንዲሰጣቸው ሳሙኤልን ጠየቁ።
___ሠ. ሳኦል ከንጉሥነቱ ወረደ።
___ረ. ዳዊት ያብዳንና ሐብርንን ገባ።
___ሰ. ዳዊት አርና አውድማ ላይ መሠዊያ ሠራ።
___ሸ. ሰሎሞን ለጌታ ቤተ መቅደስ ሠራ።
___ቀ. አቤሰሎም ዳዊትን ለጊዜው ከዙፋኑ አባረረ።
___በ. ዳዊት የኢየሩሳሌም ከተማን በመውሰድ የመላው እስራኤል ንጉሥ ሆነ።

5. በተሰጠው ስፍራ ቁጥሩን በማስቀመጥ ከመግለጫው ጋር አብር የሚሄደውን አመልክት።
   1) ሳሙኤል 2) ዳዊት 3) ሳኦል 4) ሰለሞን

___ሀ. የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማስተዳደር ጥበብ እንዲሰጠው ያቀረበው ጥያቄ ጌታን አስደሰተው።
___ለ. የእግዚአብሔርን መንፈስ ምሪት መከተል እንዳለበት ቢያውቅም ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ ምክንያት ከንጉሥነቱ ወረደ።
___ሐ. ንጪአት ቢሠሩም ለእስራኤል መጪለዩን በታማኝነት ቀጠለ።
___መ. በውጭ ሚስቶቹ በመሳብ ከጌታ ርቆ ሌሎች አማልክትን አመለከ።
___ሠ. ንጉሥ እንዲሆን የተቀባ ቢሆንም ንጉሥ እስኪሆን ድረስ ለብዙ ዓመታት የእግዚአብሔርን ጊዜ ጠበቀ።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

10. ባለመታዘዙ ምክንያት ሳኦል የተጨነቀና መንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ የገባ ይመስላል። ነገ የሚሆንበት ጊዜና ከዚህ ሁኔታው የሚላቀቅበት ጊዜ ዳዊት በገናውን ሲጫወትለት ብቻ ነበር። (መልስህ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይገባል)።

1. ሀ. የእግዚአብሔር ምርጫ እስራኤላዊ ሰው መሆን ነበረበት።

   ለ. የእግዚአብሔር ሕግ ቅጂ ሊራሱ እንዲኖረው ያስፈልግ ነበር። ይህንንም ሕግ በአቅራቢያው አድርጎ ሊያነበው፣ ሊታዘዘው ይገባ ነበር። እንደሊሎቹ እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ተገዢ መሆኑን መገንዘብ ነበረበት።

   ሐ. ብዙ ፈረሶች እንዲኖረው ወይም ከግብጽ እንዲገዛ አያስፈልገውም ነበር። ብዙ ሚስቶች እንዲኖረው ወይም ራሱን ሃብታም ማድረግ

   አያስፈልገውም ነበር። ኑሮውን ከሕዝቡ የተሻለ አድርጎ ማየት የለበትም።

11. ምክንያቱም ሳኦልን በእግዚአብሔር እንደተመረጠና ለንጉሥነት እንደተቀባ አድርጎ ስለአከበረው ነው።

2. ንጉሥ እንዲኖራቸው በመጠየቃቸው ራሳቸውን ከእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ማድረግ ትተው ከሰው ሥልጣን ሥር አደረጉ።

12. ሀ. ሐሰት ለ. ሐሰት ሐ. እውነት

3. ሀ. ዋና ግዴታው ሕጉን ማወቅና መታዘዝ ነው። ይህን ካደረገ የዚህ ውጤት ለእርሱና ለዘሩ ለብዙ ዘመናት መንገሥ ይሆናል።
   ለ. ቤተ መንግሥቱን ለመሥራትና ሠራዊቱን ለማጠናከር ከሕዝቡ ይወስዳል። በዚህ ምክንያት ሕዝቡ ይመረራል፣ እግዚአብሔር ግን አይሰማቸውም።

13. ሀ. ንጪአቱን በመናዘዝ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው ለመነ። ራሱን በማዋረድ ንስሐ ገባ።
   ለ. የአንተ መልስ። የዳዊት ምላሽ እግዚአብሔር ስለ ንጪአት ሲወቅሰን ምን ማድረግ እንዳለብን ያስተምረናል።

4. ስለ እነርሱ መጪለዩን እንደሚቀጥልና ትክክለኛ የሆነውን ነገር እንደ ሚያስተምራቸው።

14. ሀ. 3 ረ. 1
   ለ. 2 ሰ. 2
   ሐ. 4 ሸ. 3
   መ. 2 ቀ. 4
   ሠ. 4

5. የአንተ መልስ።

15. መልስህ ከዚህ በታች ያሉትን ያካተተ መሆን አለበት።

   ሀ. ሁለቱም የታል ኪዳን ታቦቱ የሚቀመጥበት የውስጥ ክፍል ነበራቸው።
   ለ. ሁለቱም የመስዋዕት መስዊያ ነበራቸው።
   ሐ. ሁለቱም የእግዚአብሔር መገኘት በመካከላቸው ነበር። በሁለቱ መካከል የነበረው ልዩነት ድንኳኒ ተንቀሳቃሽ በመሆኑ እስራኤላውያን በምድረበዳ በሚጓዝበት ወቅት ከዚያ በታ ያዘዋወሩት ነበር። መቅደሱ ግን ተንቀሳቃሽ አልነበረም። ነገር ግን ምድራቸውን ለወረሱት እስራኤላውያን ቋሚ የአምልኮ ማዕከል በመሆን ያገለግል ነበር።

6. እግዚአብሔር አዲስ ባሕርይ ሰጠው።

16. በቁጥር 7-8 ላይ በተጻፈው መሰረት እግዚአብሔር መቅደሱን ሲተው የፍልፈል ማከማቻ ይሆናል።

7. ሀ. 1ሳሙ 11:1-15 - አሞናውያንን አሸንፋቸው።
ለ. 1ሳሙ 13:8-13 - እንደካዘን በመሆንና መስዋዕት በማቅረብ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አፈረሰ።
ሐ. 1ሳሙ 14:1-23- ፍልስጤማውያንን በማሸነፍ የያዜጽን ከተማ አዳነ።
መ. 1ሳሙ 15:1-7 - አማሌቃውያንን ከኤላውጥ እስከ ሱር በምታት አሸነፋቸው።
ሠ. 1ሳሙ 15:8-23 - አማሌቃውያንን ፈጽሞ እንዲያጠፋ የተነገረውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አፈረሰ።

17. ሐ. ሐሰት ለ. እውነት ሐ. ሐሰት

8. ሀ. እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ መታዘዝ አስፈላጊ አልመሰለውም። እውነተኛው ምክንያት ያህ ነው። በ"ለ" ና በ"ሐ" ላይ የሰጠው ያለመታዘዝ የመሳው የጌታን ፈቃድና ትእዛዝ ካለማክበር እዝማሚያ የመጣ ነበር።

18. ሐ

9. ሀ. ሁለቱም መልክ ቀናዎች ነበሩ።
ለ. እግዚአብሔር ልቡን ስላየ ተቀባይነት አላገኘም።
ሐ. የእግዚአብሔር ምርጫ ያመለከተው የዳዊት ልብ ከእግዚአብሔር ጋር የተስተካከለ እንደ ነበር ነው።

7

ትምህርት

የነገሥታት ዘመን ሥነ-ጽሑፍ

በስድስተኛው ክፍለ ትምህርት ሳኦል የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ እንዴት እንደተመረጠና ከእርሱ ቀጥሎም ዳዊትና ሰለሞን በተከታታይ በእስራኤል ላይ እንደነገሡ ተመልክተናል።

በዚህ ክፍለ ትምህርት ደግሞ በእስራኤል ዘመነ መንግሥት አስገራሚ የሆኑ የቅኔና የጥበብ መጻሕፍት የአጻጻፍ መሠረታዊ ስልቶችን በአጭሩ በመዳሰስ የእያንዳንዳን መጽሐፍ ፍሬ ሃሳብና የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት እንመለከታለን።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የግጥምና የጥበብ መጻሕፍት ተብለው የሚጠሩ አምስት ጽሑፎች አሉ። እነርሱም ኢዮብ፣ መዝሙር፣ ምሳሌ፣ መክብብና መኃልየ መኃልይ ናቸው። እነዚህ እንዳለፉት መጻሕፍት ታሪካዊ ይዘት ያላቸው ሳይሆኑ ስለ እስራኤላውያን የዕለት ተዕለት የኑሮ ልምምድ የሚያወሱ ናቸው። በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ የተጠቀሱት ችግሮች፣ ልምዶች፣ አስተሳሰቦችና ስሜቶች ስለ እስራኤላውያን የኑሮ ዘይ እንዳንድ ነገር ይጠቁመናል።

ከእነዚህ መጻሕፍት አብዛኞቹ በንጉሣት ዘመን የተጻፉ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ከዚያ ቀደም ብለው የተጻፉ እንደሆኑ ይገመታል። ነገር ግን ሁሉም በታሪክ ውስጥ የነበሙ ልጅ የሚተመሙን የጋራ የሆነ ውሳ ውረድ ስለሚያስተምሩ ለዘመናት ሁሉ ጥቅም አላቸው። እነዚህ መጻሕፍት ዛሬም ለኛ መንፈሳዊ እድገት የሚሆን መልእክት ያዘሉ በመሆናቸው የእግዚአ ብሔር መንፈስ እንዲረዳን በጸሎት መንፈስ ሆነን ልናጠናቸው ይገባል።

የክፍለ ትምህርቱ አስፋፈል

- ጽሑፎችና ዓይነታቸው
- የጥበብ ጽሑፎች
- የአምልኮ ጽሑፎች

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- በጥበብና በቅኔ መጻሕፍት ውስጥ ያለውን መሠረታዊ የአጻጻፍ ዘይ መግለጽ።
- የእያንዳንዱን የቅኔና የጥበብ መጻሕፍት ፍሬ ሃሳብና መንፈሳዊ መልእክት መግለጽ።
- በግል የአምልኮና የጸሎት ጊዜህ በቅኔና በጥበብ መጻሕፍት በመጠቀም፣ ያዘሉትን መልእክቶች ከሕይወትህ ጋር ማዛመድ።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1 በክፍለ ትምህርቱ ላይ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች በጥንቃቄ አንብብ።

2. ትምህርቱን በሚገባ ተከታትለህ ስትጨርስ የመክሯ ፈተናውን በመውሰድና መልሶችህን በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ከሰፈሩት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸውን አስተካክል።

የትምህርቱ ዝርዝር

ጽሑፎችና ዓይነታቸው

ዓላማ 1 አምስቱን የጥበብና የቅኔ ጽሑፎች ለመዋቀስ።

በዚህ ትምህርት የምናጠናቸው መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ዘንድ ተወዳጅነት ያላቸው ናቸው። ከጸሐፊዎቹ መካከል በሙያቸው ነገሥታት፣ ነቢያት፣ ባለቅኔዎችና ተራ ሰዎች ይገኙበታል። ምንም እንኳን እነዚህ ጽሑፎች ከተጻፉበት ዘመንና ባህል ርቀን ብንኖርም በውስጣቸው የሰፈሩት መሠረታዊ ትምህርቶች አሁንም ጠቃሚነትና ተፈላጊነት አላቸው። እግዚአብሔር ለዕለት ተዕለት አኗኗራችን ምን ያህል እንደሚያ ስብ ከእነዚህ መጻሕፍት ለመረዳት እንችላለን። ስለ መከራችን፣ ሥራችን፣ ቤተሰባችንና አምልኮአችን ሁሉ የሚገደው አምላክ እንደሆነ እንገነዘባለን።

(1). አምስቱ የጥበብና የግጥም መጻሕፍት የትኞቹ ናቸው?

1. _____
2. _____
3. _____
4. _____
5. _____

(2). ከኢዮብ በፊት ያለው መጽሐፍ _____ ነው። ከመኃልየ መኃልይ ቀጥሎ ያለው መጽሐፍ _____ ነው።

የጽሑፎቹ ቅርጽ

ዓላማ 2 መሠረታዊ የግጥም አጻጻፍ ስልቶችንና ምሳሌዎችን በቅኔና በጥበብ መጻሕፍት ውስጥ ለይቶ ማወቅ።

የግጥምና የጥበብ መጻሕፍት የተጻፉት ትይዩ በሆኑ ለንኖች የግጥምና የቅኔ አጻጻፍ ዘይ ነው። ይህም የዕብራይስጥ የግጥም አጻጻፍ ዋና ስልት ነው። የትይዩ ለንኖች ስልት ማለትም በሰንኖቹ መካከል ያለው ሃሳብ ይመሳሰላል ወይም ሚዛናዊነት አለው ማለት ነው። ይህም ስልት ቤትን ከሚመታ የግጥም አጻጻፍ የተለየ ነው። ቤት መምታት የሚባለው የለንኞች የመጨረሻ ቃላት ተመሳሳይ ድምፅ ሲኖራቸው ነው።

1. ቤት የሚመታ ቅኔ፦ በመስቀል ሞተ መድሃኒቴ
ሊያድነኝ ብሎ ከኃጢአቴ

2. ትይዩነት፦ ምንሮችን ወደ ቆላዎች ይልካል
በተራሮች መካከል ውሆች ያልፋሉ
(መዝ 104፡ 10)

የዕብራይስጥ ቅኔ ውበት ያለው ሲሆን፣ ይዘንንም ውበት የሚሰጡት በውስጡ የተገለጸት አሳቦች ናቸው። የሚያስደንቀው ደግሞ በሚተረጉምበት ጊዜ እንኳ የቅኔው ውበት አይጠፋም።

ሦስት ዓይነት ትይዩነት አለ።

1. <u>ተደጋጋሚ</u>፡ ሁለተኛው ስንኝ የመጀመሪያውን ስንኝ ሃሳብ በለላ ቃላት ሲደግም ነው (መዝ 85:7)።
2. <u>አጠናካሪ</u>፡ ሁለተኛው ስንኝ በመጀመሪያው ስንኝ ላይ በተመሳሳይ ርዕስ ተጨማሪ ሃሳብ ሲያክል ነው (መዝ 85:6)።
3. <u>ተቃራኒ</u>፡ ሁለተኛው ስንኝ ከመጀመሪያው ስንኝ ተቃራኒ ትርጉም ያለው ሃሳብ ሲያቀርብ ነው (ምሳ 15:28)።

እነዚህን የግጥምና የጥበብ መጻሕፍት ስናነብ ይህን የግጥም ስልት ማጤን ይጠቅመናል። የጥበብና የቅኔ መጻሕፍትን እያጠናህ ስትሄድ እነዚህን ሦስት ዓይነት ትይዩ ስንኞች ለመረዳት ሞክር።

(3). በተሰጠው ሰፍራ ቁጥሩን በማስፈር አብሮ የሚሄደውን አመልክት።

1. ቤት የሚመታ
2. ተደጋጋሚ
3. አጠናካሪ
4. ተቃራኒ

___ሀ. ብርሃንህንና እውነትህን ላክ
እነርሱ ይምሩኝ፣
___ለ. በመስቀል ሞተ መድኃኒቴ
ሊያንኝ ብሎ ከንጠኢቱ
___ሐ. እግዚአብሔር የጻድቃንን መንገድ ይጠብቃልና
የክፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች።
___መ. ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ
የሰማያም ጠፈር የእጁን ሥራ ያውጃል።
___ሠ. የሚወደውን ሁሉ ይንከባከባል
ንጠኢተኛን ግን ያጠፋል

የግጥበብ ጽሑፎች

መጽሐፈ ኢዮብ - ስለመከራ የተሰጠ መልስ
ኢዮብ 1-15፣ 28-35፣ 38-42 አንብብ

ዓላማ 3 መጽሐፈ ኢዮብ የሚሰጠውን ዋና ትምህርት ለመግለጽ።

ኢዮብ በአብርሃምና በሙሴ መካከል በነበረው በአባቶች ዘመን እንደኖረ ይታመናል። በትንቢተ ሕዝቅኤል ውስጥ ከኖህና ከዳንኤል ጋር አብሮ ተጠቅሶአል (ሕዝ 14:14፣20)። ይህ መጽሐፍ ከሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ይልቅ ጥንታዊነት አለው። የመጽሐፉ ርዕሰ ነገርም እስካሁን መሳትሔ ስላልተገኘለትና ዓለም ዓቀፋዊ ችግር ስለሆነው ስለሰው ልጅ መከራ የሚነገር ነው።

የመጽሐፉ መከፈቻ ፈተና ሲሆን፣ ይህም በኢዮብ 23:10 ላይ ተጠቅሶ እናገኛለን። የመጽሐፉ አከፋፈል እንደሚከተለው ነው።

1. ኢዮብ 1:1-3:26 - ኢዮብንና ሦስቱ ባልንጀሮቹን ያስተዋውቀናል
ኢዮብ የሚገኘው በክፍሉ ደህንትና ቁስል ውስጥ ነው።
2. ኢዮብ 4:1-31:40 - ኢዮብና ሦስቱ ባልንጀሮቹ ተራ በተራ ንግግር
ያለዋወጣሉ። ስለ መከራውም ይወያያሉ።
3. ኢዮብ 32:1-37:24 - ኤሊሁ ይናገራል። መከራ የማንጻትና የቅጣት
መግሪያና መንገድ ነው ይላል።
4. ኢዮብ 38:1-41:34 - እግዚአብሔር ይናገራል። አሳቡ ከሰው ሃሳብ በላይ
ስለሆኑ ሰው የፈጣሪውን መንገዶች ሙሉ በሙሉ
መረዳት አይችልም።
5. ኢዮብ 42:1-7 - ኢዮብ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል። የጠፋው ንብረቱም
እጥፍ ሆኖ ተመለሰለት።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ መከራ የተጠቀሱትን አራት አመለካከቶች እንማራለን። እነዚህም የሰይጣን፣ የጻድቅ ሰው፣ በሥቃይ ውስጥ ያሉና የአዳኙ አመለካከቶች ናቸው።

1. የሰይጣን አስተያየት፡- ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩት ስለሚያስገኘው የባለጠግነትና የክብር ጥቅም ሲሉ ነው (ኢዮብ 1:1-2፣8)። ኢየሱስን በፈተነበት ሰዓትም ሰይጣን ይህን ፍልስፍናውን ተጠቅሞአል (ማቴ 4:1- 11)።

2. የጓደኞች (የጻድቃን) አስተያየት፡- የኢዮብ ባልንጀሮች የኤልፋዝ፣ የበልዳዶስና የሶፋር አስተያየት ተመሳሳይ ሲሆን፣ ይህም ጽድቅን የሚያደርጉ ሁልጊዜ ሲባረኩ ንጠኢትን የሚያደርጉ ደግሞ ሁልጊዜ ይሰቃያሉ የሚል ነው። ስለዚህም ኢዮብ ብዙ ሥቃይ መቀበሉ የሚያሳየው ከባድ ንጠኢተኛ መሆኑን ነው ብለው ይመደመዳሉ (ኢዮብ 4:7)።

3. የሚሰቃዩ አስተያየት፡- (የኤሊሁ አስተያየት) መከራ እኛን ወደ መንገዱና ሃሳቡ ለመመለስ እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚጠቀምበት የአባትነት ቅጣት ነው። የኤሊሁ ንግግር በብዛት ለእግዚአብሔር መሟገት ነው።

4. የአዳኝ አስተያየት፡- እግዚአብሔር ራሱን ለኢዮብ ገለጠ። ጻድቃን መከራ የሚቀበሉበት ምክንያት ራሳቸውን ማየት እንዲችሉ ነው። ኢዮብ መልካም ሰው ሆኖ ሳለ በጻድቅነቱ ይመካና ይመጻደቅ ነበር።

የኢዮብ መጽሐፍ የሚያሳየን መከራና ፈተና የሚመጣው ሁልጊዜ ለቅጣት አለመሆኑን ነው። አንዳንድ ጊዜ ወደ ሕይወታችን እንዲመጡ የሚፈቀዱላቸው እኛን ለማስተማርና ለማበልጠን ነው። ለምሳሌ አንድ እስፖርተኛ ጥብቅ በሆነ ልምምድና ሥልጠና ውስጥ የሚለፋው ለቅጣት ተብሎ አይደለም። ሥልጠናው ሩጫውን በሚገባ እንዲሮጥ ያደርገዋል። በተመሳሳይ መንገድም እግዚአብሔር እያንዳንዳችን ልንፈጽም ለሚገባን ሥራ ብቁዎች እንድንሆን በመከራና በፈተና ውስጥ ዘግሳለፍ ሊያሰለጥነን ይችላል። በምናልፍበት መከራ ሁሉ የእግዚአብሔር ጥበብና ዓላማ አለበት፣ እርሱም ጥበቡን ሊያሳየን ይፈልጋል።

(4). "የአዳኝ አስተያየት" ያለው ሰው የሚናገረው ሐሳብ መከራ በንቀበል፦

ሀ. እግዚአብሔርን በማገልገል መቀጠል የሚገባን መሆኑን ራሳችንን መጠየቅ ያስፈልጋል።
ለ. ያለመታዘዛችን ውጤት መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል።
ሐ. ራሳችንን ለማወቅና እግዚአብሔርንም በአዲስ መንገድ ለመረዳት መዘጋጀት አለብን።

(5). የኢዮብ መጽሐፍ የሚሰጠውን ዋና ትምህርት በተሻለ መንገድ የሚገልጠው የትኛው መግለጫ ነው?

ሀ. ሰው የእግዚአብሔርን መንገድ ሊረዳ ስለማይችል የደረሰበትን መከራ ሁሉ እንደቅጣት አድርጎ መቀበል አለበት።
ለ. ስቃይ ዘወትር የኃጢአት ውጤት አይደለም። በስቃይ ውስጥ የሚያልፉ የእግዚአብሔር ሰዎች ግን ራሳቸውን ዝቅ በማድረግና እርሱን በማምለክ ምላሽ መስጠት አለባቸው።
ሐ. እግዚአብሔርን በታማኝነት የሚያገለግሉ ሰዎች መከራ እንዲቀበሉ እግዚአብሔር ስለማይፈቅድ ፈተናና መከራ አይደርስባቸውም።

መጽሐፈ ምሳሌ - የአናኒር መመሪያዎች

ምሳ 1-10፣ 13-16፣ 29-31 አንብብ

ዓላማ 4 የመጽሐፈ ምሳሌን ይዘት ለመግለጽ።

መጽሐፈ ምሳሌ አስገራሚ የሆኑ የጠቢባን አነጋገር ጥርቅም ነው። አይሁዶች ከመቅደሱ የውጭ አደባባይ ጋር ያመሳስሉታል። ምክንያቱም አይሁዶች ከሌላው ሰው ጋር የሚገናኙት በዚያ አደባባይ ለለሆነ ነው። መንፈሳዊነት በተግባር ሲተረጎም ምን እንደሚመስል የሚያሳየን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ነው። በሕይወታችን ውስጥ በተለያየ አቅጣጫ ያለን ግንኙነት ተጠቅሰውበታል። ለእግዚአብሔር፣ ለባልንጀራ፣ ለወላጆች፣ ለልጆችና ለአገር ያለብንን ግዴታ ሁሉ በዚህ መጽሐፍ ተጽፎ እናገኘዋለን።

የመጽሐፈ ምሳሌን አብዛኛው ክፍል የጻፈው ሰለሞን ነው። እጅግ ጥበበኛ ከመሆኑ የተነሣ እሱ ራሱ "የጥበብ ወኪል" ተብሎ ተገልጿአል (1ኛ ነገ 3፡3-28፣ 4:29-30፣ 5:12)። ብዙ የውጭ መሪዎች የእርሱን ምክር ለመጠየቅ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር (2ኛ ዜና 9:1-24) ከሰለሞን ጋር (ምሳ. 1:1፣ 10:1) የሚከተሉት ጸሐፊዎችም ተጠቅሰዋል።

1. የጠቢባን ቃላት	ምሳሌ 22:17
2. በሕዝቅያስ ሰዎች የተቀዱ የሰለሞን ምሳሌዎች	ምሳሌ 25:1
3. አጉር	ምሳሌ 30:1
4. ንጉሥ ልሙኤል	ምሳሌ 31:1

መጽሐፉ በሦስት ይከፈላል

1. ለወጣቶች የተሰጠ ምክር	ምዕራፍ 1-10
2. ለሰዎች ሁሉ የተሰጠ ምክር	ምዕራፍ 11-20
3. ለነገሥታትና ለመሪዎች የተሰጠ ምክር	ምዕራፍ 21-31

ከዚህ አስገራሚ መጽሐፍ ውስጥ ትኩረት ሊሰጥበት የሚገባው ምዕራፍ 8 ነው። ይህ ምዕራፍ ጥበብን በቆንጆ አገላለጽ የሚያሳይ ነው። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በአዲስ ኪዳን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጡትና በዚህ ምዕራፍ መካከል ያላቸውን ተመሳሳይነት ለመገንዘብ ችለዋል። ለምሳሌ በቆላስይስ 2:3 ላይ ስለ ጥበብና እውቀት ሲናገር "የጥበብና የእውቀት ሃብት ተሰውሮ የሚገኘው በክርስቶስ ዘንድ ነው" ይላል። በምሳሌ መጽሐፍ ጥበብ በሚለው ቃል ፋንታ ክርስቶስ የሚለውን በማስገባት ለማንበብ ሞክር። ይህ መጽሐፍ ያለውን ኃይል በሌላው ጎን ያሳይሃል። ቢሆንም በምሳሌ 8 ውስጥ ጥበብ አካል ወይም ሰብዕና ባለው መልክና ሰውኛ በተባለው ዘይቤያዊ ንግግር እንድትናገር በማድረግ ተገልጿል እንጂ የተነገረው ሁሉ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብለን መውሰድ አይገባንም።

(6). ምሳሌ 8:23-31 ከዮሐ 1:1-2 እና ከዕብ 1:2 ጋር አነጻጽር። በሁሉም ምንባቦች ውስጥ ስለ ጥበብ ሁለት ነገሮችን ከ8:23-31 በማስታወሻ ደብተር ላይ ጻፍ።

(7). በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ የተዘረዘሩትን ጥቅሶች ካነበብህ በኋላ ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በማስገባት አብሮ የሚሄደውን አመልክት።

1. 3:5-6	ሀ. ሐሜት
2. 6:6-8	ለ. ስንፍና/ሥራፈትነት
3. 11:1	ሐ. ማጭበርበር
4. 11:13	መ. ትዕቢት
5. 16:18	ሠ. ምሬት
	ረ. ታማኝነት

(8). *መጽሐፈ ምሳሌን በተሻለ መንገድ ሊጠቃለል የሚችለው፡*

ሀ. ለእግዚአብሔር ስለምንሰራው ሥራ የተሰበሰቡ የጥበብ አባባሎች
ለ. ነገሥታት እንዴት መኖር እንዳለባቸው የተሰጠ ገለጻ
ሐ. በሕይወት ማንኑነቶች ሁሉ ውስጥ በሥራ የሚተረጎም ተግባራዊ ጥበብ

መጽሐፈ መክብብ - ተስፋ ስለማጣት የተሰጠ መልስ
መክብብ 1:1-12:14 አንብብ

ዓላማ 5 የመጽሐፈ መክብብን ዋና መልእክት ለመግለጽ።

በመጽሐፈ መክብብ ውስጥ የሰፈረው ስብእዊ የሆነ የኑሮ ፍልስፍና ነው። የሰው አእምሮ ሊያፈልቅ የሚችለውን ፍልስፍናና ሰው ሠራሽ ሃይማኖት ሊሰጥ የሚችለውን መፍትሔ ያዘለ ሰነድ ይመስላል። በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኘው እግዚአብሔር ለማለት የፈለገው ሃሳብ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር መነፈስ መሪነት የተጻፈ የሰው ልጅ ሃሳብ ወይም አመለካከት ነው። እንዲያውም አንዳንድ የመጽሐፈ መክብብ ክፍሎች ከመጽሐፍ ቅዱስ አባባል ጋር በቀጥታ የሚቃረኑ ናቸው (መክ 1:15፣ 3:19፣ 8:15)።

ጸሐፊው ራሱን "የሰባኪው፣ የዳዊት ልጅ የኢየሩሳሌም ንጉሥ" ብሎ ይጠራል። ይህም ሰለሞን እንደሆነና መጽሐፉም የእርሱን የሕይወት ልምምድ የሚያንጸባርቅ እንደሆነ ይገመታል። የጸሐፊው ዋነኛ ጥያቄ "ከዐሐይ በታች በሚደክምበት ድካም ሁሉ የሰው ትርፉ ምንድን ነው?" የሚል ነው። ሰዎች ተድላንና ደስታን ፍለጋ በሚያደርጉት ሩጫ ሁሉ እርካታ ቢስና ተስፋ የሌለው እንደሆነ ይናገራል። ሰዎች ከእግዚአብሔር ውጭ እርካታን ይፈልጋሉ (መክ 1:1-3)። በሳይንስ ውስጥ እርካታን ያፈልጋሉ (መክ 1:4-11)። በፍልስፍና ውስጥ መልስ አያገኙም (መክ 1:12=18) ተድላ፣ ደስታ፣ ስካር፣ ሥራ፣ ባለጠግነት፣ ሙዚቃ እርካታን አይሰጣቸውም (መክ 2:1-11)። ሁሉም ከንቱ፣ ነው!! ጸሐፊው እርካታ ይሰጣሉ የተባሉትን ሌሎች ነገሮችም ሞክሮ ሁሉም ከንቱ፣ ሆነው አገኛቸው።

ጸሐፊው የንዋይን ፍቅር ሞከረ (መክ 2:12-16)፣ ሁሉንም በግድየለሽነት የመቀበል አቅል እምነትንም ሞከረ (መክ 3:1-15)፣ ሕያውነት የሌለውን የሰም ሃይማኖት ተከተለ (መክ 3:16-22)። እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ግን ቀላል እንዳልሆነ ተረዳ (መክ 5:1-8)። ባለጠግነት ምንም ደስታ አልሰጠውም (መክ 5:9-16)፣ መልካም ሥነ ምግባርም ደስታን አልሰጠውም (መክ 7:1-12)።

በመጨረሻ ጸሐፊው አስፈላጊ ወደሆነው ነጥብ ደረሰ። ይህም "የነገር ሁሉ ማሰሪያ፣ የችግሩ መፍትሔ የሆነው እግዚአብሔርን መፍራትና የእግዚአብሔርን ትዕዛዝት መጠበቅ ነው" (መክ 12: 13)።

(9). *የመጽሐፈ መክብብ ዋና መልዕክቱ ምንድን ነው?*

ሀ. ስለ ሃብትና ንብረት የሰለሞን ሃሳብ ምን እንደነበር ይነግረናል።
ለ. በሕይወት ምንም ደስ የሚያሰኝ ነገር እንደሌለ ይነግረናል።
ሐ. ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ በስተቀር የቀረው በሙሉ መጨረሻው ተስፋ መቁረጥ ላይ እንደሚያደርስ ይነግረናል።
መ. ሃብታምና ድሃ ሰዎች አንድ ዓይነት የሆነ እድል እንደሚገጥማቸው ያመለክታል።

የእምልክ ጽሑፎች

እግዚአብሔር ሰውን ከእርሱ ጋር ሕብረት እንዲኖረው ፈጠረ። ከመጽሐፈ መክብብ እንደተማርነው ሰው ከእግዚአብሔር ውጭ ለኑሮው ትርጉም አያገኝም።

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ከሚፈጥርባቸው መንገዶች አንዱ አምልኮ ነው። እግዚአብሔርን በናመልክ የእግዚአብሔርን ክብርነት እንረዳለን። ለእግዚአብሔር ሥራ ልንሮጥ እንችላለን። ነገር ግን ዘላቂ እርካታ የምናገኘው ለእርሱ መገዛት ሲኖረንና በእውነተኛ አምልኮ ፍቅራችንን ስንገልጽ ነው። በዚህ ክፍል የምናጠናቸው ሁለት መጻሕፍት የአምልኮ ምሳሌዎች ሆነው ሊያገለግሉን የሚችሉ ናቸው።

መጽሐፈ መዝሙር - ምሥጋናና ጸሎት
መዝ 1-41፣ 79-91፣ 119-150 አንብብ

ዓላማ 6 የምስጋናና የጸሎት መዝሙሮችን ለመግለጽ

የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ለዘመናት ታዋቂና ተወዳጅ ከሆኑት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ ነው። ከዳዊት ዘመን ጀምሮ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ለማምለክ ተጠቅመውበታል። ዛሬም ቢሆን ክርስቲያኖች በየትኛውም አገር ለዝማሬ ይጠቀሙበታል። የዳዊት መዝሙር ተወዳጅ ሊሆን የቻለበትም ምክንያት ጽሑፎቹ በሰው የሕይወት ልምምድ ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው ነው።

መዝሙራት የተባሉትም የምስጋናና የውዳሴ መጻሕፍት ስለሆኑ ነው። የእግዚአብሔርንም ስም፣ ታልና ቸርነት በምስጋናና በውዳሴ ስለሚገልጹ ነው። የመጽሐፈ መዝሙር ሁለት ሦስተኛው ክፍል ጸሐፊዎች ወይም ደራሲዎች በስም ተጠቅሰዋል። ከነዚህም ውስጥ ዳዊት 73 መዝሙራት ሲጽፍ፣ አሳፍ 12፣ የቆሬ ልጆች 10፣ ሰለሞን 2፣ ሙሴ 1፣ ኢታንና ሔማን 2 መዝሙራት ጽፈዋል (1ነገ 4:31)።

አሳፍ በዳዊት የተሾመ የመዘምራን አለቃ ነበር። የቆሬ ልጆች የተባሉትም በዳዊት ዘመን የነበሩ ከሌዊ ወገን የሆኑ የመዘምራን ቡድን እንደሆኑ ይገመታል። አሐፊዎቻቸው በሰም ያልታወቁት የቀሩት መዝሙሮች ደግሞ የዳዊት የራሱ መዝሙሮች ይመስላሉ። የሕይወት ልምምዱም መዝሙራቱ ባለበት ዐቃ ሁሉ ተንፀባርቆአል። ተስፋ በሚያስቆርጥ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ለኛ የሚያስብና የሚጠነቀቅ አምላክ ስመሆኑ ዳዊት ከሕይወቱ ልምምድ በግልጽ አካፍሎናል።

150 የሚሆኑት እነዚህ መዝሙራት በአምስት ክፍሎች ወይም መጽሐፍቶች ይከፈላሉ። ይህም የተለመደ አከፋፈላቸው ሲሆን፣ እያንዳንዱ ክፍል በምስጋና ቃል ይጨርሳል። አከፋፈላቸውም ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

1.	መዝሙር	1-41	መጽሐፍ 1
2.	መዝሙር	42-72	መጽሐፍ 2
3.	መዝሙር	73-89	መጽሐፍ 3
4.	መዝሙር	90-106	መጽሐፍ 4
5.	መዝሙር	107-150	መጽሐፍ 5

መዝሙራት እንደ ርዕሰ ጉዳያቸው የጸሎት፣ የንስሐና የኑዛዜ፣ የምስጋና፣ የታሪክ፣ የትንቢት፣ የመከራ እና የትምህርት በመባል ሊከፋፈሉ ይችላሉ።

(10). ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ምዕራፎች ከመዝሙረ ዳዊት ካነበብህ በኋላ አብሮ የሚሄደውን በክፍተቱ ስፍራ ቁጥሩን በማስገባት አመልክት።

1. ንስሐና ኑዛዜ
2. ትምህርት
3. ታሪክ
4. ጭንቀት
5. ምሥጋና

____ሀ. መዝ 1
____ለ. መዝ 32
____ሐ. መዝ 105
____መ. መዝ 111
____ሠ. መዝ 142
____ረ. መዝ 149

በመዝሙራት ውስጥ ስለ መሲሑ ስለ ክርስቶስ የተነገሩ ብዙ ትንቢቶች አሉ። ከነዚህም ትንቢቶች ብዙዎቹ በመጀመሪያ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ ሲፈጸሙ፣ ሌሎቹ ደግሞ በዳግም ምጽአት ጊዜ የሚፈፀሙ ይሆናሉ።

(11). ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥቅሶች ከመዝሙረ ዳዊት ካነበብክ በኋላ ስለ ክርስቶስ ምን እንደሚናገሩ አጭር መግለጫ ስጥ፣

ሀ. መዝ 2:8 ለ. መዝ 22:16 ሐ. መዝ 110:4 መ. መዝ 118:22

ከእግዚአብሔር ጋር ስላለን ሕብረት መዝሙራት የሚያስተምሩን አንድ ቁም ነገር አለ። ይኸውም ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ሕብረት ከወዳጅ

ጋር እንደሚደረግ ማንኛውም ምድራዊ ሕብረት ሁሉ ቅንነትን የሚፈልግ መሆኑን ነው። ሕብረት እውነት ላይ ሊመሠረት ይገባዋል። እግዚአብሔር በጸሎትና በአምልኮ ጊዜ ከኛ ስለሚፈልገው ነገር ዳዊት በመዝሙሮቹ ገልጾታል። ይኸውም እውነተኛና ትክክለኛ ለሚታችንን መግለጽ ነው። በመቅደስ ወይም በሞኛ ተሸሽገን ስናመልክ፣ በሐዘን አዘቅት ውስጥ ሆነን አለዚያም በደስታና ፈንጠዚያ ስሜታችንን የምንገልጥባቸው መዝሙራት አሉ። የመዝሙርን መጽሐፍ የግልህ መጽሐፍህ ልታደርገው ይገባል።

(12). 2 ሳሙ 11 እና 12 ካነበብክ በኋላ መዝ 51 አንብብ። የእግዚአብሔር ነቢይ ሳቀረበው መልእክት የዳዊት ምላሽ እንዴት ነበር?

(13). በመዝ 5:3 ላይ ዳዊት ምን አለ?

የግልህ የአምልኮ፣ የምሥጋና የጸሎት ጊዜ አለህ? ከሌለህ በማም አስፈላጊ ጉዳይ ስለሆነ ጊዜ መርጠህ ዛሬውኑ ጀምር።

(14). እውነተኛ የሆነውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. የመዝሙር መጽሐፍ ከተጻፈ ረጅም ጊዜ ቢሆንም አማኞች ዛሬም ይጠቀሙበታል።
ለ. ሦስት አራተኛው የተጻፈው በዳዊት ነበር።
ሐ. ተስፋ መቁረጥና ጭንቀት የእግዚአብሔር ሰዎች ልምምድ እንዳልሆነ መዝሙረኛው ይነግረናል።
መ. የመዝሙር መጽሐፍ ስለ ክርስቶስ ሞት የሚናገሩ ትንቢቶችን ይዟል።
ሠ. አንዳንድ የመዝሙር ምንባቦች በእሥራኤል ታሪክ ውስጥ የተፈጸመ ሁኔታዎችን ያወሳሉ

መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን - ታማኝነትና ፍቅር

መኃልየ 1:1-8-14 አንብብ

ዓላማ 7 የመጽሐፉን ባዘሪያት መንፈሳዊ መልእክቱን ለማየት

ይህ መዝሙር ሰሎሞን ከደረሳቸው አንድ ሺህ አምስት መዝሙራት አንዱ ነው (1ነገ 4:32)። መኃልየ መኃልይ ማለት "የመዝሙራት ሁሉ መዝሙር" ማለት ሲሆን ከሰሎሞን መዝሙራት ሁሉ ብልጫ እንዳለው ከዚህ ለመረዳት እንችላለን።

በቀጥተኛው ትርጉሙ መጽሐፉ የሚናገረው ስለሰው የጋለ የፍቅር ስሜትና ስለጋብቻ ነው። ዋናዎቹ ተናጋሪዎች የሱላማጢት ሴትና አፍቃሪዋ እንዲሁም ከኢየሩሳሌም የተውጣጡ ሴቶች ናቸው (6:13)። ሁለቱ ተፋቃሪዎች ሙሽራይቱና ሙሽራው በመባል የቀረቡ ሲሆን እንደኛው ትርጉም እንደሚያመለክተው ሴቲቱ ወደ ቤተ መንግሥት ተወስዳ ንጉሱ ለእርሷ ያለውን ፍቅር ይገልጽላታል (1:1-2:7)። እርሷ ግን የምትሻውና

የምትናገረው እረኛ አፍቃሪዋን ነው (2:8-7:9)። መጨረሻም ከእርሱ ጋር ትጣመራለች (7:10-8:14)። ሌሎች ብዙ ትርጉሞችም ይዛሞ ተሰጥተዋል።

መጋልየ መጋልይ በሁለት ወገኖች መካከል ያለውን ፍቅር ለሚያመለክት መንፈሳዊ ትርጉም በእግዚአብሔርና በሕዝቡ በእስራኤል መካከል ያለውን ግንኙነት በምሳሌነት ያሳያል። በእስራኤልና በእረኛዋ በእግዚአብሔር መካከል ያለው መተሳሰር በጣም ጠንካራ በመሆኑ ማንም ሊያቋርጠው አይችልም። በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለውን ግንኙነት ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም በጋብቻ ይመሰሉታል (ኢሳ 50:1፣ ሕዝ 16:23 እና 3:1-20 ተመልከት)። በአዲስ ኪዳን ደግሞ እንደሚታየው እንደጋብቻ የተገለጸውን በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ላለው ግንኙነት ምሳሌ ነው (ኤፌ 5)።

(15). ከዚህ በታች የተጻፈውን መግለጫ ካነበብህ በኋላ ቁጥሩን በተሰጠው ሥፍራ በማስገባት አብሮ የሚሄደውን አመልክት።

1. ቀጥተኛ ትርጉም 2. መንፈሳዊ ትርጉም

_____ሀ. ሱናማዊት ሴት በለ እረኛው ፍቅረኛዋ ታልማለች።
_____ለ. እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው ፍቅር እጅግ አስደናቂ ነው።
_____ሐ. እረኛው ወደእርሱ እንድትመጣ ፍቅረኛውን ይጠራታል።
_____መ. እስራኤል ለሚወዳት ለእግዚአብሔር ታማኝ ነች።
_____ሠ. በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለው መተሳሰር በጣም የጠለቀ ነው።

የመከራ ፈተና

1. የሚከተለው አረፍተ ነገር ከምሳሌ መጽሐፍ የተወሰደ የጥቅሱ የመጀመሪያ ሰንኝ ነው። ጥቅሱ በተታራኒ ትይዩነት የተጻፈ የግጥም በልት ስለሆነ ሁለተኛው መሥመር ምን መሆን አለበት?

የመልካም ሰው ቃላት እንደ ንጹህ ብር ነው

ሀ. የክፉ ሰው ሃሳብ ዋጋቢስ ነው።
ለ. ብዙ ሰዎችን ይጠቅማል።
ሐ. የጻቅ ሰው ንግግር የሕይወት ምንጭ ነው።

2. ስለ መጽሐፈ መክብብ እውነት የሆነውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. ዘብት ማግኘት እንደ ሕይወት ግብ መቁጠር ከንቱ ነው።
ለ. ደስታ የሚገኘው እግዚአብሔርን በመታዘዝ ብቻ እንደሆነ ይደመድማል።
ሐ. ጸሐፊው ዳዊት ነበር።
መ. የተሰጡት መግለጫዎች ሁሉ ከሌሎቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ይስማማሉ።
ሠ. ስለ ሕይወት የእግዚአብሔር አስተያየት ተሰጥቶበታል።

3. በአዲስ ኪዳን ውስጥ በእግዚአብሔርና በዘንዶ መካከል ያለው ግንኙነት በጋብቻ ውስጥ እንዳለ ግንኙነት ተመስሉአል (ኤፌ. 5) በብሉይ ኪዳን ተመሳሳይ የሆነ ስዕል የምናገኘው በየትኛው መጽሐፍ ነው?

ሀ. በኢዮብ
ለ. በመዝሙር
ሐ. በምሳሌ
መ. በመክብብ
ሠ. በመጋልየ መጋልይ

4. የኢዮብ መልእክት እንደሚያበረዳው ኢዮብ የተሰቃየው

ሀ. ኃጢአቱንና ክፋቱን እንዲያቆም እግዚአብሔር ስለፈለገ ነው።
ለ. ለለራሱና ስለ እግዚአብሔር አዲስ ነገሮችን እንዲያስተምረው ብሎ ነው።
ሐ. ጓደኞቹ ሁሉ የእግዚአብሔር ዓላማ እንደገባቸው ሊያሳየው ፈልጎ ነው።
መ. ኢዮብ የተፈረደበት በኃጢአቱ እንደሆነ ሰይጣን እንዲያይ ለማድረግ ፈልጎ ነው።

5. ስለ አምልኮ መንገዶችና ጓደኝነት ለማመዛዘን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለማበጠናት ብትፈልግ፣ ይህን ጥናት ለማካሄድ የተሻለው መጽሐፍ የትኛው ነው?

ሀ. ኢዮብ ለ. መዝሙር ሐ. ምሳሌ መ. መክብብ

6. እይሁዶች የምሳሌን መጽሐፍ በመቅደሱ ውጭአዊ አደባባይ የመሰሉት

ሀ. ልዩ ልዩ መሥዋዕቶችን ስለማቅረብ ሕጎችን ስለሚገልጽ ነው።
ለ. ስለ ካህናት ሥራዎች አንድ ክፍል ስላለው ነው።
ሐ. ሰው ከሌሎች ጋር ሲኖረው ስለሚገባ ግንኙነት ተግባራዊ ጥበብን ስለሚሰጥ ነው።

7. ከዚህ በታች ያሉት ጥቅሶች ከአምስቱ የግጥምና የጥበብ መጻሕፍት የተወሰዱ ናቸው። አብሮ የሚሄደውን በተሰጠው ሰፍራ ቁጥሩን በማስገባት አመልክት።

1. ኢዮብ
2. ምሳሌ
3. መክብብ
4. መዝሙር
5. መኃልየ መኃልይ

____ሀ. ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር እልል ይበል!
ለስሙ ክብር ዘምሩ፣ ውዳሴውንም አድምቁ!
____ለ. እግዚአብሔር ጥፋትህን እንዲያሳይህ ጠየቅኸውን?
ኃጢአትን ማድረግ ለማቆም ተስማምተሃልን?
____ሐ. በዚህ ዓለም ላይ የሚደረገውን ነገር ሁሉ አይቻለሁ፣ ልንገራችሁ ሁሉም ከንቱ ነው፣ ነፋስን እንደመከተል ነው።
____መ. ፍቅሬ ሆይ ከአትክልቱ ስፍራ ድምፅሽን ልስማው ጓደኞቼ ሰትናገሪ ለመስማት በናፍቆት ይጠብቃሉ።
____ሠ. ስለ አንተ የማውቀው ሌሎች ከነገሩኝ ብቻ ነበር፣ አሁን ግን ዓይኔ አይታሃለች።
____ረ. ለሞኝ ሰው የማጠቅም ነገር በነገር አትመ ሊቀበለው አይችልም።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

8. ሐ

1. ኢዮብ፣ መዝሙር፣ ምሳሌ፣ መክብብና መኃልየ መኃልይ

9. ሐ

2. አስቴርና ኢሳይያስ

10. ሀ. 2) ትምህርት ለ. 1) ንስሐና ኑዛዜ ሐ. 3) ታሪክ
መ. 5) ምሥጋና ሠ. 4) ሐዘን ረ. 5) ምሥጋና

11. ሀ.2:8 በምድር ላይ ሁሉ ይገዛል
ለ. 22:16 እጀቴና እግሮቼ ተወግተዋል
ሐ. 110:4 እንደ መልከጼዴቅ ሹመት ኅዘን ነው
መ. 118:22 እርሱ ከሁሉም በላይ የሆነውና የተናቀው ዓለት ነበር

3. ሀ. 3) አጠናካሪ መ. 2) ተደጋጋሚ
ለ. 1) ቤት የሚመታ ሠ. 4) ተቃራኒ
ሐ. 4) ተቃራኒ

12. ኃጢአቱን በመናዘዝ ንስሐ ገባ

4. ሐ

13. ወደ ጌታ በጠዋት እንደጸለየ ይናገራል።

5. ለ

14. ሀ. እውነት መ. እውነት
ለ. ሐሰት ሠ. እውነት
ሐ. ሐሰት

6. ጥበብ ከፍጥረት በፊት ነበረ፣ በፍጥረትም ውስጥ ድርሻ ነበረው።

15. ሀ. 1) ቀጥተኛ ለ. 2) መንፈሳዊ
ሐ. 1) ቀጥተኛ መ. 2) መንፈሳዊ
ሠ. 2) መንፈሳዊ

7. ሀ. 4) 11:13 መ. 5) 16:18
ለ. 2) 6:6-8 ሠ. 1) 3:5-6
ሐ. 3) 11:1 ረ. 3) 11:1

8

ትምህርት

የተከፋፈለ መንግሥት

ባለፈው ትምህርት በነገሥታት ዘመን ስለተጻፉት የቅኔና የጥበብ መጻሕፍት ተምረናል። በዚህ ክፍለ ጊዜ ደግሞ የንጉሡ ሰለሞን የኋለኛ ዘመን ዓመታትና ከዚያም በኋላ የተፈጸሙ ድርጊቶችን እንመለከታለን።

በመሳፍንት ዘመን እንደነበረው ውጣ ውረድ ሳይሆን፣ በተባበረው መንግሥት ዘመን የእስራኤል ሕዝብ ወርቃማ ጊዜ ነበራቸው፣ ብዙ አገሮችንም አስተዳድረው ነበር። ሆኖም እጅግ በተባረኩና በሰለጠኑ ጊዜ ግድ የሰዎች እየሆኑ መጡ፣ ሣአታትን ማምለክም አበዙ። በነቢዩ ሳሙኤል የተነሣቸውንም "እግዚአብሔርን ፍሩ፣ ያደረገላችሁንም ታላቅ ነገር አይታችኋልና በፍጹም ልባችሁ በእውነት አምልኩት" (1ሳሙ 12:24) የሚለውን መመሪያ ዘነጉ። ንጉሥ ሰሎሞንም ባዕድ አምልኮ ሰላዘወተረ እግዚአብሔር ፍርድን አመጣበት።

በተጨማሪም በነገዶች መካከል ያለው ጥላቻ አገረሸ። የመለያየትና የመከፋፈል ጥላ እንጥበበባቸው። የእሥራኤልም ክብርና ድል እየሟሸሸ መጣ። ከሁሉም የከፋው በእስራኤላውያን በደል ምክንያት የእግዚአብሔር ሰም በአሕዛብ መካከል መሰደቢያና ማላገጫ መሆኑ ነበር። ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ሕዝቡን አልተዋቸውም። በነቢያት በኩል መልዕክት ያስተላልፍና ይመክራቸው ነበር።

የትምህርቱ አከፋፈል

- የተባበረው መንግሥት መከፈል
- ስለተከፈለው መንግሥት ማብራሪያ
- የተከፈለው መንግሥት ታሪክ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- የተባበረው መንግሥት ለምን እንደተከፈለ ማስረዳት
- የተከፈለውን መንግሥት ዋና ዋና ባህሪና ታሪክ መግለጽ
- በዚሁ ዓመታት ያገለገሉትን ነብያት መልእክት በአጭሩ መግለጽ

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. በክፍለ ትምህርቱ ላይ የተሰጡትን ምንባቦች በሙሉ አንብበህ መጨረስህን አረጋግጥ።

2. ትምህርቱን በሚገባ ተከታትለህ ስትጨርስ የመከራ ፈተናውን ውሰድ። ከዚያም መልሶችህን በመጽሐፉ ላይ ከሰፈሩት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸው ካሉ እስተካክል።

የተባበረው መንግሥት መከፈል

1ነገ 11:14፣ 1ዜና 10-11 አንብብ

ዓላማ 1 ለመንግሥቱ መከፈል ምክንያት የሆኑትንና ውጤቶቹን ለመግለጽ።

ንጉሥ ዋናውን እንደሚያስከትልባቸው እግዚአብሔር ሕዝቡን በሙሴ፣ በኢያሱና በሳሙኤል በኩል አስቀድሞ አስጠንቅቆአቸው ነበር። አሁንም የደረሰባቸው ችግር በሙሉ ጠላት ምክንያት የመጣ መከራዎች ሳይሆን፣ ራሳቸው በልባቸው እግዚአብሔርን ችላ በማለታቸው የመጣ ሽንፈት ነው። ስለዚህ ስለንጉሣቸው ከእግዚአብሔር ፍርድ መቀበል ነበረባቸው። የእስራኤል መንግሥት ለሁለት መከፈል ሦስት ምክንያቶች ነበሩ።

የሰሎሞን ወደ ጣዖት አምልኮ ማዘንበል

ባዕድ አምልኮን እንዳይከተል እግዚአብሔር ሰሎሞንን ሁለት ጊዜ አስጠንቅቆት ነበር። ሆኖም ሰሎሞን ከእርሱ ፈቀቅ አለ እንጂ ለእግዚአብሔር አልታዘዘም (1ነገ 11:10)። ከዚህም የተነሣ በርሱ ዘመን አይሁን እንጂ መንግሥቱ ከእርሱ እንደምትወሰድ፣ እግዚአብሔር ለንጉሡ ለዳዊትና ስሰአያሩሳሌም ሲል አንድን ነገድ ለሰሎሞን ልጅ እንደሚያስቀርለት ነገረው (1ነገ 11:13)። ለመንግሥቱ መከፈል ሦስተኛው ምክንያት የሆነው ሰሎሞንና ሕዝቡ እግዚአብሔርን ትተው ወደ ጣዖታትና ባዕድ አምልኮ መመለሳቸው ነበር።

(1). 1ነገ 11:27-39 ካነበበህ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. ነቢዩ ለመንግሥቱ መከፈል ምን ምክንያት ሰጠ?
ለ. መንግሥቱ የሚከፈለው እንዴት ነበር?

የሮብዓም ዝንባሌ

ለመንግሥቱ መከፈል ሁለተኛ ምክንያት የሆነው የሰሎሞን ልጅ የሮብዓም ዝንባሌ ነበር። በሰሎሞን የኋለኛው ዓመታት ሕዝቡ ከፍተኛ የግብር ጫና ስለነበረባቸው ሰላም አሳጥቸው። አዲሱ ንጉሣቸው ሮብዓምን ከዚህ የግብር ፅና እንዲያላቅሩላቸው ጠየቁት። እርሱም ጥበብ የሚጎድለትን የአሳውንቶችን ምክር ንቆ ወጣት ባልንጀሮቹን አማከራቸው። የሰጠው ምላሽ በ1ኛ ነገ 12:14 ላይ እንደተመዘገበው ተጨማሪ ግፍን የሚያንጸባርቅ ነበር። ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ በማመጽ በሰሎሞን ዘመን ከሹማምንት አንዱ የነበረውን ኢዮርብዓምን በማንገስ የሰሜኑን መንግሥት አቋቋሙ።

በነገዶች መካከል ጥላቻ

ሦስተኛው ምክንያት ከጥንት ጀምሮ በይሁዳና በኤፍሬም ነገድ መካከል የነበረው ጥላቻ መቀስቀሱ ነው። ኢያሱ ኤፍሬማዊ ነበር። በሌላ በኩል ንጉሥ ሳኦል ደግሞ ከብንያም ነገድ የተመረጠ ሲሆን ዳዊት ከይሁዳ ወገን ነበር። በይሁዳና በኤፍሬም መካከል ያለው ሽኩቻ በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል። ለእግዚአብሔር መታዘዝ ሲጀምሩ አንድነታቸው ይታያሰል። ማመጽ ሲጀምሩ ደግሞ ሊወገድ የማይችል መለያየት ይፈጠራል።

መንግሥቱ በሁለት ተቀናቃኝ ቡድን ሲከፈል ጠቅላላ የእስራኤል አስተዳደር ተናጋ። ፍስጥኤማውያን፣ ሶሪያውያን፣ አሞናውያን ሁሉ ለእስራኤል ከነበራቸው ተገዥነትና ግብሪነት ነፃ ወጡ። ከፍተኛ የኢኮኖሚ መናጋት ተፈጠረ። የግብሪዎች የገንዘብ ምንጭ ሲቋረጥ አስራኤል ምጣኔ ሃብቷን መምራት አልቻለችም። እሥራኤላውያን ንግድ የሚያልፍበትን መሥመር ለመቆጣጠር ተሳናቸው። ጥናናው መንግሥት ሁለት ደካማና አንስተኛ መንግሥቶች በመሆን ተከፍሎ ቀረ።

(2). 1 ነገ 12 አንብብ። ሮብዓም በኢዮርብዓም ሥር የነበረውን ነገድ ለመውጋት ወታደር በለበለበ ጊዜ እግዚአብሔር ምን ተናገረው?

ሀ. አንድነትን ለመጠበቅ ከአመጸኞቹ ነገዶች ጋር ተዋጋ አለው።
ለ. ከነቢዩ መመሪያ አስኪመጣ ድረስ እንዲቆይ ነገረው።
ሐ. መከፈሉ የእርሱ ፈቃድ በመሆኑ ሕዝቡን ወደ መጠበት እንዲልክ ነገረው።

(3). ስለ መንግሥቱ መከፈል የተሰጡትን መግለጫዎች ካነበብክ በኋላ መግለጫው የመከፈሉ ምክንያት ወይም ውጤት መሆኑን ለመለየት ክፍት ቦታ ላይ ቁጥሩን በማስገባት አመልክት።

1. ምክንያት 2. ውጤት

_____ሀ. ሮብዓም የወጣት ጓደኞቹን ምክር ተከተለ።
_____ለ. የእሥራኤል ሕዝብ ማስገዛሩ ቀረ።
_____ሐ. የንግዱን መንገድ መቆጣጠር አልቻሉም።
_____መ. ሕዝቡና፣ ንጉሡ እግዚአብሔርን ከማምለክ ራቁ።
_____ሠ. ከሰለሞን የቀደሞ ሹም ከኢዮርብአም ሥር ሌላ መንግሥት ተቋቋመ።

ስለተከፈለው መንግሥት ማብራሪያ

ዓላማ 2 የለሜኑና የደቡቡ መንግሥታት ማንነትና ባሕርይ ለመግለጽ።

ስማቸው

"እሥራኤል" የሚለውን ስም እስካሁን ስንጠቀም የነበረው ለያዕቆብና ለዘሮቹ ነበር (ዘፍ 32:22-32፣ 49:2፣ኢያሱ 1:2)። መንግሥቱ ከተከፈለ በኋላ ግን "እስራኤል" የሚለው ስም በኢዮርብዓም መሪነት ለተቋቋመውና አሥሩን ነገድ ላቀፈው ለሰሜኑ መንግሥት ተሰጥቷል። የሰሜኑ መንግሥት አንዳንድ ጊዜ እጅግ ተሰሚነት በነበረው "በኤፍሬም" ነገድም ይጠራል።

በሌላ በኩል የይሁዳና የብንያም ነገዶችን ያቀፈው የደቡብ መንግሥት "ይሁዳ" የሚል ስያሜ ተሰጠው። የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ስናነብና ስናጠና እነዚህን ሁለት ስሞች፣ "እስራኤልና" "ይሁዳ" ለይተን መረዳት ይኖርብናል።

ሁለቱ መንግሥታት ሲነሳሀሩ የሰሜኑ መንግሥት "እስራኤል" ከደቡብ መንግሥት "ይሁዳ" ይልቅ ብዙ ጠቃሚ ነገሮች ነበሩት።

የሰሜኑ መንግሥት

- አሥር ኃያላን ነገዶችን አቅፎአል።
- የመሬቱ ይዞታ ሰፊ ከመሆኑም በላይ ፍሬያማውን የዮርዳኖስን ሸለቆ ይዞአል።
- የሕዝቡ ብዛት የይሁዳን ሦስት እጥፍ ነበር።
- በዳዊትና በሰሎሞን የተሠሩት መታይራዊ ማዕከሎች በዚያ ይገኛሉ።
- በቤቴል፣ በጌልጌላና በራማ የነበሩት የነቢያት ትምህርት ቤቶችም የሚገኙት በዚያ ነበር።

የደቡቡ መንግሥት

- በሕዝብ ብዛትና በመሬት ስፋት አነስተኛ ነበር።
- ሁለት ነገዶችን ብቻ ያቀፈል። (አንዳንድ ጊዜ ይሁዳና ቢንያም እንደ አንድ ነገድ ይቆጠሩ ነበር)
- የእስተዳደርና የሃይማኖት መዲና የሆነችው ኢየሩሳሌም በዚያ ትገኛለች።


የሰሜኑ ሕዝብ በኢየሩሳሌም ትዝታ እንዳይቀሳቀስና ለአምልኮ ወደዚያ እንዳይሳርፍ፣ ኢዮርብዓም በዳንና በቤቴል በምትኩ የአምልኮ ማዕከል በማሰራት ታላቅ ስህተትን ፈጸመ (1ነገ 12:25-31)። ከዚህም የተነሳ የእግዚአብሔር ቁጣ በኢዮርብዓም ላይ በመንደዱ የእግዚአብሔር ፍርድ መጣበት።

(4). 1ነገ 12:25-31 አንብብ። ሕዝቡ ለማምለክ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄ ለማድረግ ኢዮርብዓም ምን ለማድረግ ሞከረ?

ከኢዮርብዓም ድርጊት የተነሣ ለእግዚአብሔር የማያወላውል ታማኝነት የነበራቸው ካህናት፣ ሌዋውያንና ሌሎችም ሰዎች ከእያንዳንዱ የሰሜን ነገድ እየፈለሱ ለደቡብ መንግሥት ታማኝነታቸውን ገለጡ። የይሁዳም የሕዝብ ብዛት ቁጥር ጨመረ። በይሁዳም ግዛት የእያንዳንዱ ነገድ ቅሬታ ተገኘ (2ዜና 11:13-17)።

የደቡብ መንግሥት ከሰሜኑ የሚሻልበት አንድ ሌላ ምክንያት አለ። ይኸውም ነገሥታቱ ሁሉ ከአንድ ሐረግ የወጡ የዳዊት ዘር ነበሩ። ይህም እግዚአብሔር ለባሪያው ለዳዊት የገባውን ታላቅ ኪዳን መጠበቁን ያስረዳል። በተቃራኒው የሰሜኑ መንግሥት ነገሥታት ከዘጠኝ የተለያዩ የነገሥታት ቤተሰብ ሲሆኑ፣ አሥራ ዘጠኙ ክፉና ጠማማ ጎዟዎችም ከዚሁ ከሰሜን ነበሩ። እነዚህ ነገሥታት የመንግሥት ሥልጣን ይጨብጡ የነበረው አንዱ ሌላውን በመግደልና ደም በማፍሰስ ነበር። በዚህም ምክንያት የሰሜኑ መንግሥት ዕድሜ ከደቡቡ ይልቅ በ130 ዓመት ያጠረ ነበር።

እሥራኤል	ይሁዳ
የሰሜን አሥር ነገዶች መዲና ሴኬም በኋላም ሰማርያ የግዮት አምልኮ በዳንና በቤቴል	የደቡብ ሁለት ነገዶች መዲና ኢየሩሳሌም የአምልኮ ማዕከል ቤተ መቅደስ
ዘጠኝ የተለያዩ ሥርወ - መንግሥት ሁሉም ነገሥታት መጥፎ ነበሩ በጠቅላላ 19 ነገሥታት ነገሡ 240 ዓመታት ፈጀ	አንድ ሥርወ - መንግሥት መልካሞችና መጥፎ ነገሥታት ነበሩበት 19 ነገሥታትና 1 ንግሥት 395 ዓመታት ፈጀ
በ722 ዓ.ዓ መንግሥቱ ወደቀ በአሶራውያን እጅ በመውደቅ ወደ ምርኮ ተጋዙ	በ586 ዓ.ዓ መንግሥቱ ወደቀ በናቡከደነፆር አማካኝነት ወደ ባቢሎን ተማርከው ተጋዙ



(5). የሰሜኑ መንግሥት፦

ሀ. በንጉሥነት የተገዛው በዳዊት ነበር።
ለ. ሁለት የሃይማኖት ማዕከሎች ነበሩት።
ሐ. ከደቡብ ይልቅ የቆየው ለአሥሮር ጊዜ ነበር።

የሰሜኑና የደቡቡ መንግሥት ግንኙነት

የእርሰ በርሰ ጦርነት በአንድ አገር ላይ የሚያስከትለው ጥፋት በተላለ የሚገመት አይደለም። ቤተሰቦችን ይከፋፍላል፣ ሰዎች አንደ ልባቸው በመዘዋወር እንዳይሰሩ ያደርጋል። የንግድና የትራንስፖርት እንዲሁም የማሕበራዊ ኑሮ አገልግሎቶችን ያበላሻል። እሰራኤል አንድ ቤተሰብ፣ አንድ ቋንቋና አንድ ሕዝብ ነበሩ። አሁን ግን ነቢዩ አኪያ እንደተናገረው አሥራ ሁለት ዩታ እንደ ተቀደደ ልብስ ሆኑ። አሥሩ ቁራጭ በሁለቱ ቁራጭ ላይ ተባበረ። በሁለቱ ወገን የነበረው ግንኙነት በአራት ደረጀ ይከፈላል።

1. *የእርስ በርስ ጥላቻ*፦ በዚህ ዘመን የይሁዳ ነገሥታት በሰሜኑ መንግሥት ላይ ለማየል የሞከሩበት ጊዜ ነበር። ከዚያም የተነግ ለ60 ዓመታት በመካከላቸው የማያቋርጥ ጦርነት ነበር።

2. *በጋራ ጠላት ላይ ግንባር መፍጠር*፦ ሶሪያ በሁለቱ መንግሥታት ላይ በየጊዜው የወረራ መከራ ታደርግባቸው ነበር። ስለዚህም የእስራኤል ንጉሥ አክአብና የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥ በጋብቻ በመተሳሰር ግንባር ፈጠሩ። ይህም እያየለ የመጣውን የሶሪያን ኃይል ለመቋቋም ነበር።

3. *የእርስ በርስ ጥላቻ ማገርሸት*፦ ኢዩ በሰሜኑ መንግሥት ላይ በነገሠ ጊዜ የቀሩትን የአክአብን ዘሮች ፈጀ። ይህም አክአብ ከደቡብ መንግሥት ጋር ፈጥሮ የነበረውን ግንኙነት እንዲሻክር አደረገ። የሰሜኑ መንግሥት የባዕ ጣዖት አምላኪ እየሆነ ሄደ። ብዙ ትንቢታዊ መልእክቶችና ማሰጠንቀቂያዎች ቢነገሩም በመጨረሻው በ722 ዓ.ዓ. በአሶራውያን ተማረከ።

4. *የደቡብ መንግሥት ለብቻው*፦ አሶር፣ ግብፅና ከሰዳውያን ይዙዳን ለመውረር ሞከሩ። ይህ ትግል እስከ 586 ዓ.ዓ. ለ130 ዓመታት ሲካሄድ ቆየ። በመጨረሻም በዚሁ ዓመት ይሁዳ በናቡከደነጾር አማካይነት በባቢሎን ተማረከች።

(6). ከመግለጫው ጋር አብሮ የሚሄደውን ቁጥሩን በመጻፍ አመልክት።
1) የሰሜኑ 2) የደቡቡ

____ሀ. ፍሬያማ ምድር ያለው
____ለ. አነስተኛ ደሰ ምድር ያለው

____ሐ. በ722 በአሶራውያን የተማረከ
____መ. በ586 ዓ.ዓ በባቢሎን የወደቀ
____ሠ. የአክአብን ቤተሰብ የገደለ
____ረ. አሥሩን ነገዶች እንደገና ለመግዛት የሞከረ
____ሰ. ዘጠኝ የተለያየ ሥርወ - መንግሥት የነበረው
____ሸ. አንድ ሥርወ - መንግሥት ብቻ የነበረው
____ቀ. ዋና መቀመሜው ኢየሩሳሌም የሆነ
____በ. ከኢዮሳፍጥ ቤተሰብ ጋር በጋብቻ በኩል ጥምረት ያደረገ

የተከፋፈለው መንግሥት ታሪክ

1ነገ 15-16፣20-22፣ 1ዜና 13:17፣ 28-29፣ 2ዜና 13-20 አንብብ።

ታሪካቸው

ዓላማ 3 የሳሙኤልን፣ የነገሥትንና የዜና መዋልዕን መጽሐፍት ይዘት ለማብራራት።

የተባበረው መንግሥትና የተከፋፈለው መንግሥት ታሪክ በሳሙኤል፣ በነገሥትና በዜና መዋዕል መጻሕፍት ተመዝግቦአል። እነዚህ መጻሕፍት በአንድ ላይ የብሉይ ኪዳንን አንድ አምሰተኛውን ክፍል ሲይዙ፣ በእነዚህ መጻሕፍት የተመዘገበው ታሪክ የተጻፈው ከእግዚአብሔር አመለካከት፣ ዓላማና እቅድ አንጻር ነው። ለምሳሌ ያህል ዘንበሪ ሰለ ተባለው የሰሜን ንጉሥ ብንመለከት የዘንበሪ ቤተሰብ ለ44 ዓመታት ሲነግሱ ይህም በእሥራኤል ላይ ከነገሡት ሥርወ - መንግሥታት ውስጥ በርዝመት ሁለተኛው ነው። ሌሎች የታሪክ ምንጮች እንደሚናገሩት የዘንበሪ መንግሥት በሰሜን በጣም ዋናና ነበር። መዲናውንም ወደ ሰማሪያ አዛውሮ ታላቅ ከተማ አደርጓልታል። ሞአባውያን ወስደውት የነበረውን ግዛትም አሰመልሶአል። እንዲያውም አሶራዊያን በኋላ እሰራኤልን በወረሩበት ጊዜ የዘንበሪ አገር ብለው ነበር የጠሩት። ይህን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ የዘንበሪን መንግሥት ታሪክ በሁለት ጥቅሶች ብቻ ያጠቃልለዋል (1ነገ 16:23-24)። ለለሆነም እነዚህ ታሪካዊ ጽሑፎችን ስናጠና የተመዘገቡት ከመለኮታዊ ሃሳብና ዕቅድ አንጻር መሆኑን ማስታወስ አስፈላጊ ነው።

(7). 1ሳሙ 16:7 እና 1ነገ 16:21-28 አንብብ ዘንበሪ ሰለፈጸማቸው ድርጊቶች ጥቂት የተነገረለት ለምን ይመስልሃል?


ከላይ የጠቀስናቸው የታሪክ መጻሕፍት በደብታቸው ትኩረት የሚሰጡት በተለያዩ ርዕሶች ላይ ነው።
1. *1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል* የሚያተኩሩት ለሚቋቋመው መንግሥት መሠረት ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር ስለሰጣቸው *መመሪያዎች* ነው። የመንግሥቱ መሠረት በሳሙኤል የተብራሩት መንፈሳዊ መለኪያዎች ናቸው። የሚነሱት ነገሥታት ሁሉ የዳዊትን ታማኝ መሪነት በምሳሌነት ሊከተሉ ይገባቸዋል።

2. *1ኛ እና 2ኛ ነገሥት* የሚያተኩሩት መንግሥቱ እንዴት እየደገ እንደመጣ ነው። ናትን ለዳዊት የተናገረው ትንቢት ተፈጸሚነቱን በእነዚህ መጻሕፍት እናያለን (2 ሳሙ 7:12-16)። ይህም ትንቢት ከዳዊት በር ምንጊዜም ነገሥታት እንደማይታጡ ነው። 1ኛና 2ኛ ነገሥት ስለ ሁለቱም ለሰ ሰሜንና ደቡብ መንግሥታት ይናገራሉ። ለነቢዩ ለኤልያስና ለነቢዩ አልሳዕ በነዚህ መጻሕፍት ብዙ ሥፍራ ተሰጥቶአቸዋል።

3. *1ኛ እና 2ኛ ዜና መዋዕል* ትኩረት የሚሰጡት *ለቤተ መቅደሱ* ነው። ለለ መቅደሱ የአምልኮ ሥርዓትና ስለ አገልጋዮች ያብራራሉ። ዋና ርዕሳቸው ክህነቱና መቅደሱ ሆኖ ሳለ በሳኦል፣ በዳዊትና በሰሎሞን ያመራ ስለነበረው መንግሥትም ይናገራሉ። ከዚያም አብዝተው የሚያወሱት ለለ ደቡቡ የይሁዳ መንግሥት ታሪክ ነው። የሰሜኑ መንግሥት የተወገደው ከደቡብ ጋር የተያያዘና የተሳሰደ ነገር ሲኖር ብቻ ነበር።

(8). እውነተኛ የሆነውን መሣሰፍ ፊደሉን በመከበብ እመልክት።

ሀ. ሁለቱም የነገሥትና የዜና መዋዕል መጻሕፍት የይሁዳን ታሪክ አስፍረዋል።
ለ. የዜና መዋዕል መጽሐፍት አብዛኛው በጉባኤት ሕይወት ላይ ያተኩሩ ናቸው።
ሐ. የነገሥት መጽሐፍት የሚያተኩሩት በሰሜኑ መንግሥትና በክህነቱ ላይ ነው።
መ. የዜና መዋዕል መጻሕፍት የሚሸፍኑት ጊዜ ከሳሙኤልና ከነገሥት መጽሐፍት ጋር ተመሳሳይ ነው።
ሠ. የዜና መዋዕል መጽሐፍ የሚያመለመው ሕዝቡ ወደ ምርኮ ሲሄድ ነው
ረ. ለለ ዳዊት መንግሥት የተነገረው ትንቢት የሚገኘው በ2ኛ ሳሙኤል ላይ ነው።
ሰ. የሳሙኤልና የነገሥት መጻሕፍት ሳአል ስለነገሰበት ዘመን ይገልጻሉ።



መጽሐፈ ነገሥት	መጽሐፈ ዜና መዋዕል
የሁለቱም የይሁዳና የእስራኤል ታሪክ ለነብያቱ ትኩረት ይሰጣል ለለ መንግሥቱና ነገሥታቱ ይገልጻል የሚጨርሰው ህዝቡ ወደ ምርኮ ሲሄዱ ነው	ታሪኩ በአብዛኛው በይሁዳ ላይ ነው በክህነት ላይ ትኩረት ያደርጋል ለለ ቤተ መቅደስና ክህነቱ ይገልጻል የሚጨርሰው ህዝቡ ከምርኮ ሲመለስ ነው

ነገሥታት

2ነገ 20-24፣ 2ዜና 29-35 አንብብ

ዓላማ 4 ለለ እስራኤልና ይሁዳ ነገሥታት በዝርዝር ለመማለጽ።

የእለራኤልና የይሁዳ መንግሥት አካሄዳቸው የሚገመገመው በነገሥታቶቻቸው ነበር። ምክንያቱም ለሕዝቡ መንፈሳዊ አኗኗር የንጉሡ ሚና ከፍተኛና ወሳኝ በመሆኑ ነው። የሕዝቡ ሁኔታ በንጉሡ ማንነት ይወሰናል። ይህ በመልካምነቱም ሆነ በክፋቱ ነገሥታት አካሄድ ላይ የታየ ጉልህ ውጤት ነበር።

ከሰሎሞን በኋላ የነበሩት ነገሥታት ከእግዚአብሔር መንገድ ያፈገፈጉ ለለነበሩ ታሪካቸው አሳዛኝ ሆነ። በሰሜን መንግሥት፣ ኢዮርብዓም የወርቅ ምስሎች እሠርቶ እንዲያመልኩ አድርጎአል። የመጀመሪያው ንጉሥ እንደመሆኑ መጠን በመሣፎ ምሳሌነቱ ሕዝቡን አለቶአል፣ አገሪቱንም ለጥፋት ዳርጓታል (1ነገ 16:7፣ 22:52፣ 2ነገ 10:31)

በደቡብ ደግሞ ሮብዓም ሕዝቡ ለሐሰተኛ አማልክት የማምለኪያ ሥፍራ እንዲሠሩ ፈቀደላቸው። ከፓለስቲና እንዲያባርሩአቸው የታዘዙትን የነፋ ሕዝቦችን ፈለግ ተከተሉ (1ነገ 14:22-24)። ምንም እንኳን አብዛኞቹ ነገሥታት ክፋቶች ቢሆኑም መልካሞችም ነገሥታት ተነሥተዋል። ለምሳሌ ያህል በይሁዳ የሕዝቅያስ ዘመን መንፈሳዊ መነቃቃትና ሞገሥ የታየበት አስደናቂ ጊዜ ነበር (2ነገ 18:1-20:21)።

የነገሥታቱና የሕዝቡ መጥፎ አካሄድ በመጨረሻ ለሁለቱም መንግሥታት መውደቅ ምክንያት ሆነ። የሰሜን በ722 ዓ.ዓ. ሲወድቅ የደቡብ ደግሞ በ586 ዓ.ዓ. መደቀ። ይህ ዓይነቱን አወዳደቅ በዘዳ 28:33፣36 ላይ ከ800 ዓ መት በፊት በባሪያው በሙሴ በኩል እግዚአብሔር አስቀድሞ ተናግሮታል። የጣያት አምላኪነትና የዓመጽ ውጤቱም ምርኮና ስብራት ሆነ።

(9). ዘዳ 28:33፣36 ካነበብህ በኋላ ሕዝቡ ካልታዘዘ ምን እንደሚሆን በማለታወሻ ደብተርህ አስፍር፣

ነቢያቱና መልእክታቸው

1ነገ 17-19፣ 2ነገ 1-8፣19-20 አንብብ

ዓላማ 5 ወደፊት ስለሚፈፀሙት ነገሮች በተተነበዩት ትንቢቶች እና ዛሬ በእለት ተእለት ሕይወታችን ትክክል ለሆነውና ለላልሆነው መመሪያ በሚለውን ትንቢታዊ መልእክቶች መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ።

በሰሜንና በደቡቡ መንግሥታት የጨለማ ዘመን ሕዝቡን እንዲያስጠነቅቁ እግዚአብሔር ብዙ ነቢያትን አስነሣ። ከነዚህ ውስጥ 12 ያህሉ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በስማቸው የጻፏቸው መጻሕፍት አሉአቸው። ዮናስ ለሌላ አገር ከተማ የተላከ ሲሆን ሐጌ፣ ዘካርያስና ሚልኪያስ ከምርኮ በኋላ የተነሡ ነቢያት ናቸው። ነቢያት እንደ መሆናቸው መልእክታቸው የወደፊቱን የሚናገር ብቻ ሳይሆን ባለበት ዘመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሕዝቡ የሚያበራራ ነው። ስለ እገራቸው ወቅታዊ ሁኔታ በቂ እውቀት ነበራቸው፤ በ2ኛ ነገሥት 17:13 ላይ "እግዚአብሔር በነቢዩ ሁሉና በባለራዕዩ አና ሁሉ በእስራኤልና በይሁዳ መሰከረ" ተብሎ ተጽፏል።

ስለ ነብያቶቹና ስለሚመጣው ፍርድ ሰንገሥታቱም ሆነ ለሕዝቡ በትልቅ ደረጃ ለመናገር ነብያቱ ፍርሃት አይታይባቸውም ነበር። ነቢያት እግዚአብሔር በተሰጠ የመረጣቸው ሰዎች ነበሩ። አገልግሎታቸው እንደ ነገሥታትና ካህናት ሲወርድ ሲዋረድ የወረሱት አልነበረም። ከእግዚአብሔር ምርጫ በቀር የቤተሰብ የጎደ ወይም የትምህርት ተጽዕኖ አልነበረበትም። ነቢያት የሚከተሉት ሁለት ዋና ዋና ሥራዎች ነበሩአቸው።

- ከእግዚአብሔር መልእክትን መቀበል
- በእግዚአብሔር ስም መልእክትን ማስተላለፍ

የነብያት መልእክት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንጂ ከራሳቸው አልነበረም። መልእክታቸውን ከራሳቸው የሚያመነጩ የሐሰት ነብያት ብቻ ነበሩ። በእግዚአብሔር ስም የሚናገር ነቢይ የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደመሆኑ መጠን ነቢዩ የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ ያለ ፍርሃት በድፍረት ያቀርብ ነበር።

ነብያት መልእክትን ሲቀበሉና ሲያስተላልፉ በእግዚአብሔር መንፈስ ተንድተው ነው። ይሁን እንጂ የአእምሮ ችሎታቸው፣ የተፈጥሮ ባሕርያቸውና የአነጋገር ልምዳቸው እንዳለ ይሆናል። የሚያገለግሉት በእግዚአብሔር እጅ ያሉ መሣሪያዎች ሆነው እንጂ ግዑዝ ሰው ሰራሽ ዕቃዎች ሆነው እይደለም። በእግዚአብሔር መንፈስ መነዳት ማለት ክፉዎች መናፍስት በቁጥጥራቸው ስር እንደሚያውሉት ዓይነት ስላልሆነ ልዩነቱን መረዳት ጠቃሚ ነው።

የነብያት መልእክት ሦስት ክፍሎች

1. *ለራሳቸው ዘመንና ትውልድ* ከእግዚአብሔር በቀጥታ የተላከ መልእክት።

2. *የወደፊቱን ሁኔታ የሚናገር* መልእክት ለምሳሌ። የእሥራኤል ውድቀት እና ፍርድ፣ የጎረቤት አገሮች ሁኔታ፣ የመሲሁ መምጣት፣ የሚቀበለው መከራና የሚጠበቀው ክብር እንዲሁም የመሲሁ መንግሥት በምድር ላይ መቋቋም።

3. *አሁን በዚህ ዘመን* ላለን ትክክል የሆነውንና ያልሆነውን የምናውቅበት ሕያው መልእክት።

ነቢያት ለራሳቸው ዘመን መልእክትን በሚያስተላልፉበት ጊዜ በውስጡ የወደፊቱን የሚያመለክት ነገር ይኖርበታል፣ እንደዚሁም ትክክል የሆነውንና ያልሆነውን ለመለየትም የሚረዳ መመሪያ ይገኝበታል። በነቢያት መልእክት ስለ መጪውና ስለጉሮ መመሪያዎች ጠቃሚ ትምህርት እናገኝበታለን።

(10). ከትንቢተ ሚክያስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥቅሶች ካነበብህ በኋላ በተሰጠው ስፍራ ቁጥሩን በማስፈር አጠር የሚሄደውን አመልክት።

____ሀ. ሚክ 1:6-7
____ለ. ሚክ 2:1-3
____ሐ. ሚክ 3:8-11
____መ. ሚክ 5:2
____ሠ. ሚክ 6:6-8

1. መጻፊት የሚሆኑ ድርጊቶች
2. ትክክለኛ ለሆነውና ላልሆነው መመሪያዎች

ነቢያቱና አገልግሎታቸው

ዓላማ 6 የመጻሕፍቱን መሪ ሐሳብ የሚያሳዩ ዘትንቢት መጻሕፍት ውስጥ ያሉትን ጥቅሶች፣ ከሚገኙበት መጽሐፍ ጋር ለማዛመድ።

ለሰሜኑ መንግሥት የተናገሩ ነቢያትና መልእክታቸው

በ722 ዓ.ዓ. የሰሜኑ መንግሥት በአሦራውያን እጅ ከመማረኩ በፊት ያገለገሉ ነቢያት ዮናስ፣ አሞጽና ሚክያስ ሲሆኑ፣ በተጨማሪም ኤልያስ፣ ኤልሳዕ፣ አኪያ፣ እዩ ሚክያስና አዳ ይገኙበታል። እያንዳንዱ ነቢይ ከጌታ የተሰጠው የየራሱ አገልግሎት ነበረው። ኤልያስና ኤልሳዕ ብዙ ተአምራቶች እደርገዋል (1ነገ 17፣ 2ነገ 4)። ዮናስ የውጭ አገር ከተማ ወደ ነበረችው ወደ ኒነዌ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲያስጠነቅቃቸው ተልኳል (ዮናስ 1-4)።

(11). ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ካነበብህ በኋላ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ በማለፈርና የነቢዩን ስም በመጥቀስ ያደረገው ምን እንደሆነ አጭር ገለጻ ስጥ።

ሀ. 1ነገ 14:1-17 ሐ. 1ነገ 18:20-39 ሠ. 2ዜና 28:9-11
ለ. 1ነገ 16:1-7 መ. 2ነገ 5:9-16

መልእክታቸውን በጻሐፍ ባስተላለፉት ነብያት እግዚአብሔር ለሰሜኑ መንግሥት የሰጠው መልእክት የሚከተሉት ናቸው።

ትንቢተ ሆሴዕ

ሆሴዕ ኃጢአተኛና አመንዝራ ለነበረችው ሚስቱ ያሳየው ፍቅርና ይቅርታ፣ እግዚአብሔር ለኃጢአተኛዋ እስራኤል ያለውን ፍቅርና ይቅርታ ያሳያል። በሆሴዕ ምዕራፍ 1-3 ያለው የሆሴዕን የግል ሕይወት ልምምድ የሚናገር ሲሆን፣ በእግዚአብሔር ላይ በመንፈሳዊ ግልሙትና ውስጥ ባለችው በእስራኤል መካከል የሚካሄደውን ነገር ያመለክታል። ከሆሴዕ ምዕራፍ 4-14 ያለውም ይህንኑ የእግዚአብሔርንና የእስራኤልን ግንኙነት በተብራራ መንገድ የሚገልጽ ነው (ሆሴዕ 1-14 እንብብ)።

ትንቢተ አሞጽ

የአሞጽ ስብከት ለአገራቱ ኃጢአት ሕዝቡ ተጠያቂነት እንዳለው የሚያስጠነቅቅ ነው። በእስራኤል ዙሪያ ያሉ የእሕዛብ አገሮችም ለአገራቸው ኃጢአት የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ተንግሮአቸዋል። እስራኤል ግን ብርሃን የበራላት አገር ሆና ሳለ ይህን በመፈጸሟ ፍርዷ የባሰ እንደሚሆን ተንግሮአታል (አሞጽ 1-9 እንብብ)።

ትንቢተ ሚክያስ

ሚክያስ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ፣ ስለ ተስፋና ስለሚመጣው በረከት ለሰሜኑም፣ ለደቡቡም መንግሥት የተነበየ ሰው ነበር። ሚክያስ ምዕራፍ 1-3 የጨለመ ሁኔታን ይናገራል። ሚክ 4-5 ስለ ብሩህ ቀን ያወሳል። ምዕራፍ 6 ስለ ተጨማሪ ፍርድ ያሳስባል። ከምዕራፍ 7:7 ጀምሮ ለእስራኤል የወደፊት ብሩህ ተስፋ ያበስራል (ሚክ 1-7 እንብብ)።

(12). ከታች ስለተጠቀሱት ነቢያት የሚናገረውንና የቀረበውን ምንባብ አንብብ። ከዚያም እያንዳንዱን ነቢይ ስለመልዕክቱ፣ ወይም ስለተጣራው ከሚናገረው ጋር አዛምድ።

1. አኪያ 1ነገ 14:1-18
2. ሕልዳና 2ነገ 22:12-20
3. ሸማያ 2ዜና 12:5-8
4. ኤል 1ነገ 18:20-39

____ሀ. ከዘጣል ነቢያት ጋር ታጣሙ አሸነፈ።

___ለ. የግብጽ ንጉሥ ሺሻቅ ይሁዳን እንደሚወጋ ትንቢት ተናገረ።
___ሐ. የኢዮርብዓምን ሚስት በትክክል ለይቶ አወቃት።
___መ. በኢየሩሳሌም ላይ የሚመጣውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ኢዮስያስ እንደማያይ ተናገረ።

ለደቡብ መንግሥት የተናገሩ ነቢያትና መልእክታቸው

በነብያትነት አገልግሎት በደቡብ ክፍል ያገለገሉና መልእክታቸውን በጽሑፍ ያስተላለፉ ነቢያት አብድዩ፣ ኢዩኤል፣ ኢሳይያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስና ኤርሚያስ ናቸው። በተጨማሪም ሸማያ፣ አዶ፣ አዛርያስ፣ አናኒ፣ አልአዛርና ሕልዳና ነበሩ።

ኢዩኤል

አገሪቱ በአንበጣ መንጋ እንደምትመረርና በአሰቃቂ ድርቅ እንደምትመታ አስፈሪ መልእክት ለሕዝቡ ይናገራል። ይህ መቅሰፍት በጾምና በጸሎት በመገሥጽም ትንቢቱ በምሳሌነት በአገሮች ሁሉ ስለሚመጣው ከባድና የፍጻሜ ፍርድ ያመለክታል። ታማኞች ብድራትን ሲቀበሉ ክፋ አድራጊዎች ደግሞ ቅጣት ይጠብቃቸዋል (ኢዩ 1-3 እንብብ)።

ኢሳይያስ

ኢሳይያስ በንጉሥ ሕዝቅያስ ዘመን የነበረ የተከበረ ሰውና ነቢይ ነበር። እርሱም ለመሪዎች የማስጠንቀቂያ፣ የማጽናኛና የምክር ቃል አስተላልፎአል፣ ስለይሁዳ መንግሥት መውደቅና ስለምርኮ ተንብዮአል፣ ሆኖም ግን ስለ አዲስ መንግሥት መቋቋም ብሩህ ተስፋንም አብስሮአቸዋል። ስለመሢሁ መከራና ክብርም አስቀድሞ ተናግሮአል (ኢሳ 1፣ 6-7፣ 39-44፣ 52-66 ያለውን እንብብ)።

ሚክያስ

ሚክያስ ለሁለቱም መንግሥታት ትንቢት ተናግሮአል። ቀደም ባለው ክፍል ስለመልዕክቱ የተጻፈውን እንደገና ተመልከት።

(13). ኢሳ 43:5-7 ከሚክ 4:6-7 አነጻጽር። በእነዚህ ሁለት ትንቢቶች እግዚአብሔር የተናገረው

ሀ. እስራኤልን በየአገሩ እንደሚበትን ነው።
ለ. ሕዝቡን ከየአገሩ እንደሚሰበስብ ነው።
ሐ. በሕዝቡ ላይ በመፍረድ እንደሚቀጣቸው ነው።

ናሆም

የናሆም ትንቢት ያተኮረው በአሶር መንግሥት ላይ ነው። አሶር ይሁዳን ለሠመናት ጨቁኖአል። ናሆምም የአሶር መዲና የሆነችው ነነዌ ስለሚጠብቃት መደምሰስ ትንቢት፣ ገለጻና ማብራሪያ ሰጥቶአል (ናሆም 1-3 አንብብ)።

ሶፎንያስ

ስለ ጌታ ቀን የሚናገር ትንቢት ነው። ይህ ቀን በዓልን ላመለኩና ለተከተሉ ሁሉ ጥፋትን ያዘለ ሲሆን፣ (ሶፎንያስ ምዕራፍ 1) ለእውነተኞቹ የእግዚአብሔር ቅሬታዎች ግን መንጻትንና በረከትን የሚቀበሉበት ቀን እንደሚሆን ይናገራል (ስፎ 1-3 አንብብ)።

ኤርምያስ

"ባለ እንባው ነቢይ" ተብሎ ይጠራል። ከካህናት ቤተሰብ ሊሆን ለነቢይነት የተጠራው ገና ልጅ ሆኖ ነው። ለሃሻሽ ምዕተ ዓመት ያህል የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ የታመነ በመሆኑ በዚህ አገልግሎት ንቀት፣ ፍርሃት፣ ጥላቻና ስደት ተፈራርቀውበታል። የኢየሩሳሌምን መናረስና የስባውን ዓመት ምርኮ በመተንበዩም እንደ ከሀዲ ተቆጥሮ የሞከሰ ድርጊቶች ተፈጽመውበታል (ኤር 1-9፣ 18-19፣ 36-39፣ 52 አንብብ)።

ሰቆቃው ኤርምያስ

ይህ ስለ ኢየሩሳሌምና ስለ መቅደሱ መናረስ እንደዚሁም ስለሕዝቡ መማረክ በቅኔ መልክ የተነገረ የኤርምያስ ቃል ነው (ሰቆ 1-5 አንብብ)።

ዕንባቆም

የመልእክቱ ዋነኛ ጭብጥ ያሸንፋል የሚል ነው። ይሁዳ በክፉዎቹ ባቢሎናውያን እጅ ትቀጣለች። ሆኖም ግን ባቢሎንም በተራዋ የፍርድ ጽዋን ትቀምሳለች (ዕንባ 1-3 አንብብ)።

አብድዩ

የእግዚአብሔርን ሕዝብ ስላስቃዩ፣ የኤዶሚያስ ሰዎች ይቀጣሉ። እስራኤል ግን በረከት ትቀበላለች (አብድ 17 አንብብ)።

(14). በተሰጠው ስፍራ ቁጥሩን በማስገባት አብሮ የሚሄደውን አመልክት።

1. ኢሳይያስ
2. ኤርምያስ
3. ሆሴዕ
4. ኢዩኤል

___ሀ. ወደ ሌሎች አማልዕክት ዘወር ቢሉም . . . እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን እንደወደዳቸው አንተም እርሷን ውደዳት።
___ለ. የአንበሳ መንጋ ምድራችንን ወሯል። ኃይለኛና ለቁጥር የበዙ ናቸው።
___ሐ. ነገር ግን እርሱ ስለመተላለፋችን ተወጋ፣ ስለበደላችንም ደቀቀ።
___መ. ውብና ሽመንመኑን የሆነችውን፣ የጽዮንን (ኢየሩሳሌም) ሴት ልጅ አጠፋታለሁ።
___ሠ. ለመንግሥቱ ስፋት፣ ለሰላሙም ብዛት ዳርቻ ፣ለውም።

ስለ ተከፈለው መንገሥት ያደረግነው ጥናት የእግዚአብሔርን ሕዝብ መሞረድ አሳይቶናል። በመጨረሻም ነቢያት እንደ አስጠነቀቁት መጀመሪያ እስራኤል ቀጥሎም ይሁዳ በምርኮ ተወስደዋል። ሆኖም እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል የሰላም ንጉሥ ሲነግሥ ብሩህ ተስፋ እንደሚመጣና አሕዛብ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚፈልጉ ተናግሯል (ኢሳ 9፡ 6-7፣ ሚክ 4፡2)።

መከራ ፈተና

1. መንግሥቱ ለሁለት የተከፈለበትን ምክንያት በተሻለ መንገድ የሚገልጸው የትኛው መግለጫ ነው?

ሀ. ነቢዩ አኪያ አሥር ነገዶች ለኢዮርብዓም እንደሚለው በለ ተነበየ።
ለ. ንጉሥ ለሎሞን ሕዝቡን ከባድ ግብር እንዲከፍሉ በላደረገ።
ሐ. ሰለሞን ባዕድ አማልክትን በማምለክ ከእግዚአብሔር ባለራቀ።

2. ፈደሉን በመክበብ እውነተኛ የሆነውን መግለጫ አመልክት።

ሀ. የበሜኔ መንግሥት ከደቡቡ ይልቅ የበለጠ መሬት ነበረው።
ለ. የደቡቡ መንግሥት ሌላው ሰም ኤፍሬም ነበር።
ሐ. የደቡቡ መንግሥት በዳንና በቤቴል የአምልኮ ማዕከሎች ነበሩት።
መ. እሰራኤል የሚለው በም የሰሜኑን መንግሥት ለመጥቀስ ነው።
ሠ. ሁለቱ መንግሥታት ከተከፈሉ በኋላ ምንም ሰምምነት አላደረጉም።

3. ትክክለኛ የሆነውን ፈደሉን በመክበብ አመልክት። የ1ኛ ና የ2ኛ ነገሥት መጻሕፍት

ሀ. የንጉሥ ለሎሞንን ዘመነ መንግሥት ይገልጻለ።
ለ. አብዛኛውን ትኩረት የሚስጡት ለካህናትና ለቤተ መቅደሱ ነው።
ሐ. የ1ኛ እና 2ኛ ዜና መዋዕልን ቅደም ተከተል ይከተላለ።
መ. የኤልያስንና የኤልሳዕን አገልግሎት መዝግበው ይዘዋል።
ሠ. በ1ኛ 2ኛ ዜና መዋዕል ያልተጨመረ የጊዜ ዘመን ይሸፍናል።

4. ቁጥሩን በተሰጠው በፍራ በማስፈር አብሮ የሚሄደውን አመልክት።
1) የሰሜኑ መንግሥት 2) የደቡቡ መንግሥት

___ ሀ. መንግሥቱ መልካምና መጥፎ ነገሥታት የነበሩ ተከታታይ ግዥዎች ነበረው። መንግሥቱ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ586 ፈረሰ፣ ሕዝቡም በምርኮ ወደ ባቢሎን ተወሰደ።
___ለ. ኢዮርብዓም የመንግሥቱ የመጀመሪያ መሪና ለሕዝቡ የጣዖት ማምለኪያ የሰራ ነበረ፣ ንጉሥ አክአብ በነገሰበት ዘመን ነቢዩ ኤልሳዕ ለዚህ መንግሥት አገልግሎት ነበረው።
___ ሐ. የዚህ መንግሥት 6ቱ ነገሥታት ዙፋኑን ያገኙት በግደያ ሲሆን በዚያ ዘመን ያገለገለውም ነቢዩ ሚክያስ ነበር።

5. የሰሜኑም ሆነ የደቡቡን መንግሥት መፈራረስ በተሻለ መንገድ የሚገልጸው የትኛው ነው?

ሀ. በማይታዘዙት ላይ እግዚአብሔር ፍርደ እንደሚያመጣ ነብያት አስታወቁ።

ለ. የአካባቢው አገሮች ጠንካራና ብርቱ በመሆናቸው አስራኤልንና ይሁዳን ለመግረዝ ቻሉ።
ሐ. ሕዝቡና አብዛኛዎቹ ነገሥታት እግዚአብሔርን በታማኝነት አልተከተሉም።

6. በለ ተከፈለው መንግሥት ነብያትና ስለ መልእክታቸው እውነት የሆነውን መግለጫ ፈደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ. የነቢያቱ መልእክት የወደፊቱን የእሰራኤልንና የይሁዳን ሁኔታ የሚመለከት በመሆኑ ዛሬ ለእኛ ምንም የሚጠቅም አይደለም።
ለ. በአንዳንድ ትንቢቶች ወደፊት ስለሚፈጸመው ሲናገሩ እንደ ማብራሪያ የተጠቀሙት ተፈጥሮአዊ ድርጊቶችን ነበር።
ሐ. ነብያት ሕዝቡን እንዲያገለግሉ የተጠሩት በእግዚአብሔር በለሆነ ለውጭ አገሮች ማንኛቸውም መልእክት አልተሰጣቸውም።
መ. ከዘለቱ የነቢይ ኃላፊነቶች አንደኛው የሚቀጥለው ንጉሥ የሚሆነውን ሰው መምረጥ ነበር።
ሠ. የነቢያትን መልእክት ብዙ ጊዜ ለእለት ሕይወታችን ልንጠቀምበት የምንችለው ትክክል ስለሆነውና ስላልሆነው መመሪያዎችን ስለያዘ ነው።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. ሀ. ሰሎሞን ጌታን እንቢ ማለቱ፣ ሌሎች አማልክትን ማምለኩ፣ የጌታን ትዕዛዝ አለመጠበቁ (ወይም ተመሳሳይ መልስ)።
ለ. አሥር ነገዶች ለኢዮርብዓም ይሰግዳሉ። እንዱ ከሰሎሞን ልጅ ጋር ይቆይል (ይሁዳና ቢኒያም የተቆጠሩት እንደ አንድ ነበር)።

9. ባዕዳን ሰዎች በብላቸውን እንደሚወስዱና እንደሚያበጫንቋቸው ተናገረ። እነርሱና ንቱው ምርኮኛ ሆነው ወደ ባዕድ አገር በመወሰድ ሣያታትን ያገለግላሉ።

2. ሐ

3. ሀ. 1) ምክንያት መ. 1) ምክንያት
ለ. 2) ውጤት ሠ. 2) ውጤት
ሐ. 2) ውጤት

10. ሀ. 1) ወደፊት የሚፈጸሙ ድርጊቶች
ለ. 2) ትክክል ለሆነና ላልሆኑ መመሪያዎች
ሐ. 2) ትክክል ለሆነና ላልሆኑ መመሪያዎች
መ. 1) ወደፊት የሚፈጸሙ ድርጊቶች
ሠ. 2) ትክክል ለሆኑና ላልሆኑ መመሪያዎች

4. የሁለት ኮርማዎች ምስል ከወርቅ አሰራ። ሕዝቡ እንዲያመልክባቸው አንዱን በዳን አንዱን ደግሞ በቤቴል አኖረ (ወይም ተመሳሳይ መልስ)።

11. ሀ. አኪያ፣ ለኢዮርብዓም ሚስት ልጁ እንደሚሞት መልእክት አስተላለፈ፣ በኋላም ልጁ ሞተ።
ለ. ኢዩ፣ እርሱና ቤተሰቡ በንጠአታቸው ምክንያት እንደሚጠፉ ለባአል መልእክት አስተላለፈ።
ሐ. ኤልያስ፣ መሰዊያ ሰርቶ እግዚአብሔር ከሰማይ እሳት እንዲያወርድ ጸለየ። እግዚአብሔርም ፈጴቱን ሰማ።
መ. ኤልሳዕ፣ ንዕማን እንዲፈወስ በዮርዳኖስ ወንዝ እንዲታጠብ ነገረው፣ ንዕማንም በመታዘዝ እንደዚሁ አደረገ። ወዲያውም ተፈወሰ።
ሠ. ያዩ፣ አሥረኞችን ከኢየሩሳሌምና ከደብዳ በመውሰዳቸው የሰሜኑን ሠራዊት ገሰጸ። (መልስዐ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል።)

5. ለ እና ሐ

12. ሀ. 4 ሐ. 1
ለ. 3 መ. 2

6. ሀ. 1) ሰሜን ረ. 2) ደቡብ
ለ. 2) ደቡብ ሰ. 1) ሰሜን
ሐ. 1) ሰሜን ሸ. 2) ደቡብ
መ. 2) ደቡብ ቀ. 2) ደቡብ
ሠ. 1) ሰሜን በ. 1) ሰሜን

13. ለ. ሕዝቡን ከየአዛኑ እንደሚሰበስብ

7. በእግዚአብሔር አመለካከት አስፈላጊውና ዋናው ቁምነገር የሰውየው መንፈሳዊ ሕይወት በመሆኑ ነው። (ከዚህ የሚመሳሰል)

14. ሀ. 3) ሆሴዕ 3፡1 መ. 2) ኤር 6፡2
ለ. 4) ኢዮኤል 1፡6 ሠ. 1) ኢሳ 9፡7
ሐ. 1) ኢሳ 53፡5

8. ሀ. እውነት ሠ. ሐሰት
ለ. ሐሰት ረ. እውነት
ሐ. ሐሰት ሰ. ሐሰት
መ. እውነት

9
ትምህርት

ቅጣትና ምርኮ

ባለፈው ክፍለ ትምህርት በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት መጨረሻ አካባቢ በበረከትና በብልጽግና ዘመናቸው ሕዝቡ ግድየለሽ በመሆን ወደ ባዕድ አምልኮ በመመለሳቸው እግዚአብሔር ፍርድ እንደላከባቸው ተመልክተናል። በዚህ ክፍለ ትምህርት ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝብ በንጠአታቸው ምክንያት ውርደት ደርሶባቸው ምርኮኞች በመሆን በባዕድ አገር ለብዙ ዓመታት እንደተንከራተቱ እንመለከታለን።

የሕዝቡ መማረክ እግዚአብሔርን እጅግ አሳዝኖታል። እግዚአብሔር ስሕዝቡ እቅድና ዓላማ ስለአለው በአንድ የእምነት ሰው አማካኝነት ታላቅ ሕዝብ ወደ መሆን እድርሶአቸው ነበር። ሕዝቡ እርስ በእርስ ከመከፋፈላቸውም በተጨማሪ ከንጠአታቸው የተነሳ ትልቅ ጥፋት እንዲደርስባቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነ። እግዚአብሔር የሚወደ ውንና እንደልጁ የተቀበለውን ይቀጣል (ዕብ 12፡6)። እኛ ከንጠአታችን እንመለስ ዘንድ እግዚአብሔር ይቀጣናል። ደህም አድራጎቱ ከፍተር የመነጨ ነው። ከእርሱ የሚያፈገፍጉትን ወደ ሕብረት ለመጥራት እግዚአብሔር ፈተናዎችን ይጠቀማል። የእስራኤል ሕዝብ ከገጠማቸው ከባድ ልምምድ ብዙ ትምህርት ቀስመው እንደተመለሱ ከትምህርታችን እንገነዘባለን።

የቅጣቱንና የምርኮውን ዘመን ታሪክ ስታጠና እንዚህ ሰዎች ካለፉበት መንገድ የተማሩትን መፈራ ትምህርት ታስተውላለህ። እነዚህ ትምህርቶች ከእግዚአብሔር ጋር ላላቸው ግንኙነት ትልቅና ዘላቂ ትምህርት ሰጥታቸዋል። በዚህ ውስዋ አንተም በሕይወትህ የምትለማመደው ትልቅ ትምህርት ታገኛለህ።

የትምህርቱ አከፋፈል

- የፍርድ በትር

  የሰሜኑ መንግሥት መውደቅ
  የደቡቡ መንግሥት መውደቅ
- የምርኮ ዘመን ልምምድ

  ስለ ምርኮው ማብራሪያ
  የምርኮ ዘመን መሪዎች
  የምርኮው ውጤት

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ያዘን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- በሰሜኑና በደቡቡ መንግሥት ላይ የመጣውን ፍርድ መግለጽ።
- በፍርድና በምርኮ ዘመን እግዚአብሔር ከሕዝቡ መካከል ያስነሳቸውን መሪዎችና ነቢያት መግለጽ።
- በምርኮው ምክንያት የእግዚአብሔር ሕዝብ የተቀበሉትን ጥቅሞች መዘርዘር።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች


1. የትምህርቱን ዝርዝር በሚገባ ካጠናህ በኋላ ጥያቄዎቹን በሙሉ መልስ።
2. የመኸሬ ፈተናውን በመጽሐፍህ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸውን ጥያቄዎች አስተካክል።

የትምህርቱ ዝርዝር

ፍርድና በትር

ዓላማ 1 የሰሜኑና የደቡቡ መንግሥት በመደቀ ጊዜና ከመውደቁ በፊት የተፈጸሙትን ድርጊቶች በቅደም ተከተል ለመዘርዘር።

እግዚአብሔር በንጉሶቹ በኩል ለሕዝቡ ስለአስተላለፋቸው ማስጠንቀቂያዎች እንደተረዳነው፣ የእነዚህ ማስጠንቀቂያዎች ዋነኛ መልእክት ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ አለመገኘት ጥፋትን እንደሚያስከትል የሚገልጹ ነበሩ። እግዚአብሔር ታጋሽ ስለሆነ ቅጣቱን ሊያዘገይ ይችላል፣ ሆኖም ግን ምንም ጊዜ ቢሆን ንጠአትን ሳያቀጣ አያቀውም። እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማዳን ሞክሮ ነበር፤ እነርሱ ግን አልሰሙትም። አንዳንድ ጊዜ ውጫዊ የሆነ ለውጥ ለማሳየት ቢሞክሩም ውስጣዊ ለውጥ ወይም ተሃድሶ አያታይባቸውም ነበር። በዚህ ሁሉ የጨለማ ቁዎ ግን የእግዚአብሔር አመራር ለሕዝቡ ካለው ዓላማና እቅድ አንጻር ስለሆነ፣ ሕዝቡን ቀጥቶ አንጻቸው እንጂ ጨርሶ አላጠፋቸውም።



የሰሜኑ መንግሥት መውደቅ

የእስራኤል ሕዝብ በሦስት ንያላን መንግሥታት የተከፈለ ነበር። እነርሱም ግብፅ፣ ባቢሎንና አሶር ነበሩ። እነዚህ አገሮች ዓለምን በቁጥጥራቸው ሥር

ሰማድረግ በመካከላቸው የወራሪነት ፋክክር ነበረባቸው። ይሁዳና እስራኤልም በመካከል ሆነው በመዳፋቸው እንዳሉ ይመስላሉ። በእግዚአብሔር ታምነው በሚመላለሱበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከነዚህ ኃያላን መንግሥታት ይታደጋቸዋል። እግዚአብሔርን በሚተዉ ጊዜ ግን እነዚህን ኃያላን መንግሥታት በመጀመሪያ ሰማስጠንቀቂያ በመጨረሻም በሕዝቡ ላይ ፍርድ ሰማምጣት ይጠቀምባቸው ነበር።

የእስራኤል መንግሥት ንጉሥ አክአብ በነገሠ በ16ኛው ዓመት በአሶር አንድ ታላቅ ንጉሥ ተነሣ። እርሱም ሳልማኒ ስልምናሶር ይባል ነበር። መንግሥቱን የሚስፋፋት ምኞት ስሰ ነበረው የእስራኤልን ድንበሮች አልፎ አልፎ ይዋስ ነበር። ይሁን እንጂ በአሶር መንግሥት ውስጥ የርስ በርስ ችግር ስሰተከሰተ የወረራቸውን ሥፍራዎች ከመሞቱ በፊት መልሶ አጣ። ከእርሱ ቀጥሎ የተነሡት የአሶር ነገሥታት ሳልማኒ ቼልጌልቼልፌልሶር፣ ስልምናሶር 5ኛ፣ እና ዳግማዊ ሳርጎን አሶርን በወታደራዊ ኃይልና በኢኮኖሚ ገናና አደረጉዋት። ይህ ዕድገት 40 ዓመት የፈጀ ሲሆን እስራኤልም በዚህ ጊዜ የአሶር ቅኝ ግዛት ሆና መገበር ጀመረች። ሆሴዕ፣ አሞጽና ኢሳይያስ የተባሱት ነቢያት ይህ እንደሚሆን አስቀመው አስጠንቅቀው ነበር። ሆኖም እስራኤል በኃጢአቷ ስሰቀጠሰች የተባሰው ሁሉ ደረሰባት (2ነገ 17:1-18)።

(1). 2ነገ 17:1-18 ካነበብህ በኋላ በሰሜኑ መንግሥት ላይ ፍርድ የመጣበትን ምክንያት በደብተርህ ላይ አስፍር።

የሰሜኑ መንግሥት የተዘረዘሩትን ኃጢአቶች በማድረግ ብቻ ሳያበቃ የነቢያትን መልእክት ችላ በማሰት በድሰዋል። የነብያትን መልእክት ችላ ባይሱ ኖሮ እግዚአብሔር በታደጋቸው ነበር። ከመሪዎቹ ትዕቢት የተነሳና እውነተኛ ንስሐ ስላሳሳየች እግዚአብሔር እስራኤልን ሰአሶር አሳልፎ ሰጣት። የሰሜኑ መንግሥት መጻና የነበረችው ሰማሪያ ሰአምስት ዓመት ከተወረረች በኋላ በ722 ዓ.ዓ. በአሶር ንጉሥ ዳግማዊ ሳርጎን እጅ ወደቀች። የሰሜኑን መንግሥት ነዋሪዎች ወደ ሌላ አገር አፈሰሳቸው። በሰማሪያም የሌላ አገር ምርኮኞችን አምጥቶ የእግዚአብሔር ሕዝብ በነበሩበት ስፍራ አሰፈራቸው (2ነገ 17: 24)። በአዲስ ኪዳን በመን በዮሐንስ 4 የነበሩት ሳምራዊያንም ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ የእነዚህ ነገዶች ዘር ናቸው።

አሥሩ ነገዶች ወዴት እንደተወሰዱ ብናውቅም፣ ከዚያ በኋላ መጨረሻቸው ምን እንደሆነ አያታወቅም። ወደ አገራቸውም አልተመለሱም፣ በታሪክ ምዕራፍም ተጽፈው አናገኛቸውም። ይሁን እንጂ የመጀመሪያው የሰሜን ንጉሥ ኢዮርብዓም ጣዖታትን አቁሞ ባስተዋወቀ ጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሁሉ ከየነገዱ ወደ ይሁዳ፣ ወደ ይሁዳ እንደሄዱና እንደሰፈሩ መዘንጋት የሰብንም። የሰሜኑ መንግሥት አባል የሆኑ አንዳንድ ግለሰቦች ከምርኮ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሳይመለሱ እንዳልቀሩ ይገመታል።

(2). የሰሜኑን መንግሥት መውደቅ ድርጊቶች በቅደም ተከተል አስፍር። በመጀመሪያ ሰተፈጸመው ድርጊት ቁጥር 1 ከዚያም ቀጥሎ ለተፈጸመው ድርጊት ቁጥር 2 በመጻፍ በቅደም ተከተል አስፍር።

____ሀ. ስልምናሶር 3ኛ የአሶርን መንግሥት አስፋፋ።
____ሰ. አሥሩ ነገዶች ወደ አሶር ተወሰዱ።
____ሐ. አሶር በወታደራዊ ኃይልና በሃብት ገናና ሆነች።
____መ. ዳግማዊ ሳርጎን ሰማርያን ማረከ።
____ሠ. ሰማርያ ሰአምስት ዓመታት ተወረረች።

የደቡቡ መንግሥት መውደቅ

የሰሜኑ መንግሥት መውደቅ ለይሁዳ ማስጠንቀቂያና መልእክት ያዘሰ ነበር። የእግዚአብሔር ጥበቃና ሌሎችም የተሰያዩ ምክንያቶች ታክለው ይሁዳ በዚህ ጊዜ በኃያሏ የአሶር መንግሥት እጅ አልወደቀችም (2ነገ 19:32-36፣ ኢሳ 36-37)።

(3). 2ነገ 19:32-36፣ ኢሳ 36-37 ካነበብህ በኋላ እግዚአብሔር ይሁዳን በአሶራውያን እጅ ከመውደቅ እንዴት እንደጠበቃት ግሰጽ።

ከጊዜ በኋላ የአሶር መንግሥት ራሱ በገናናው በባቢሎን መንግሥት እጅ ወደቀ። ነቢዩ ናሆም ይህን አስቀሞ ተናግሮ ነበር። የአሶር መዲና የነበረችውና ዮናስ የሰበከባት ከተማ ነነዌ በ612 ዓ.ዓ. በባቢሎን ተደመሰሰች። የአሶርን ምዕራባዊ ክፍል ሰመቆጣጠር በግብፅና በባቢሎን መካከል ፋክክር ይካሔድ ነበር። በዚህ አጋጣሚም ይሁዳ ከባቢሎን ወራሪነት ሰጊዜው ተርፋ በፀጥታ ኖረች። በዚሁ ጊዜ እንደ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆምና ሶፎንያስ ያሉ ነብያት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የእግዚአብሔርን መልእክት ያስተላልፉ ነበር። ባቢሎንም ገናናነቷን ይዛ ኖረች። አልፎ አልፎ መንፈሳዊ መነቃቃት ቢታይም ይሁዳ ልባዊ የሆነ ንስሐ አላሳየችም፣ በመጨረሻም እግዚአብሔር እስራኤልን ሰመቅጣት አሶርን እንደተጠቀመ፣ ይሁዳን ሰመቅጣት ደግሞ በባቢሎንን ተጠቀመ። ነብዩ ኢሳይያስና ኤርምያስም የምርኩውን ምክንያት በዝርዝር አስተምጠውታል። ይሁዳ ከባቢሎን ጋር የ20 ዓመት ትግል ካካሄደች በኋላ በመጨረሻ ምርኮው በሚከተሱት ሦስት ደረጃዎች ተከናወነ።

1. 605 ዓ.ዓ ናቡከደነጸር ንጉሡን ኢዮአቄምን መሳፍንቱንና መኳንንቱን ማርኮ ወሰደ። ዳንኤልና ባልንጀሮቹም የተወሰዱት በዚህ ጊዜ ነበር። ይህ አንዳንድ ጊዜ የመጀመሪያ ምርኮ ተብሱ ይጠራል (2ዜና 36:5-6፣ ዳን 1:1-6)።

2. 598 ዓ.ዓ ናቡከደናጸር ንጉሡን ዮአኪንና አሥር ሺህ የሚሆኑ ዜጎችን ወደ ባቢሎን ማርኮ ወሰደ። ነቢዩ ሕዝቅኤልና የአስቴር አጎት የመርዶክዮስ ቅድማያት የተወሰዱትም በዚሁ ጊዜ ነበር (2ነገ 24:14-16)

3. 586 ዓ.ዓ ኢየሩሳሌምና መቅደሱ ተቃጥለው ወደመ። የቀሩትም ሰዎች አብዛኛዎቹ ወደ ባቢሎን በምርኮ ተወሰዱ (2ነገ 25:7-9)።

የደቡቡ መንግሥት ከሰሜኑ ይልቅ የተሻለ ዕድል ነበረው። በመከራና በሰደት ቢቀጡም ቅሉ ወደ አገራቸው ለመመለስና ኢየሩሳሌምን መልሶ ለመገንባት ዕድል እጋጥሞአቸዋል። ይሁን እንጂ በዳዊትና በሰለሞን ዘመን የነበራቸው ክብርና ሥልጣን እልተመለሰም። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ተመልሶ መጨረሻ የሌለውን ግናና መንግሥት እስኪመሠርት ድረስም የእስራኤል ክብርና ሞገስ አይመለስም (ራዕይ 11:15)።

(4). የደቡቡን መንግሥት አወዳደቅ ድርጊቶች በቅደም ተከተል አስፍር። በመጀመሪያ ለተፈጸመ ድርጊት 1 ቁጥር በመጻፍ፣ ቀጥሎም ለተፈጸመው 2 ቁጥር በመጻፍ በቅደም ተከተል አመልክት።

_____ሀ. ዳንኤልና ጓደኞቹ ወደ ባቢሎን ተወሰዱ።
_____ለ. ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደሱ ተቃጥለው ወደመ።
_____ሐ. የሰሜኑ መንግሥት መውደቅ ለደቡቡ መንግሥት ማስጠንቀቂያ ነበር።
_____መ. ንጉሥ ዮአኪንና ሕዝቅኤል ተማርከው ወደ ባቢሎን ተወሰዱ።
_____ሠ. ነነዌ በባቢሎናውያን እጅ ወደቀች።

የምርኮ ዘመን ልምምድ

ዓላማ 2 የምርኮውን ሁኔታ ለመግለጽና በዚሁ ወቅት እግዚአብሔር ያስነሳቸውን መሪዎችና የእግዚአብሔር ሕዝብም ከዚሁ የተማሩትን ትምህርቶች ለማስረዳት።

የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መፍረስና የመቅደሱ መቃጠል ለአንዳን መንፈሳውያን አይሁዶች የዓለም ፍጻሜ ሳያመለክቸው አልቀረም። የተሰፋቸው ሁሉ ማክተሚያ፣ የክፉዎች ድል ማብሰሪያ ነበረ የሆነባቸው። እግዚአብሔርም የተዋቸው ሳይመስላቸው አልቀረም። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ሕዝቡን አልተዋቸውም ነበር።

ስለ ምርኮው ማብራሪያ

የባቢሎናውያንን ምርኮ ሁኔታ የሚጠቅሱ አራት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አሉ። እነርሱም መጽሐፈ አስቴር፣ ትንቢት ኤርምያስ፣ ትንቢተ ሕዝቅኤልና ትንቢተ ዳንኤል ናቸው። በምርኮው ዘመን ስለተካሄዱት ነገሮች ለማወቅ እንድንችል የሚረዱን እነዚህ መጻሕፍት ናቸው።

የእይሁድ ምርኮኞች በባቢሎን ግዛት በተለያዩ መንደሮች ሰፍረው ነበር። አንድ ቡድን ሕዝቅኤልም ጭምር በኬባር ወንዝ አጠገብ ሰፈሩ (ሕዝ 1:1)። ሌሎች ደግሞ በትላልቅ ከተሞች፣ በባቢሎን ከተማ ሳይቀር ሕብረት

ፈጥረው በጋርዮሽ ይኖሩ ነበር። የእይሁድ ምርኮኞች ያገቡና ይጋቡ፣ መሬት ያርሱ፣ ይነግዳሩ ይሠሩ ነበር። ብዙዎቹ ንብረት አፍርተው፣ ቤት መርተው ከአገሪቱ ቤጎች እኩል ባለመብት ሆነው ኖሩ (ኤር. 29: 4-7)።

(5). ኤር 29:4-7 አንብብ። እግዚአብሔር ለምርኮኞቹ ምን እንደነገራቸው አስተውል። እነዚህን ነገሮች እንዲያደርጉ የፈለገው ለምን ይመስልሃል?

ከዳንኤልና ከአስቴር መጽሐፍ እንደምንረዳው እንዳንድ ምርኮኞች በባቢሎንና በፋርስ ግዛት ውስጥ እስከ ከፍተኛ ሥልጣን ድረስ የደረሱ ነበሩ። ይሁን እንጂ ብዙዎች ይህ የምርኮ ኑሮ አላረካቸውም። በዛዕድ አገር ምርኮኞች ስለነበሩ አገራቸው፣ ቤታቸውና መቅደሳቸውም መና ሆኖ ነበር። መዝሙር 137 በዚህ የምርኮ ዘመን የነበረውን የሕዝቡን ስሜት ልብ በሚነካ መንገድ ያቀርበዋል።

(6). መዝ 137 ላይ የተጻፈውን በዝማታና በማስተዋል አንብብ። ምርኮኞቹ ሊረሱት እንደማይችሉ ቃል የገቡት የተለየ ቦታ የትኛው ነው?

የምርኮ ዘመን መሪዎች

በዚህ የምርኮ ዘመን እግዚአብሔር የተበተኑትን ሕዝቦቹን ያለመልእክት አልተዋቸውም። ከመካከላቸው ጠንካራ መሪዎችን አስነሣላቸው። ዳንኤልና ሕዝቅኤል ከነዚህ መሪዎች ውስጥ ይገኙባቸዋል። ሁለቱም ከይሁዳ ተማርከው የሄዱ ነበሩ። ዳንኤል ከመጀመሪያዎቹ ምርኮኞች ጋር ሲወሰድ ሕዝቅኤል የተወሰደው ከሁለተኞቹ ጋር ነበር።

ዳንኤል ወጣት መስፍን ሲሆን፣ በናቡከደነጾር ፊት ወዲያውኑ ተቀባይነት አገኘ። የዳንኤል መጽሐፍ ታሪካዊና ትንቢታዊ ነው። ዳንኤል ስለወደፊት የዓለም መንግሥታት የተነበየ ሲሆን፣ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶችም ጌታ ሆኖ ስለሚነግሰው ስለመሲሁ መከራና ክብርም ተንብዮአል።

(7). ዳን 1:3 እና 9 ካነበብክ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሶች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. ስለመብልና ስለመጠጥ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን ይችል ዘንድ ምን ሃሳብ አቀረበ?
ለ. ናቡከደነጾር ስለ ሕልሙ፣ ጠቢባኑን ሰዎች ዘረተናቸው ጊዜ ዳንኤል በእግዚአብሔር ላይ እምነቱን ያሳየው እንዴት ነበር?
ሐ. የሲድራቅ፣ የሚሳቅና የአብድናጎ ልምምድ ውጤት በእሳት ውስጥ ምን ነበር?

ሕዝቅኤል ወጣት ካህን ነበር። እግዚአብሔር ነቢዩ ሕዝቅኤልን ያስነሣው ሰለሚመጣው ተጨማሪ ፍርድ እንዲመሰክር ነበር። ሕዝቅኤል

አገልግሎቱን ሊጀምር ኢየሩሳሌምና መቅደሱ ገና አልፈረሱም። ለአራት ዓመት ተኩል ስለሚመጣው ፍርድና ቅጣት አወጀ። ከዚያም ኢየሩሳሌም እስክትደመሰስ ድረስ ለሁለት ዓመት ፀጥ አለ። የትንቢቱ መፈጸም ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ለው መሆኑን አስመስክሮለታል። በኋላም ሕዝቅኤል ስለ መሢሁ መምጣትና ስለ እውነተኞች የእግዚአብሔር ሕዝቦች ብሩህ ተስፋ ክእግዚአብሔር ዘንድ ራዕዮችን ለመቀበል የታደለ ሰው ነበር። የሚከተሉትን ምዕራፎች ከሕዝቅኤል መጽሐፍ እንብብ (ሕዝ 3-5፣ 7፣ 11፣ 33፣ 37 እና 47 እንብብ)።

(8). የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. ሕዝ ምዕ 3-5 ላይ በተጻፈው መሠረት እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን መፍረስ መልእክት፣ ሕዝቅኤል ስምርኮኛቹ እንዲያስተላልፍ የፈለገው እንዴት ነበር?

ለ. በሕዝ 37 ላይ በተጻፈው መሠረት ሕዝቡን ወደ ምድራቸው እንደሚመልስ ለማሳየት እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል ምን ራዕይ ሰጠው?

ሐ. ሕዝ 47 እና ራዕ 22፡1-3 አነጻጽር። ሕዝቅኤል ያየው ወንዝ ምን የሚያመለክት ይመስልሃል?

ኤርምያስ በዚህ ዘመን ይጽፍም ይተነብይም ነበር። ትንቢቶቹ ፍጻሜ ስላገኙ በዚህ ወቅት በጣም የተከበረ ሰው ሆነ። በምርኮው ጊዜ በይሁዳ ቀርቶ ነበር። በኋላ ወደ ግብፅ ከሸሹት እስራኤላውያን ጋር ሄደ። በመልእክቱም ከምርኮ ስለመመለስ ተስፋ እየተናገረ ያበረታታቸው ነበር። የምርኮኞቹን ወደ ኢየሩሳሌም መመለስም ተንብዮአል (ኤር ምዕ 29-31፣42፣ 50-52) እንብብ።

አስቴር ሌላዋ በምርኮ ዘመን የነበረች ናት። የባቢሎን መንግሥት በፋርስ ተሸንፎ ነበርና አስቴር የኖረችው በፋርስ መንግሥት ዘመን ሲሆን የፋርስ ንጉሥም አርጤክስስ ነበር። የንግሥትነት ደረጃ ከያዘች በኋላ ለእግዚአብሔር በነበራት መታዘዝና ድፍረት በዚያን ዘመን የነበሩትን አያሁድ ከጥፋት አድናለች። የእርሷ ታሪክ እንደ ሩት ታሪክ እግዚአብሔር ለሀገሩ ያለውን እንክብካቤ ያሳያል።

(9). አስቴር ምዕ 1-10 እንብብ። በተለይም በምዕ 4፡12-14 የተጻፈውን ልብ ብለህ አስተውል። የእንተን ሁኔታ ከአስቴር ሁኔታ ጋር ማንጻጸር ትችላለህ? ከአስቴር ልምምድ ለመማር የምትችለውን ትምህርት በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

(10). ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በመጻፍ አብሮ የሚሄደውን አመልክት።
1) ዳንኤል 2) ሕዝቅኤል 3) ኤርምያስ 4) አስቴር

___ሀ. የወደፊቱን የሳለምን መንግሥታት የሚያመለክት ምስል በራዕይ ያየ።
___ለ. በሃማ እቅድ ምክንያት አይሁድን ከሞት ለማዳን የረዳ።

___ሐ. ለአራት ዓመታት ተኩል የኢየሩሳሌምን መውደቅ የሰበከ ካህንና ነቢይ
___መ. በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነጾር መንግሥት ታላቅ ሹም የነበረ።
___ሠ. አይሁዶችን ለመግደል ማቀዱን እንዲያቆም አርጤክስስን የጠየቀች የፋርስ ንግሥት።
___ረ. በባቢሎን በስደት ላይ ለነበሩ ይብዳቤ የላከ።

የምርኮ ውጤት

የምርኮው ዘመን ከባድና መራራ ቢሆንም እንኳን እንዳንድ መልካም ውጤቶች ነበሩት። ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት አምስቱ ይገኙበታል።

1. ከጣዖት አምልኮ መንጻት

ለምርኮ ያበቃቸው ነገር ጣዖትን በማምለክ የመጣባቸው የእግዚአብሔር ቅጣት ነበር። ነገር ግን በምርኮ ዘመን የእግዚአብሔርን ሕልውና በአዲስ መንገድ ተረዱት። የእሶር፣ የባቢሎንና የግብፅ አማልክት ከመንግሥታቸው መውደቅ ጋር አብረው ሲቀሩ የእስራኤል አምላክ ግን እንደ ምንጊዜውም ሕያውና ኃያል ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝብ ትንቢቶቹ ሲፈጸሙ አዩ፣ በረከትን በተለየ መንገድ ተለማመዱ። የተቀበሉት ቅጣት ለመንፈሳዊ ድል ምክንያት ሆኖቸው። ከዚያ በኋላ ስጣዖት አምልኮ የነበራቸው ዝንባሌ አከተመ።

2. አዲስ የአምልኮ ይዘት

በምርኮ አገር የመኖሪያ ድንኳንም ሆነ ቤተ መቅደስ ስለሌለ እስራኤላውያን በእጃቸው ያሉትን ቅዱሳት መጻሕፍት ለማንበብና ለመወያየት መሰብሰብ ጀመሩ። ይህም የአምልኮ ሥፍራ ለነበረው ለምኩራብ መፈጠር ምክንያት ሆነ። በምኩራብም ሰዎችን እርስ በእርስ የሚያቀራርብ ትምህርት ይሰጥ ነበር። መቅደሱ ከተሠራ በኋላ እንኳ ይህ የአምልኮ ሥርዓት በምኩራብ ይካሄድ ነበር። የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእምነታቸው እንዲጠነክሩ የረዳ የምኩራቡ የአምልኮ ሥርዓት ነበር።

3. ስለ እግዚአብሔር የጠለቀ ዕውቀት

ከአገራቸው ተሰደው በሰው አገር ስለነበሩ፣ እግዚአብሔር የሚገኘው በመቅደስና በእስራኤል ብቻ ነው፣ የሚለውን አመለካከት ሰረዙ። ስለ እግዚአብሔር ያላቸው አመለካከት እየሰፋና እየጠለቀ ሄደ። ስለ መሢሁ መምጣት የእግዚአብሔርን መልእክት መቀበል ጀመሩ። እግዚአብሔር ምድርን ሁሉ እንደሚገዛ የተገለጠላቸውና የበለጠ እውን የሆነላቸው በዚህ ጊዜ ነበር።

4. ተአምራታዊ ጥበቃና እንክብካቤ

እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን የህዝቡን ቅሬታ ወደ ኢየሩሳሌም ሰመመለስ እንዲችሉ በተአምር ጠበቃቸው። ብዙ የተማረኩ ሕዝቦች እንደሚሆኑት ሳይሆን እስራኤላውያን በዚህ በምርኮ አገር ተዋልደውና ተውጠው ሳይቀሩ በደህና ተመለሱ (2ነገ 19:31)።

(11). 2 ነገ 1:31 አንብብ። በዚህ ትንቢት ላይ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ

ሀ. ከኢየሩሳሌም ጥፋት የሚተርፉ እንደሚኖሩ።
ለ. የይሁዳ ምርኮኞች ሁሉ ወደ ጽዮን እንደሚመለሱ።
ሐ. ከተማረኩት የበለጠ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚመለሱ።

5. የቅዱሳት መጻሕፍት መጠበቅ

የምርኮው አንዱ ውጤት በእግዚአብሔር ሰዎች የተጻፉት መጻሕፍት መሰባሰባቸውና መጠበቃቸው ነበር። ይህ ዛሬ ለእኛም እጅግ ብዙ በረከት አስገኝቶአል።

(15). የእግዚአብሔር ሕዝብ ከምርኮው ዘመን ሰላገኙት ጥቅም የተሟላ ገለጻ የሚበጠው የትኛው ነው?

ሀ. ከምርኮው በመናት በኋላ እስራኤላውያን በፊት እንዳደረጉት ጣዖታትን አላመለኩም። ምንም እንኳ ኃጢአት መሥራታቸውን ቢቀጥሉም የእስራኤል አምላክ ከእነርሱ ጋር በመሆኑ አልተሸነፉም።
ለ. ምርኮኛ ሆነው ወደ ባዕድ አገር ቢሰደዱም ማንነታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ እግዚአብሔር በተአምር ጠበቃቸው። ይህም ጥበቃ አንድ ቀን ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ እንዲቻል አደረገ።
ሐ. ከጣዖት ማምለክ እንደተመለሱ፣ ስለ እግዚአብሔር የነበራቸው አስተሳሰብ እየሰፋ ሄደ። አዲስ የሆነ የአምልኮ መንገዶች ጀመሩ፣ ወደ ምድራቸውም ይመለሱ በንድ እግዚአብሔር ጥበቃ አደረገላቸው።

ዓመታት እየገፉ ሲሄዱ እስራኤላውያን በቅጣታቸውና በምርኮአቸው ውስጥ የእግዚአብሔር ታላቅ ዓላማ እንዳለበት ተረዱ። ስለ እ ዚአብሔር ታላቅነ ትና እውነተኛ አምላክነት ጥርጣሬአቸውን አስወገዱ። ዋጋ ቢያስከፍላቸውም አስደናቂ የሆነና የማይረሳ መንፈሳዊ ትምህርት ለማግኘት ቻሉ።

የመከራ ፈተና

1. የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ በወረደበት ዓመታት ከነበሩት ሦስት የዓለም ታላላቅ ኃያላን ውስጥ የማይካተተው

   ሀ) ሶርያ ለ) ባቢሎን ሐ) ግብፅ መ) አሦር

2. ራያሉን በመከበብ እውነተኛውን መግለጫ አመልክት።

ሀ. ሰማርያ የተማረከችው በባቢሎን ለ5 ዓመታት ከተከበበች በኋላ ነው።
ለ. ኢየሩሳሌም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ586 በአሦራውያን እጅ ወደቀች።
ሐ. የአሦር ግዛና መንግሥት በባቢሎናውያን ተሸነፈ።

3. የሚከተሉትን ድርጊቶች በቅደም ተከተላቸው አሰቀምጥ። በመጀመሪያ ለተፈጸመው ድርጊት 1፣ ከዚያም ቀጥሎ ለተፈጸመ 2 እያልክ በመጻፍ አመልክት።

___ሀ. ባቢሎን በፋርሶች ተሸነፈች።
___ለ. ኢየሩሳሌም በንቡሥ ናቡከደነጸር እጅ ወደቀች።
___ሐ. ኢየሩሳሌምን በአሦራውያን እጅ እንዳትወደቅ እግዚአብሔር ታደጋት።
___መ. ሰማርያ በዳግማዊ ሳርጎን ተማረከች።
___ሠ. ነቢዩ ሕዝቅኤል በምርኮ ተወሰደ።
___ረ. አስቴር ንጉሥ አርጤክሰስ አይሁዶችን እንዲታደግ አደረገች።

4. ስለ ፍርድና ምርኮ ዓመታት የተሰጡትን መግለጫዎች አንብብ። ከዚያም መግለጫው የሚያመለክተው የምርኮውን ምክንያት፣ የምርኮውን መንገድ ወይም ከምርኮ የተገኘውን ጥቅም ከሆነ ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በመጻፍ አዛምድ።

   1) ምክንያት 2) የፍርድ መንገድ 3) ጥቅም

___ሀ. ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን በመውረር አጠፏት።
___ለ. የሰሜኑ መንግሥት ከወደቀ በኋላ እንኳ የደቡቡ መንግሥት ሙሉ በሙሉ ንሰሐ አልገባም።
___ሐ. በሕዝቡና በመንግሥታቱ መካከል ባዕድ አምልኮ ተስፋፋ።
___መ. አይሁዶች ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት በሚወያዩበት ስፍራ ምኩራብ ተጀመረ።
___ሠ. ሕዝቡ ስለ እግዚአብሔር ኃይልና የበላይነቱ አዲስ ግንዛቤ አገኘ።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. ፍርድ የመጣው ጣዖታትን በማምለክ የክንዓናውያንን ልማድ ተከትለው እግዚአብሔር የማይወደውን በማድረጋቸው ነው።

5. የምርኮው ዘመን ሲያልቅ ወደ ምድራቸው ለመመለስ እንዲችሉ ጠንካራ እንዲሆኑ ስለፈለጉ። (ወይም ተመሳሳይ መልስ)።

2. ሀ. 1 ሐ. 2 ሠ. 3
   ለ. 5 መ. 4

6. ኢየሩሳሌም

7. ሀ. ጤንነት እንደሚያስጎኝ ለማረጋገጥ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለአሥር ቀናት እንዲከተል እንዲፈቀድለት ጠየቀ።
   ለ. ስለ ሕልሙ ለማወቅ ጊዜ በመጠየቅ የሕልሙን ምስጢር እንዲገል ጥሎት ወደ እግዚአብሔር ጸለየ።
   ሐ. ንቱት የእሥራኤል አምላክን አምስኗት። ሕዝቡ ሁሉ ክብር እንዲ ስጡት አዘዘ።

3. የጌታ መልእክ የአሶራውያን ወታደሮችን ገደለ።

8. ሀ. ከበባውን በድርጊት መልክና የተለያዩ ነገሮችን በመጠቀም እንዲያ ሳይ አደረገው።
   ለ. የደረቁ አጥንቶች ሕያዋት ዘርተው ሲነሱ ራዕይ አሳየው።
   ሐ. ሕይወት በመስጠትና በመፈጠስ የእግዚአብሔርን ሀልዎት ሊያመ ለክት ይችላል

4. ሀ. 3 ሐ. 1 ሠ. 2
   ለ. 5 መ. 4

9. አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሞክሶና የሥልጣን ሥፍራ እንድናጥኝ፣ ተስሚነትም እንዲኖረን ያደርጋል። የአስቴርም ሕይወት እንደዚሁ ነበር።

10. ሀ. 1) ዳንኤል
    ለ. 4) አስቴር
    ሐ. 2) ሕዝቅኤል
    መ. 1) ዳንኤል
    ሠ. 4) አስቴር
    ረ. 3) ኤርሚያስ

11. ሀ. ከኢየሩሳሌም ጥፋት የሚተርፉ አለ።

10

ትምህርት

መመለስና መታደስ

ታላቁ ቤተመቅደስ ፈራርሶአል፣ የኢየሩሳሌምም ውበት ደብዝዞአል፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ በባዕድ አገር በምርኮ ውስጥ ቢሆኑም ታሪኩ በዚህ አያከትምም።

እግዚአብሔር መጠገን ሲፈልግ ይቀጣል። የእስራኤላውያን ቅጣት ሊያመልጡት የማይችሉት የኃጢአታቸው ውጤት ቢሆንም ቅሉ እግዚአብሔር ወደ ፊት ላስበላቸው ተስፋና መረማመጃ ስለሆነላቸው ትምህርትና ማስተዋል አግኝተውበታል።

ሰባው ዓመት የምርኮ ዘመን ሲያከትም የእስራኤላውያን ተስፋዎች ይረጃ በደረጃ መፈጸም ጀመሩ። ቃል እንደገባላቸውም እግዚአብሔር ወደ ምድራቸው መለሳቸው። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑ የዘላለም ስለሆነ በጊዜው አዲስ ጅማሬ ሰጣቸው።

እንደ እሥራኤላውያን ሁሉ እኛም በአገልግሎታችንም ሆነ በአንድ በተወሰነ አቅጣጫ፣ በምንኖርበት አካባቢያችንን ለማደስ እግዚአብሔር ለተሐድሶ ሊጠራን ይችላል። ምንም እንኳ አለመታዘዝ ቅጣት ቢያስከትልም፣ ንስሐ ደግሞ ተስፋን ያፋጥናል። ይህንን ሁኔታ በአእምሮአችን በመያንዘብ፣ ድካማችንንም በማወቅና የእርሱን ኃያልነት በመረዳት ጥናታችንን እንቀጥል።

የትምህርቱ አከፋፈል

- የተሀድሶ ዓላማ
- የተሀድሶ ደረጃዎችና እድገት
- ለአዳኖች የተሰጠ መልእክት
- ለሕዝቡ የተሰጠ የመጨረሻ ማበጠንቀቂያ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ምድራቸው ለምን እንደመለሳቸው መግለጽ።
- የተሃድሶውን ሂደት ሦስት ደረጃዎች መዘርዘር።
- ትንቢተ ሐጌ፣ ዘካርያስና ሚልክያስ ያዘሉትን ዋና መልእክት መዘርዘር።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ከመጽሐፈ ዕዝራ፣ ነህምያ፣ ሐጌ፣ ዘካርያስና ሚልክያስ እንድታነብ በክፍለ ትምህርቱ ውስጥ መመሪያ ሲሰጥህ ወዲያው አንብብ።

2. የክፍለ ትምህርቱን ዝርዝር በሚገባ አጥና፣ ለጥናት ማጠናከሪያ የተሰጡትንም ጥያቄዎች መልስ። መልስህንም በመጽሐፉ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት አስተካክል። ከዚያም የመከራ ፈተናውን በመውሰድ እንደዚሁ አድርግ።

የትምህርቱ ዝርዝር

የተሃድሶ ዓላማ

ዓላማ 1 አይሁዶች ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ ለምን እንዳስፈለጋቸው መግለጽ።

እግዚአብሔር በባዕድ አገር ሕዝቡ ሊማሩ የሚገባቸውን ትምህርት እንዲማሩ ካደረገ በኋላ በታላቅ ኪዳኑ መሠረት ወደገዛ ምድራቸው ተመልሰው የፈራረሰውን እንደገና እንዲገነቡ አደረገ። ታላቁ ቤተ መቅደስ ፈርሶአል፣ የኢየሩሳሌም ከተማ ውበት ደብዝዟል የ70 ዓመታት የምርኮ ዘመን ሲያከትም የእስራኤላውያን ተስፋዎች ደረጃ በደረጃ መፈጸም ጀመሩ። ታላቅ በገዛላቸው መሠረት እግዚአብሔር ወደ ምድራቸው መለሳቸው። አዲስ ጅማሬም ሰጣቸው፣ ኃጢአት ቅጣት ቢያስከትልም ንስሐ መግባት ደግሞ አዲስ ጅማሬን ያስገኛል።

እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ስለ ቤተሰቡና ስለ ዘሮቹ ታላቅ ኪዳን እድርጎ ነበር። ይህን ኪዳኑንም ለዳዊት በመድገምና በማደስ ይበልጥ አጠናክሮ ታላቅ እግዚአብሔር ይህን የመሰለ ታላቅ ኪዳን የገባላቸውን ሕዝቦች በዚህ ዓለም መንግሥታት ኃይል ተውጠው እንዲቀሩና እንዲጠፉ አልፈቀደም።

ዓለም በበተምሥራቅ በኩል በነበሩት ኃያላን መንግሥታት ቁጥጥር ሥር የዋለችበት ዘመን አከተመ። ሩርበ የመጨረሻው የምሥራቅ መንግሥት ነበር። ከዚያም በኋላ በምዕራብ በኩል የመጀመሪያው ታላቅ መንግሥት ሆኖ የመቄዶንያ መንግሥት ተነሣ፣ ፋርስንም አሸነፈ። የአይሁድ ሕዝብ በእግዚአብሔር ጥበቃ ሥር ባይሆኑ ኖሮ በአዳዲስ የምዕራብ ኃያላን መነሳት ከመንኮታኮትና ከእልቂት ተርፈው ባልወጡ ነበር። የዓለም ምበክርም ለመሆን ባልበቁም ነበር። ዳሩ ግን እግዚአብሔር በተነሰለኛው ወቅት ሕዝቡን ወደ ምድራቸው መለሳቸው።

እግዚአብሔር ሕዝቡን የዓለም ዋና ዋና ድርጊቶች በሚፈጸምባቸው ማዕከሎች፣ በድሮውና በአዲሱ ሥፍራ መካከል አስቀመጣቸው። አሮጌዎቹ ኃያላን፣ አሶር፣ ባቢሎንና ፋርስ እክትመው፣ አዳዲስ የምዕራብ ኃያላን መታየት ጀመሩ። አይሁድ የምሥራቁን ክፍል ከደመለሰው አሰቃቂ የመርገት ዕልቂት ውስጥ ተርፈው መውጣታቸው ታላቁ የእግዚአብሔር ተአምር ነው። ነቢያት እንደተናገሩት ምድር ሁሉ የእግዚአብሔርን መንፈሳዊ መንግሥት በማወቅ ትሞላለች። ዛሬ እኛም የዚያኑ ትንቢት ፍጻሜ ለማፋጠን የእግዚአብሔር መጣሪያዎች ለመሆን እንችላለን።

(1). ኤር 25:11-12፣29:10 እና ዳን 9:1-19 ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ መልስ።

ሀ. ዳንኤል ያነበበው ምን ነበር?

ለ. ዳንኤል የተናዘዘው ምን ነበር?
ሐ. ዳንኤል የጠየቀው ምን ነበር?

(2). አይሁዶች ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ ለምን እንዳስፈለጋቸው በማስ ታወሻ ደብተርህ ላይ በሁለት ወይም በሦስት ዐረፍተ ነገር ግለጽ።

የተሀድሶ ጸረእየምችና ወድግት

ጠንካራውና ገናናው የባቢሎን መንግሥትና ከተማ በ538 ዓ.ዓ. ከነርሱቶስ ልደት በፊት በሩርስ ንጉሥ በቂሮስ እጅ ወደቀች። ቂሮስ ሌሎችም ብዙ የምሥራቅ አገሮችን ወርሮአል፤ አሁን ደግሞ ተራው የባቢሎን ሆነ። ጥንታዊያን የታሪክ ማህደሮች እንደሚያስረዱት ቂሮስ የአሶርያውያንና የባቢሎናውያን አሠራር ሳይሆን፣ ሌላ የራሱን አሠራር ይከተል ነበር። ይኸውም ምርኮኞቹን ሁሉ ነፃ ማውጣትና ወደ ትውልድ አገራቸው መመለስ ነበር።

የእስራኤልን መመለስና መቋቋም ለማወጅ እግዚአብሔር ቂሮስን ተጠቀመበት። ስለ መቅደሱ መሠራትና መጠገን ቂሮስ ትእዛዝ ሰጠ። አንድ የአሕዛብ ንጉሥ "እግዚአብሔር ምድርን እንድገዛ ሥልጣን" ብሎ ሲናገር አይሁዳውያን ሳያደንቁ አይቀሩም። ለእስራኤል ሕዝብ መመለስና ለምድሪቱ መታደስ መነሻ የሆነው በዕዝራ 1:1-4 ላይ የሚገኘው የቂሮስ አዋጅ ነው።

(3). ቂሮስ ያወጣውን ትዕዛዝ ከዕዝራ 1:1-4 ላይ ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. ቂሮስ እግዚአብሔር ምን ኃላፊነት እንደሰጠው ተናገረ?
ለ. የሩርስን ሕዝብ አይሁዶችን እንዲረዱ የነገራቸው በምን መንገድ ነበር?

የሦስቱ ዙር የግዞት ተመላሾች

ዓላማ 2 አይሁዶች ቤተ መቅደሱንና የኢየሩሳሌምን ከተማ መልሶ ለመገንባት ያደረጉትን ሶስት ዙር ጉዞ ለመግለጽ።

የሕዝቡ መመለስና የጥገናው ሥራ በወቅሳላው 100 ዓመታት ፈጅቶአል። በቂሮስ ይጀመር እንጂ መልሶ የመገንባቱ ሂደት የሌሎችም የሩርስ ንገሥታት እጅ አለበት። በዚህ ጊዜ አይሁዶች ከሩርስ ወደ እስራኤል ሦስት ዙር ጉዞዎችን አድርገዋል። መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ ይህንኑ ታሪክ ይዘረዝራሉ።

	የመጀመሪያው ተመላሽ ቡድን ዕዝራ 1-6 (538 - 536 ዓ.ዓ.)	በ59 ዓመታት ቆይታ ነበር። በዚህ ወቅት የሩርስ ነገሥታት ከሦስቱ ዳርዮስ እና አርጤክስስ	ሁለተኛው ተመላሽ ቡድን ዕዝራ 7-10 (458 -457 ዓ.ዓ.)	ሦስተኛው ተመላሽ ቡድን ነህምያ1-13 (445-444 ዓ.ዓ.)
የነበረው የሩርስ ንጉሥ	ቂሮስ		አርጤክስስ	አርጤክስስ
የአይሁድ መሪ	ዘሩባቤል		ዕዝራ	ነህምያ
የተመላሾች ቁጥር	49,697		1,758	ነህምያና አሻቢ ወታደሮች
የተፈጸሙ ድርጊቶች	መቅደሱ ተጀመረ፣ መሰዊያት ማቅረብና በዓላት መታሰብ ተጀመሩ፣ ቤተ መቅደሱ በ516 ዓ.ዓ አለቀ።		ሕጉና የእምልኮ ሥርዓት መነቀሳቀስ	የፈረሰው ቅጥር ግንብ እንደገና ተሰራ፣ የእግዚአብሔር ሕግ ተነበበ
የገጠማቸው ችግር	የሳምራውያን ተቃውሞ		አይሁዳዊ ካልሆኑ ጋር ጋብቻ መፈጸም	የሰንባላጥ የጦቢያና የጌሹም ተቃውሞ
የነበሩ ነብያት	ሐጌና ዘካርያስ			
የፈጀው ጊዜ	20 ዓመታት 536-516 ዓ.ዓ		25 ዓመታት 457-432 ዓ.ዓ.	

(4). ትክክለኛ የሆነውን መግለጫ ሬደሉን በመክበብ አመልክት፣

ሀ. ቅጥሩ እንደገና የተሰራው በሦስተኛው ዙር የግዞት ተመላሾች ነበር።
ለ. በመጀመሪያው የግዞት ተመላሾች ጊዜ የነበረው የሩርስ ንጉሥ አርጤክ ስስ ነበር።
ሐ. ከመጀመሪያው ይልቅ የበለጠ ሕዝብ የተመለሰው በሁለተኛው ዙር ነበር።
መ. ጦቢያ የቅጥሩን መሰራት ተቃወመ።

የመጀመሪያ ተመላሾች ዕዝራ 1-6 አንብብ

ከዘሩባቤል ጋር የተመለሱት የሰዎች ቁጥር የአባወራዎችን ብቻ የሚጠቅስ ሳይሆን አይቀርም። ይህም ሆኖ በምርኮ አገር ከቀሩት ሰዎች ቁጥር ጋር ሲነጻጸር፣ የተመላሾች ቁጥር በጣም ያነስ ነበር። ብዙዎቹ በምርኮ አገር በልጽገዋል፣ ተደላድለዋልም። ስለሆነም ገና የሚቋቋም አገር ለመገንባት ወደ ፖለቲካና ለመመለስ ጉጉት አልነበራቸውም።

(5). ዕዝራ 1:5 አንብብ። ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት ሁሉ በጋራ የሚያመሳስላቸው ምን ነበር?

ጉዞው አስቸጋሪና አድካሚ ስለ ሆነ አራት ወር ያህል ይፈጃል (ዕዝራ 7:9)። *የመጀመሪያዎቹ* ምርኮኞች እንደተመለሱ ቤተ መቅደሱን መሥራት ጀመሩ። መለዋያው ተጠናቅቆ የመቅደሱም መሠረት ተጣለ (ዕዝራ 3)። የድንጋዮች አቅርቦት እንደልብ ሲሆን እንጨቶች ግን ከሲባኖስ ዳር ማጓጓዝ ያስፈልግ ነበር።

የጠላቶች ተቃውሞ ከፍተኛ ስለነበር የመቅደሱ ጥገና ሰ16 ዓመት ያህል ተቋረጠ (ዕዝራ 4)። በዚህን ጊዜ ሕዝቡን ሰሥራ እንዲያበረታቱ እግዚአብሔር ነቢያቱን ሐጌንና ዘካርያስን አስነሳላቸው። ሕዝቡም የነቢያቱን ማበረታቻ ቃል ተቀብለው በመሥራታቸው ቤተ መቅደሱ በ516 ዓ.ዓ. ተሰርቶ ተመረቀ (ዕዝራ 5-6)።

የሁለተኛ ተመላሾች ዕዝራ 7-10 አንብብ

ጸሐፊውና ካህኑ ዕዝራ ቤተ መቅደሱ ከለቀ ከ60 ዓመት በኋላ ሁለተኛውን ቡድን ከባቢሎን ይዞ እየመራ ኢየሩሳሌም ገባ (ዕዝራ 7)። ዕዝራም አስፈላጊውን ቁሳቁስና ጥበቃ ሰሚሰጥና እንዲረዳው ከንጉሡ ከአርጤክሰስ የተጻፈ የድጋፍ ደብዳቤ ለጎረቤት አገር ባለሥልጣኖች ይዞ መጣ።

ከአሮን ዘር የሆነው ዕዝራ ለዚህ ጉዞው መንፈሳዊ የሆነ ተልእኮ ነበረው። አያሌ ካህናትም ከእርሱ ጋር እንዲጓዙ አደረገ። ዕዝራ በደረሰ ጊዜ በኢየሩሳሌም የሰፈሩት ሰዎች የአምልኮ ሥርዓትና ድርጊት የሚያስነቅፍ ስለነበረ ልቡ በጣም አዘነ። እነዚህን ነቀፋዎች ሁሉ በማስቆም ብዙ ተሃድሶዎችን አከናወነ። የዚህ የሁለተኛው ቡድን ጉዞና ድርጊቶች እንደሚከተለው ይጠቃለላሉ።

1.	የዕዝራ ፈቃድ መቀበል	ዕዝራ 7-8:31
2.	መድረስና መሥሞዕት ማቅረብ	ዕዝራ 8:32-36
3.	ተሀድሶ፣ ንስሐና መነቃቃት	ዕዝራ 9-10

(6). ዕዝራ 9-10 ያሰውን ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያልታዘዙት በምን ዋና ነገር ላይ ነበር?
ለ. ይህ አለመታዘዝ በጣም ከባድ የሆነው ለምን ነበር?

የሦስተኛው ተመላሾች ነህምያ 1-13 አንብብ

ነህምያ ከታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ባለታሪኮች አንዱ ነው። ለንጉሡ ለአርጤክሰስ የወይን ጠጅ አሳላፊ መሆኑ በፍርስ ቤተ መንግሥት ከፍተኛ

ስልጣን እንደነበረው ያሳያል። በኢየሩሳሌም የነበረው ሁኔታ አስከፊ እንደሆነ ስለተነገረው ወደዚያ ለመሄድና የኢየሩሳሌምን ከተማ ለመጠገን ፈቃድ ጠየቀ። ይኸውም ከአርጤክሰስም ፈቃድ በመቀበል በተሰጡት ወታደሮች ታጅቦ ጉዞውን ወደ ኢየሩሳሌም ቀጠለ። የነበረው የሥልጣን ሥፍራና እንዴ እግዚአብሔር ሰው የሚታይበት መንፈሳዊ ባሕሪያት ተደምረው አይሁዶች እንዲበረታቱ አድርገዋቸዋል።

በአይሁድ ጠላቶች ተቃውሞ ሳይረታ በ52 ቀናት ውስጥ የኢየሩሳሌምን ከተማ ቅጥር አስጠግኖ ጨረሰ። ቅጥሩም ካለቀ በኋላ በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ነዋሪዎች ቁጥር ጨመረ። ሁኔታዎችንም አረጋጋ (ነህ 7:4-5፣11:1-2)። ባለጠጎች የሆኑ አይሁዶች ድሆችን እንዳይጨቁኑ ሥርዓት አስያዘ (ነህ 5-10)። ዋናው የነህምያ ተልእኮ በተጻፈው ሕግ ላይ ተመሥርቶ የአይሁዶችን ብሔራዊ ሕልውና መልሶ መገንባት ነበር (ነህ 10:28-29)። የነህምያ መጽሐፍ እከሩፈል ባጭሩ የሚከተለውን ይመስላል።

1.	የነህምያ መድረስና ተሀድሶ	ነህ 1-7
2.	በዕዝራ የሚመራ የእምልኮና የእግዚአብሔር ሕግ እንቅስቃሴ	ነህ 8-10
3.	የቤተሰቦች ሰም ዝርዝር	ነህ 11:1-12:26
4.	የቅጥሩ ምረቃ	ነህ 12:27-13:31

(7). ነህምያ 4 እና 6 ካነበብህ በኋላ ጠላቶቹ ሊያግዱት በሞከሩ ጊዜ ነህምያ የገጠመውን ተቃውሞዎች ሁሉ እንዲት እንደተቋቋመ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ሀ. በተዘበጠበት ጊዜ (4:1-6)
ለ. ሽብር ለመፍጠር እደማ ባደረጉበት ጊዜ (4:7-23)
ሐ. እርሱን ለመጉዳት መልእክት በላኩ ጊዜ (6:1-4)
መ. ሰንበላጥ እምስተኛ መልእክት በላከ ጊዜ (6:5-9)
ሠ. ሸማዕያ እንዲደበቅ በመከረው ጊዜ (6:10-14)

(8). በነህምያ 6:15-7:1 ላይ በተጻፈው ቃል መሠረት የነህምያ ጥረት የመጨረሻ ውጤት ምን ነበር?

(9). የሚከተሉት ድርጊቶች በየትኛው የስደት ተመላሾች ወቅት ወይም ዙር እንደተፈጸመ ለማመልከት ቁጥር በመስጠት አመልክት።

___ሀ. እይሁዶች ቤተ መቅደሱን ጨረሱ።
___ለ. ነህምያ ከተቃዋሚዎች ደብዳቤ ደረሰው።
___ሐ. የቅጥሩ ግንባታ ተጠናቅቆ ተመረቀ።
___መ. ዕዝራ የባዕዳን ሚስቶች እንዲወገዱ ለሕዝቡ ተናገረ።
___ሠ. የእግዚአብሔር ሕዝብ ቤተ መቅደሱን እንደገና እንዲሰሩ ቂሮስ አዘዘ።

ለአዳሾች የተነገረ መልእክት

ዓላማ 3 በሐጌና በዘካርያስ መልዕክቶች መካከል ያለውን ልዩነት ለይቶ ለማወቅ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው መልሶ የመገንባቱና የመንፈላዊ ተሀድሶው ተግባር ብዙ ተቃውሞዎች ደርሰውበታል። በውጭ የእግዚአብሔርን ሥራ መከናወን ማየት የማይፈልጉ ሲኖሩ፣ በውስጥ ደግሞ በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጡና የሚታክቱ ነበሩ። በዚህ ሁሉ የግንባታ ሥራ ወቅት ግን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የማበረታቻ ቃል ነበረው። በዚህ በመቅደሱ ጥገና ወቅት ነቢዩ ሐጌና ዘካርያስ የእግዚአብሔርን መልእክት ያስተላልፉ ነበር። መልዕክታቸው በወቅቱ ለነበረው ሕዝብ ልዩ ትርጉም ነበረው፣ በተጨማሪም ስለ ወደፊቱም ተልዘ አድርገው የሚያሳዩ ትንቢቶች ነበሩ።

ትንቢተ ሐጌ

ሐጌ የመጀመሪያውን መልእክቱን ባስተላለፈበት ወቅት የመቅደሱ የጥገና ሥራ ለ10 ዓመታት ያህል ተስተጓጉሎ ነበር። ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ቤትና ሥራ የነበራቸውን ቸልተኝነት በመውቀስ ሐጌ ተናገረ (ሐጌ 1-2 አንብብ)።

በትንቢተ ሐጌ የተጠናቀሩት አሳማሮር መልእክቶች እግዚአብሔር በ520 ዓ.ዓ. በነቢዩ በሐጌ በኩል ያስተላለፋቸው መልእክቶች ናቸው። ምንም እንኳ ሕዝቡ ከስድት ተመልሰው በኢየሩሳሌም መኖር ከጀመሩ ጥቂት ዓመታት ያለፋቸው ቢሆንም ቤተ መቅደሱ ግን ገና እንደፈረሰ ነበር። ስለዚህ መልእክቱ የሕዝቡ መሪዎች ቤተ መቅደሱን እንዲያድሱ የሚገፋፋ ነበር።

(10). ሐጌ 1:2-11 ያለውን ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ሀ. ቤተ መቅደሱን ከመጨረስ ፈንታ ሰዎቹ ምን ያሰሩ ነበር?
ለ. የድርጊታቸው ውጤት ምን ነበር?

በሐጌ በኩል እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው አስደናቂ መልእክት ቤተ መቅደሱን እንደገና ለመሥራት ሕዝቡን አነሳሳቸው። ሆኖም ወዲያውኑ ተስፋ ቆረጡ። እግዚአብሔር ግን እንደገና ለእነርሱ መልእክት ነበረው።

(11). ሐጌ 2:1-9 አንብብ። በዚህ መልእክት መሠረት እግዚአብሔር ስለ አዲሱ ቤተ መቅደስ ምን አለ?

ሀ. ከፊተኛው ጋር እኩል ክብር ይኖረዋል።
ለ. ከፊተኛው ይልቅ ክብር ይኖረዋል።
ሐ. ከእህዛብ በተሰበሰበ ሀብት ይሞላል።

ትንቢተ ዘካርያስ

የትንቢተ ዘካርያስ መጽሐፍ 14 ምዕራፎች ብቻ ያዘለ ቢሆንም በብሉይ ኪዳን ከተጠቀሱት ትንቢቶች ውስጥ አያሌ የሚሆኑ አስደናቂ ትንቢቶችን ይዞአል። ከሐጌ በኋላ ተጀምሮ የነበረው የመቅደስ ጥገና ቆመ። በዚህ ወቅት ነበር የመቅደሱ ሥራ ለምን እንደቆመ የሚያሳዩ 8 ራዕዮች ዘካርያስ የተቀበለው (ዘካ 1-8)። በተጨማሪ ስለ ወደፊቱ የብሩህ ተስፋ መልእክቶችን ተቀብሎ አስተላልፎአል (ዘካ 9-14)።

ዘካርያስ ስምንቱን ራዕዮች ያየው የመቅደሱ የግዕዘን ድንጋይ ከተጣለ ከሁለት ወር በኋላ ነበር። የመቅደሱ ጥገና ለምን እንደቆመ ከተለጠቱ ምክንያቶች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል።

1. ***የተሰፋ መቁረጥ ስሜት።*** እይሁዳዊ ራሳቸውን ጥቅመቢሶች አድርገው ገመቱ። ራይዳ የሌለው ሥራ እንደሚሠሩ አድርገው ልፋታቸውን ቆጠሩ። እግዚአብሔር ግን ራሱ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚመጣና ከተማይቱንም የራሱ እንደሚያደርግ ተናገረ (ዘካ 1:17)።

2. ***የጋጠአትና የአለመታዘዝ ውጤት።*** በሕዝቡ በአሰራኤል ላይ ለቅጣት የተጠቀመባቸውን ሕዝቦች እግዚአብሔር መልሶ እንደሚያሞርዳቸው ለዘካርያስ አሳየው (ዘካ 1:20-21)።

3. ***የጸጸትና የኩነኔ ስሜት።*** ሊቀ ካህን ኢያሱ ያደረ ልብስ ሰብሶና በሰይጣን ተከሶ እግዚአብሔር ለዘካርያስ አሳየው። የኢያሱ ልብሶች ግን በአዲሶች ተለወጡ፣ እግዚአብሔርም የምድሪቱን በደል እንደሚያስወግድ ቃል ገባ (ዘካ 3:5-9)።

4. የእቅመቢስነት ስሜት። እግዚአብሔር በዘካርያስ በኩል ለዘሩባቤልና ለሌሎችም ሁሉ የማበረታቻ ቃል ላከ (ዘካ 4:6)።

ከነዚህም ሌላ ዘካርያስ ብዙ ራዕዮች አየ። ለምሳሌ ያህል በዘካ 2:1-5 ላይ የሚገኝ የመለኪያ ገመድ የያዘ ሰው ራዕይ አለ። ይህ ራዕይ የሚያሳየው ኢየሩሳሌም በሕዝብ ተሞልታ የምትጥለቀለቅበት ጊዜ እንደሚመጣ ነው። እንደዚሁም በኢያሱ ተመስሎ ስለ "ቁጥቋጦ" የተነገረው የጸድቁ ትንቢት በዘካ 6:12-13 ላይ ተጽፎአል።

በሁለተኛው የዘካርያስ መጽሐፍ ክፍል (ዘካ 9-14) ስለ መሢሁና ስለ እግዚአብሔር የወደፊት ተስፋ የተነገሩ ሌሎች መልእክቶች አሉ። አሰራኤል ትነጸለች (ዘካ 13:1)፣ እንደዚሁም የዓለም ሕዝቦች በሙሉ አንድ ቀን ለእግዚአብሔር ይሰግዳሉ (ዘካ 14:9)።

(12). ዘካ 6:9-13 ላይ የተጻፈውን ደግመህ አንብብ። "ቅርንጫፍ" ተብሎ የተጠራው ሰው ሥራው ምንድነው?

(13). ቁጥሩን በተሰጠው ሰፍራ በመጻፍ አብሮ የሚሄደውን አመልክት።
1) ሐጌ 2) ዘካርያስ

____ሀ. ይህ ቤት ፈርሶ ሳለ፣ እናንተ ራሳችሁ በተዋቡ ቤቶቻችሁ ውስጥ ለመኖር ጊዜው ነውን?
____ለ. ኃጢአትህን ከእንተ አስወግጃለሁ፣ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ።
____ሐ. የዳዊትን ቤት ጌታ ከኃጢአትና ከርኩሰት ያንጻል።
____መ. የእጃችሁን ሥራ ሁሉ በሞገ፣ በአረማሞና በበረዶ መታሁት።
____ሠ. የማበረታቻ መልእክቶችን በሰምንት ተከታታይ ራዕዮች አማካኝነት ተሰጠ።

ብዙ ጊዜ የጠፉ ነገሮች ወይም የፈራረሱ ነገሮችን እንድናስተካክል እንጠራለን። እንዳንድ ጊዜ እንደቤተሰብ፣ የአምልኮ ጊዜ እንደገና መጀመር ያስፈልገን ይሆናል። በሌላ ጊዜ ደግሞ በጌታ የሆነ ወንድም ወይም እህት ተጎድተው እንድናጽናናቸው እንጠራ ይሆናል፣ ወይም የፈረሰን አገልግሎት እንደገና ለማቋቋም እንጠራ ይሆናል። በዚህ ክፍል የተማርነው ትምህርት ለእንደዚህ ዓይነት ጊዜ እጅግ ይረዳናል።

14. መልሶ ስለሚጠገን ወይም እንደገና መሰራት ስላለበት አንድ ሥራ እግዚአብሔር ተናግሮሃልን? ከተናገረህ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ አስፍር።

ስለሕዝቡ የተሰጠ
የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ

ዓላማ 4 የትንቢተ ሚልክያስን መጽሐፍ መልእክት ለመግለጽ።

ይህ የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ፣ ትንቢተ ሚልክያስ አንዳንድ ጊዜ "ትንሹ ብሉይ ኪዳን" ተብሎ ይጠራል። ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን ዋና ዋና ርዕሶች ባጭሩ ተጠቅሰው ስለሚገኙበት ነው። የእስራኤል በእግዚአብሔር መመረጥ፣ የእስራኤል ኃጢአትና አለመታዘዝ፣ ሕግን የመታዘዝ አስፈላጊነት፣ ስለሚመጣው የጌታ ቀን እና የመሳለሉት ርዕሶች ይገኙበታል። ትንቢተ ሚልክያስ የተጻፈው ከምርኮ መልስ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው።

እግዚአብሔርን ሰመታዘዝ የነበራቸው ታላቅ ፍላጎትና ጽኑ ምኞት ተለያታቸው በእምነታቸው ደክመውና ዝለው በነበሩበት ወቅት ከኃጢአታቸው በንስሐ እንዲመለሱ በመምከር፣ ስለ ወደፊቱ ያያውን ራዕይም በመናገር፣ ሚልክያስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያበረታታቸዋል (ሚል 3:1-5)። (ሚልክያስ 1-4 አንብብ)።

የሚልክያስ መልእክት ዓላማ የእስራኤልን ኃጢአት ማሳየትና ስለ ሚመጣው ፍርድ ማስጠንቀቅ ነበር። ከጌታ ቀን በፊት "ነቢዩ ኤልያስ" እንደሚመጣ ተናገረ (ሚል 3:1፣ 4:5)። በዚህ መካከል እራት መቶ ዓመታት አለፈ። የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስም መሢሁን ክርስቶስን ያውጅ ዘንድ "ነቢዩ ኤልያስ" መጣ (ማቴ 11:10-14)።

(15). ሚል 3:6-12 አንብብ። በሕዝቡ ላይ እርግማን የነበረበት ምክንያት

ሀ. እሥራትና መሰዋዕት ለእግዚአብሔር ስላልሰጡ።
ለ. በቤተ መቅደስ ለማምለክ መምጣታቸውን ችላ በላለ።
ሐ. መሉውን አሥራትና መባን ስላላመጡ።

(16). በሚል 4:1-5 ላይ በተጻፈው መሠረት "የጌታ ቀን" የሚያመለክተው

ሀ. ኃጢአተኞችን አጥፍቶ ጻድቃንን የሚፈውስበትን ጊዜ።
ለ. ነቢዩ ኤልያስን እንደገና የሚልክበት ጊዜ።
ሐ. ለኃጢአተኞች ማስጠንቀቂያዎች የሚሰጥበት ጊዜ።

(17). ስለ ሚልክያስ መልእክት እውነተኛ የሆኑት መግለጫዎች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. እግዚአብሔር የሕዝቡን ጸሎት ያልመለሰበት ምክንያት መባ ስላልሰጡ ነው።
ለ. የካህናቱን ኃጢአት የሚገስጽና ኃጢአተኞች እንደሚጠፉ የሚናገር ትንቢት ይዟል።
ሐ. ሀዝቡ መሰሪያውን ስላላከበሩ እግዚአብሔር ማዘኑን ይገልጻል።
መ. የሚልክያስ መልእክት በሕዝቡ ኃጢአት ምክንያት ኢየሩሳሌም እንደ ምትጠፋ የሚናገር ነው።

ይህ ባጭሩ ተዘጋጅቶ የቀረበው የብሉይ ኪዳን ጥናት የህያው እምላካችንን መልዕክት በሚገባ እንድትረዳ ያስችልሃል። እግዚአብሔር እምላክ በጥንት ጊዜ እንደነበረ ዛሬም ያው ነው። በኤደን ገነት ከአዳምና ከሔዋን ጋር የተመላለሰው፣ አብርሃምን እንዲያገለግለው የጠራው፣ በኃያል እጁ ሕዝቡን ከባርነት ነፃ ያወጣው፣ ከሙሴ ጋር ፊት ለፊት የተነጋገረው፣ መዝሙሮችን እንዲጽፍ ዳዊትን የመረጠው፣ በአገልጋዮቹ በነቢያት አንደበትና ሕይወት የተናገረው "የዘላለም እምላክ የማይለወጥ ነው!" በብሉይ ኪዳን የተጻፈው ታሪክ ሁሉ ለእኛ ምሳሌና ትምህርት መሆኑን የሚገልጽ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ እንደተናገረው (1ቆሮ 10:11) "ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው፣ እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገስጸን ተጻፈ"። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በምታጠናበት ጊዜ ሁሉ ይህንን አስታውስ።

የመከራ ፈተና

1. እግዚአብሔር ሕዝቡን ጠብቆ ከምርኮ ወደ ምድራቸው የመለሳቸው

ሀ. አሶር የዓለም ግዢ መሆንዋ ስለቀረ ነው።
ለ. ቂሮስ ቤተ መቅደሱን እንዲያድሱ መመሪያዎችን ስለሰጠ ነው።
ሐ. ለመላው ዓለም የሚለጥት መልእክት ስለነበራቸው ነው።
መ. ዓለም በምሥራቅ መንግሥታት ቁጥጥር ስር ስለነበረች ነው።

2. እንደገና የመገንባቱን ሂደት ሦስት ደረጃዎች በተሻለ መንገድ የሚያቀርበው መግለጫ የትኛው ነው?

ሀ. ከውጪ ተቃውሞ ከውስጥ ደግሞ ተስፋ መቁረጥ ቢኖርም፣ ቤተ መቅደሱና የኢየሩሳሌም ቅጥር እንደገና ተሠራ፣ ይህም በዘሩባቤል፣ በኢያሱ፣ በዕዝራና በነህምያ መሪነት ከመቶ ዓመታት በላይ ፈጅቶአል። ለእግዚአብሔር ሕግ በመታዘዝ የቤተ መቅደስ አምልኮ በመልካም ሁኔታ ይካሄድ ነበር።
ለ. ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰው በወታደሮች ታጅቦ ከንጉሥ አርጤክስስ የተጻፈ ደብዳቤ ይዞ ነበር። ጠላቶቻቸው ቢያሾፉባቸውና ሊገድሏቸው ቢያቅዱም፣ የኢየሩሳሌም ቅጥርን እንደገና ከመገንባት አላስቀሩአቸውም። ቅጥሩ ተገንቦቶ እንዳለቀም የእግዚአብሔር ሕግ ተነበበ።
ሐ. አርጤክስስ በነገሠበት ዘመን ዕዝራ 1,758 ሰዎች ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። በዚያም ሲደርስ አይሁዶች የባዕድ አገር ሴቶችን እንዳገቡ ተረዳ። ከዚያም ሚስቶታቸውን በማስወገድ ከመጥፎ ልማዳቸው እንዲመለሱ አደረጋቸው። በእርሱም መሪነት የአምልኮ ሥርዓት በጥሩ ሁኔታ መካሄድ ጀመረ።

3. በሁለተኛው ጥያቄ ሥር ከሰፈሩት የሁለተኛውን ዙር የስደት ተመላሾች ድርጊቶች የሚገልጸው የትኛው ነው።

ሀ. መግለጫ "ሀ" ለ. መግለጫ "ለ" ሐ. መግለጫ "ሐ"

4. ሰዎች ምንም እንኳ ተቃውሞ ቢገጥማቸውም ለጌታ መሥራታቸውን እንዲቀጥሉ ለማበረታታት ብትፈልግ እንደ ምሳሌ አድርገህ ለመጠቀም ከሚከተሉት ጥሩ የሚሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ከባዕድ አገር ሴቶች ጋር ጋብቻን ለማሰቆም የዕዝራ እቅድ።
ለ. ነቢዩ ዘካርያስ ስለመሲሒያ ገመድ ያየው ራዕይ።
ሐ. በሁለተኛው ዙር የስደት ተመላሽ ወቅት ዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕግና የአምልኮን ሥርዓት በሚገባ እንዲጎለብቱ ማሳደጉ።
መ. የቅጥሩ ግንብ እንደገና በሚሠራበት ወቅት የነህምያ ልምምድ።

5. በተሰጠው ስፍራ ቁጥሩን በማስፈር ከመግለጫው ጋር አብሮ የሚሄደውን አመልክት።

1. አርጤክስስ
2. ቂሮስ
3. ዳርዮስ
4. ዕዝራ
5. ሐጌ
6. ኢያሱ
7. ሚልክያስ
8. ነህምያ
9. ዘካርያስ
10. ዘሩባቤል

___ሀ. የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን ዙር የስደት ተመላሾች ገለጻ ጻፈ።
___ለ. ቤተ መቅደሱን እንደገና እንዲገነቡ የመጀመሪያውን ዓሞጅ አወጣ።
___ሐ. እዲስ ልብስ ሲቀበል ለዘካርያስ በራዕይ የታየ።
___መ. በሦስተኛው ዙር የስደት ተመላሽ ወቅት የፋርስ ንጉሥ የነበረ።
___ሠ. አሥራታቸውን ባሰመነፈላቸው እግዚአብሔርን እንዳታለሉ ለሕዝቡ ተናገረ።
___ረ. የቅጥሩን እንደገና መገንባት ተቆጣጠረ።
___ሰ. ቤተ መቅደሱን እንደገና መሥራት ችላ በማለታቸው ሕዝቡን ገሰጸ።
___ሸ. እንደገና ስለ መገንባቱ 8 ተከታታይ ራዕዮች ተሰጠው።
___ቀ. የነቢዩ ኤልያስን መምጣት ተነበየ።
___በ. የመጀመሪያውን ዙር የስደት ተመላሾች መራ።
___ተ. በቂሮስና በአርጤክስስ መካከል የነገሠ የፋርስ ንጉሥ።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

9. ሀ. 1
   ለ. 3
   ሐ. 3
   መ. 2
   ሠ. 1

1. ሀ. ስለምርኮው ዘመን እግዚአብሔር የሰጠውን ትንቢት አነበበ።
   ለ. የሕዝቡን ኃጢአት ተናዘዘ።
   ሐ. እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሳ የሕዝቡን ኃጢአት ይቅር እንዲልና ቤተ መቅደሱን እንደገና እንዲያስ ጠየቀ።

10. ሀ. የራሳቸውን ቤቶች ይሰሩ ነበር።
    ለ. ሰብላቸው እንዲያንስና በምድራቸውም ላይ ድርቅ እንዲመጣ አደረገ

2. እግዚአብሔር ስለመንግስቱ ያለው መልዕክት ለመላው ዓለም እንዲዳረስ ስለፈለገ ይህንን መልዕክት የያዙትን ሕዝቡን በምርኮ ዘመን ከነበረው ጥፋትና መደምሰስ ጠብቆ ወደ ኢየሩሳሌም መለሳቸው።

በዚህም መንገድ ከሕዝቡ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ጠበቀ። ለዓለም ያለውም መልዕክት እንዳይጠፋ አደረገ። (መልስህ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት)

11. ለ እና ሐ

3. ሀ. በኢየሩሳሌም ለጌታ ቤተ መቅደስ እንዲሰራ።
ለ. ለጉዞአቸው የሚያስፈልጋቸውንና ለጌታ የሚሆን መሳ በመስጠት።

12. የጌታን ቤተ መቅደስ መገንባት።

4. ሀ. እውነት ሐ. ሐሰት
ለ. ሐሰት መ. እውነት

13. ሀ. 1) ሐጌ 1:4 መ. 1) ሐጌ 2:17
ለ. 2) ዘካ 3:4 ሠ. 2) ዘካ 1:7-6:8
ሐ. 2) ዘካ 13:1

5. እንዲመለሱ እግዚአብሔር ልባቸውን አነሳሳ።

14. የራስህ መልስ። እግዚአብሔር ለዘሩባቤል ምን እንዳለው አስታውስ። አንተም እንደማንበታው ሥራ ውጤታማ ልትሆን ትችላለህ።

6. ሀ. የባዕድ አገር ሴቶችን በማግባታቸው ነበር።
ለ. በእግዚአብሔር የተከለከለ ስለሆነና ሕዝቡን ወደ ባዕድ አምልኮና ወደ ኃጢአት ለለሚመሩ። (መልስህ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት)

15. ሐ

7. ሀ. ጸለየ፣ መስራቱንም ቀጠለ።
ለ. በእግዚአብሔር እንዲታመኑ ለሕዝቡ ነገራቸው፣ የመር መሳሪያዎችም ሰጣቸው።
ሐ. እንደማይመጣና እንደማያገኛቸው አስታወቃቸው።
መ. እየሞሸ ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ እንደነበር ነገራቸው።
ሠ. የሸማዕያ ምክር የተሳሳተ መሆኑን ለደቆ ስላወቀ በእግዚአብሔር ላይ ታመነ። (መልስህ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት)

16. ሀ

8. የቅጥሩ ሥራ ተሰርቶ አለቀ፣ ሊሞውያንም በሥራቸው ተመደቡ። (ተመሳሳይ የሆነ መልስ)

17. ሀ. ሐሰት ለ. እውነት ሐ. እውነት መ. ሐሰት

የመከራ ፈተና መልሶች

ክፍለ ትምህርት አንድ

1. ሐ
2. ሀ
3. ሀ. ሐሰት ሐ. እውነት
ለ. ሐሰት መ. እውነት
4. ሐ
5. ለ
6. ሀ እና መ
7. ለ እና መ

ክፍለ ትምህርት ሁለት

1. ሀ
2. ለ
3. ሀ. ሐሰት ሐ. ሐሰት
ለ. ሐሰት መ. እውነት
4. ሐ
5. ለ
6. ሀ
7. ሐ
8. ሀ. 6 ሠ. 9 ቀ. 4
ለ. 3 ረ. 7
ሐ. 5 ሰ. 2
መ. 1 ሸ. 8

9. ሀ. እውነት ሐ. እውነት
ለ. ሐሰት

ክፍለ ትምህርት ሦስት

1. ሀ
2. ሐ
3. ሐ
4. ለ
5. ለ
6. ሀ. እውነት መ. እውነት
ለ. እውነት ሠ. ሐሰት
ሐ. ሐሰት ረ. ሐሰት

ክፍለ ትምህርት አራት

1. ሀ. 2) የሕዝብ መተዳደሪያ ሕግ
ለ. 1) የጸኑ ምግባር ሕግ
ሐ. 3) የአምልኮ ሕግ
መ. 1) የሥነ ምግባር ሕግ
ሠ. 2) የሕዝብ መተዳደሪያ ሕግ

2. ሀ. ሐሰት ሐ. ሐሰት
ለ. እውነት

3. ሀ. 2) የግዴታ መሥዋዕት
ለ. 2) የግዴታ መሥዋዕት
ሐ. 2) የግዴታ መሥዋዕት
መ. 1) የፈቃደኝነት መሥዋዕት
ሠ. 1) የፈቃደኝነት መሥዋዕት
ረ. 1) የፈቃደኝነት መሥዋዕት
ሰ. 1) የፈቃደኝነት መሥዋዕት
ሸ. 2) የግዴታ መሥዋዕት

4. ሀ

5. ሐ

6. ለ. ክብነት
መ. የማይረሳው ድንኳን
ሠ. መሥዋዕቶች
ሸ. የነገዶች ሥፍራ
በ. በዓላትና ወቅቶች

7. ሀ. ሐሰት መ. ሐሰት
ለ. እውነት ሠ. ሐሰት
ሐ. እውነት

8. ሀ. 3) የእስራኤል ሰፈር
ለ. 1) ክብነት
ሐ. 2) የማይረሳው ድንኳን
መ. 4) መሥዋዕቶች
ሠ. 5) በዓላትና ወቅቶች

9. ሀ. 5 መ. 8 ሰ. 3
ለ. 7 ሠ. 6 ሸ. 4
ሐ. 1 ረ. 2

ክፍለ ትምህርት አምስት

1. ሀ. ሐሰት መ. ሐሰት
ለ. እውነት ሠ. ሐሰት
ሐ. እውነት

2. ለ

3. ሀ. 6 ሐ. 5 ሠ. 4
ለ. 1 መ. 2 ረ. 3

4. ሐ

5. ሀ እና መ

6. ለ

7. ለ

8. ሐ

9. መ

10. ሀ. 2) ሳሙኤል
ለ. 2) ሳሙኤል
ሐ. 1) ኢያሱ
መ. 3) ሁለቱም
ሠ. 2) ሳሙኤል
ረ. 1) ኢያሱ
ሰ. 3) ሁለቱም

ክፍለ ትምህርት ስድስት

1. ለ
2. ሀ. 2) ዳዊት ሠ. 3) ሰሎሞን
ለ. 1) ሳኦል ረ. 3) ሰሎሞን
ሐ. 3) ሰሎሞን ሰ. 2) ዳዊት
መ. 2) ዳዊት ሸ. 1) ሳኦል

3. ለ

4. ሀ. 2 ሠ. 3 ቀ. 8
ለ. 4 ረ. 5 በ. 6
ሐ. 7 ሰ. 9
መ. 1 ሸ. 10

5. ሀ. 4) ሰለሞን
ለ. 2) ሳኦል
ሐ. 1) ሳሙኤል
መ. 4) ሰለሞን
ሠ. 3) ዳዊት

ክፍለ ትምህርት ሰባት

1. ሀ

2. ሀ. እውነት መ. ሐሰት
ለ. እውነት ሠ. ሐሰት
ሐ. ሐሰት

3. ሠ

4. ለ

5. ለ

6. ሐ

7. ሀ. 4) መዝሙረ ዳዊት 66:1-2
ለ. 1) ኢዮብ 34:32
ሐ. 3) መክብብ 1:14
መ. 5) መኑልየ መኑልዩ
ሠ. 1) ኢዮብ 42:5
ረ. 2) ምሳሌ 23:9

ክፍለ ትምህርት ስምንት

1. ሐ

2. ሀ. እውነት መ. እውነት
ሰ. ሐሰት ሠ. ሐሰት
ሐ. ሐሰት

3. ሀ እና መ

4. ሀ. 2) ያዕቆብ ሐ. 1) ሰሜን
ለ. 1) ሰሜን

5. ሐ

6. ሀ. ሐሰት መ. ሐሰት
ለ. እውነት ሠ. እውነት
ሐ. ሐሰት

ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

1. ሀ) ሶርያ

2. ሀ. ሐሰት ሐ. እውነት
ለ. ሐሰት

3. ሀ. 5 ሐ. 2 ሠ. 3
ለ. 4 መ. 1 ረ. 6

4. ሀ. 2) መንገድ
ለ. 1) ምክንያት
ሐ. 1) ምክንያት
መ. 3) ጥቅም
ሠ. 3) ጥቅም

ክፍለ ትምህርት አሥር

1. ሐ
2. ሀ
3. ሐ
4. መ
5. ሀ. 4) ዕዝራ
ለ. 2) ቂሮስ
ሐ. 6) ኢያሱ
መ. 1) አርጤሰስስ
ሠ. 7) ሚልክያስ
ረ. 8) ነህምያ
ሰ. 5) ሐጌ
ሸ. 9) ዘካርያስ
ቀ. 7) ሚልክያስ
በ. 10) ዘሩባቤል
ተ. 3) ዳርዮስ

እስጀምር ላስፈፈርስን ለእግዚአብሔር ከዘላለም እስከዘላለም ክብር ይሁን። አሜን!!